# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ሐሙስ

83ኛ ዓመት ቁጥር 290 ሰኔ 20 ቀን 2016 ዓ.ም ዋጋ 10:00

ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!







## “የንብረት ማስመለስ አዋጁ ዓላማ በሕግና በሥርዓት የሚመራ ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴ እንዲኖር ማስቻል ነው”

- ጌዲዮን ጢሞቲዎስ (ዶ/ር)
የፍትሕ ሚኒስትር



ፎቶ - ሀዱሽ አብርሀ

**አዲሱ ገረመው**

አዲስ አበባ፡- የንብረት ማስመለስ ረቂቅ አዋጁ ዓላማ ጤናማ፣ ፍትሐዊ የሆነ በሕግና ሥርዓት የሚመራ ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴ እንዲኖር ማስቻል እንደሆነ የፍትሕ ሚኒስትሩ ገለጹ፡፡

ሚኒስትሩ የኢ.ፌ.ዴ.ሪ የንብረት ማስመለስ ረቂቅ አዋጁን ዓላማ፣ ይዘትና አሁን የደረሰበትን ሁኔታ አስመልክተው ለመገናኛ ብዙኃን በሰጡት መግለጫ እንዳስታወቁት፣ የንብረት ማስመለስ ረቂቅ አዋጁ ጤናማ፣ ፍትሐዊና በሕግና ሥርዓት የሚመራ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴን ለመፍጠር ያስችላል ብለዋል፡፡

የገንዘብ ምንጭ፣ የሀብትና የንብረት እንቅስቃሴ የኢኮኖሚውን ጤናማነት ፍትሐዊነት በሕግና በሥርዓት እንዲመራ ይወስናል ሲሉ ገልጸዋል፡፡

የኢ.ፌ.ዴ.ሪ የንብረት ማስመለስ ረቂቅ አዋጅ ኢኮኖሚያዊ ወንጀሎችን ለመከላከል እና የሀብት የማስመለስ መርሕን እውን ለማድረግ መዘጋጀቱን ጠቅሰው፤ የአዋጁ ዓላማ ወጥ የሕግ ማዕቀፍ ለማዘጋጀት

“የንብረት ማስመለስ... ወደ ገጽ 14 ዞሯል








ፎቶ፡ በረከት ታደሰ

## ኢትዮጵያዊቷ ላምበርጊን

ገጽ 14



ፎቶ፡ በረከት ታደሰ

## “የኅብረተሰቡን ተሳትፎ ማሳደግና የጎደሉ ነገሮችን ቆጥረን መሙላት ከቻልን ብልፅግናን ለማረጋገጥ የጀመርነው ሥራ የሚሳካበት ጊዜ ሩቅ አይሆንም”

- አቶ እንዳሻው ጣሰው
የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ርዕሰ መስተዳድር

ገጽ 14

## በዘንድሮው ፈተና የተሻለ ውጤት ለማስመዝገብ መዘጋጀታቸውን የ12ኛ ክፍል ተፈታኞች አስታወቁ

**ሳሙኤል ወንደሰን**

አዲስ አበባ፡- በዘንድሮው የ12ኛ ክፍል ሀገራዊ ፈተና የተሻለ ውጤት ለማምጣት አስፈላጊውን ዝግጅት ማድረጋቸውን ተፈታኞች ገለጹ።

የኮተቤ ቀዳማይ ምኒሊክ ሳይንስ ሼርድ ካምፓስ ተማሪ ኤፍሬም አምሳሉ ለኢፕድ እንደገለጸው፤ የሞዴል ፈተና ከዘጠነኛ እስከ አሥራ ሁለተኛ ክፍል ድረስ ያለውን ትምህርት አካቶ የያዘ ነው። ይህም ተማሪዎች የማትሪክ ፈተና ሊኖረው የሚችለውን ይዘት እንዲረዱ ያደርጋል ብሏል።

እስከ አሁን አምስት የሞዴል ፈተናዎችን እንደወሰደ እና ራሱን ለማትሪክ ፈተና ብቁ ለማድረግ ከመማሪያ መጽሐፍት በተጨማሪ አጋዥ መጽሐፎች ማንበቡን የገለጸው ተማሪ ኤፍሬም፤ ይህም በማትሪክ ፈተና ጥሩ ውጤት እንዲኖረው እንደሚያደርግ ገልጿል።


ለሞዴል ፈተና ያነበባቸውን በአጭሩ እና ሊገባው በሚችል መልኩ አዘጋጅቶ ማስቀመጡ የማትሪክ ፈተና



ተማሪ ቅድስት ወርቁ



ተማሪ ደራርቱ ኩማ



ተማሪ ኤፍሬም አምሳሉ

የሚኖረውን ይዘት ከወዲሁ እንዲረዳ ዕድል እንደሰጠው የገለጸው ተማሪ ኤፍሬም፤ በማትሪክ ፈተና የተሻለ ውጤት ለማምጣት አስፈላጊውን ዝግጅት እያደረገ መሆኑን ተናግሯል።

በዳግማዊ ምኒሊክ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የተፈጥሮ ሳይንስ ተማሪ ደራርቱ ኩማ በበኩሏ፤ የዘንድሮ የማትሪክ ፈተና ከበፊቱ የተለየ ነው። ይህም በኦንላይን የሚሰጥ መሆኑ ነው። አምና በርካታ ተማሪዎች ዝቅተኛ ውጤት ማምጣታቸው ፍርሐት አሳድሮባት እንደነበር ገልጻለች።

ይህንን ፍርሐቷን ለማጥፋት ትምህርት ከተጀመረበት ጊዜ አንስቶ ስታነብ እና የማትሪክ ፈተናዎችን ጥያቄ

በዘንድሮው ፈተና... ወደ ገጽ 14 ዞሯል






አምባሳደር በርክ በራንን

# ተርክዬ ከኢትዮጵያ ጋር ያላትን የንግድ ልውውጥ ለማሳደግ በቁርጠኝነት እየሠራች ነው

**ሞገስ ፀጋዬ**

አዲስ አበባ፡- ተርክዬ ከኢትዮጵያ ጋር ያላትን የንግድ ልውውጥ ለማሳደግ በቁርጠኝነት እየሠራች መሆኑን በኢትዮጵያ የተርክዬ አምባሳደር በርክ በራንን አስታወቁ።

በኢትዮጵያ የተርክዬ አምባሳደርና የአፍሪካ ኅብረት ቋሚ ተወካይ በርክ ባራን ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ኢትዮጵያና ተርክዬ 128 ዓመታትን ያስቆጠረ ጠንካራ የዲፕሎማሲ ትስስር አላቸው፡፡

በተለይ የሁለቱ ሀገራት የሕዝብ ለሕዝብ ግንኙነቱ ረጅም ዘመን የተሻገረ ስለመሆኑ የገለጹት አምባሳደሩ፤ አጠቃላይ ሁለቱ ሀገራት በሁሉም ዘርፍ ጠንካራ የሚባል ግንኙነት ያላቸው ሲሆን፤ የንግድ ልውውጣቸው ጥብቅ ነው፡፡ በኢትዮጵያ ከተሰማሩ የውጭ አልሚዎች ተርክዬ አራተኛ ደረጃ ላይ እንደምትገኝ ገልጸዋል፡፡

በኢትዮጵያ በርካታ የኢንቨስትመንት አማራጮች መኖራቸውን የጠቀሱት አምባሳደሩ፤ በኢትዮጵያ በሁሉም ዘርፍ ወደ ኢንቨስትመንት ለመሰማራት ግዙፍ አቅም አለ። ተርክዬ ከኢትዮጵያ ጋር ያላትን የንግድ ልውውጥና ግንኙነት ለማሳደግና ለማጠናከር በቁርጠኝነት እየሠራች ትገኛለች ብለዋል፡፡

በሁለቱ ሀገራት መካከል ያለውን የንግድ መጠን ለማሳደግ እየሠራን ሲሆን የተርክዬ የንግዱ ማኅበረሰብ ልዑካን ቡድን ወደ ኢትዮጵያ በመምጣት በኢንቨስትመንት ለመሰማራት ያሉ ዕድሎችን ተመልክተዋል፡፡ የተርክዬ የንግድ ሚኒስቴር በሁለቱ ሀገራት መካከል ያለው የንግድ ልውውጥ እንዲያድግ ድጋፍ እንደሚያደርግም ገልጸዋል።

እንደ አምባሳደር በርክ ገለጻ፤ ኢትዮጵያ ግዙፍ የኢኮኖሚና የንግድ አቅም አላት፡፡ በአፍሪካ ሁለተኛ የሕዝብ ቁጥር ባለቤት መሆኗ ተጨማሪ አቅም ነው። የተርክዬ አልሚዎች በኢትዮጵያ ለማልማት ፍላጎት ስላላቸው አንዳንድ ችግሮች ከተስተካከሉ በርካታ የተክርዬ ባለሀብቶች ወደ ኢትዮጵያ ይሰማራሉ። በርካታ አልሚዎች ወደ ኤምባሲ በመምጣት በኢትዮጵያ ስላለው የኢንቨስትመንት አማራጭና የትኛው ዘርፍ የተሻለ እንደሆነ ይጠይቃሉ፡፡ በኢትዮጵያ ያለው የተፈጥሮ ሀብትና የግብርናው ዘርፍ ሰፊ መሆኑን በመጥቀስ ኢትዮጵያ ለአልሚዎች ምቹ ናት ብለዋል፡፡

እንደ አምባሳደሩ ገለጻ፤ በአሁኑ ወቅት የተርክዬ ባለሀብቶች በኢትዮጵያ በጨርቃጨርቅ ፋብሪካዎች፣ በኮንስትራክሽን ምርቶችና በኬብል ኢንዱስትሪዎች በስፋት ተሰማርተዋል፡፡ በሁለቱ ሀገራት መካከል ያለው የንግድ ልውውጥ ከጊዜ ወደ ጊዜ እያደገ ነው፡፡ ተርክዬ ከኢትዮጵያ ጋር ያላት የንግድ ልውውጥም ሦስት መቶ ሚሊዮን ዶላር የደረሰ ሲሆን በኢትዮጵያ በኩል ሰባት መቶ ሚሊዮን ዶላር መድረሱን ገልጸዋል፡፡ ኢትዮጵያም የተርክዬን ምርቶች በቀጥታ ከተርክዬና ከሌሎች ሀገራት ስለምታስገባ የንግድ ልውውጥ ልዩነት አለ ብለዋል፡፡

የአየር ንብረት ለውጥ የዓለም ፈተና ነው ያሉት አምባሳደሩ፤ ሁሉም ሀገር የአየር ንብረት ለውጥን ለመከላከል ኃላፊነት አለበት፡፡ ይህን ኃላፊነት ለመወጣት በአረንጓዴ ኃይል ልማት ተነሳሽነት ላይ ማልማት አለባቸው፡፡ ለዚህ ደግሞ አፍሪካ ግዙፍ አቅም አላት። አፍሪካ ለአየር ንብረት ለውጥ ያላት አስተዋፅዖ አናሳ ቢሆንም ግንባር ቀደም ተጠቂ አሕጉር መሆኗን ጠቅሰዋል፡፡

# "የግልና የመንግሥት አጋርነት የግሉ ዘርፍ መሪነት የተረጋገጠበት ኢኮኖሚ ለመገንባት አይነተኛ መሣሪያ ነው"

**- በለጠ ሞላ(ዶ/ር)**
**የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስትር**

**ፋንታነሽ ክንዴ**

አዲስ አበባ፡- የግልና የመንግሥት አጋርነት የፖለቲካ ኢኮኖሚ ምሕዳሩ የግሉ ዘርፍ መሪነት የተረጋገጠበት የኢኮኖሚ ልማት ለመገንባት አይነተኛ መሣሪያ መሆኑን የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስትር በለጠ ሞላ(ዶ/ር) ገለጹ።

የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር ከግሉ ዘርፍና ባለድርሻ አካላት ጋር በ2016 በጀት ዓመት ክንውኖችና የቀጣይ ዓመት አቅጣጫዎች ዙሪያ ትናንት ምክክር አድርጓል።

ሚኒስትሩ በለጠ ሞላ (ዶ/ር) በመድረኩ ላይ እንደገለጹት፤ የሳይንስ ቴክኖሎጂ እና የኢኖቬሽን ልማት የሁሉንም ባለድርሻ አካላት ተሳትፎ የሚፈልግ ነው። የግልና የመንግሥት አጋርነት የፖለቲካ ኢኮኖሚ ምሕዳሩ የግሉ ዘርፍ መሪነት የተረጋገጠበት የኢኮኖሚ ልማት ለመገንባት አይነተኛ መሣሪያ ነው።

መንግሥት፣ የግሉ ዘርፍ፣ ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት እና የልማት አጋሮች በቅንጅት በሳይንስ፣ ኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ልማቱ ውስጥ ሊሳተፉ ይገባል ያሉት ሚኒስትሩ፤ በተለይ የግል ዘርፉ የማይተካ ሚና አለው ብለዋል።

በበጀት ዓመቱ የግሉን ዘርፍ ተሳትፎ የሚያጠናክሩ የተለያዩ ተግባራት መከናወናቸውን አስታውሰው፤ በተለይ በምክትል ጠቅላይ ሚኒስትሩ የሚመራ የዲጂታል ትራንስፎርሜሽን ምክር ቤት ተመሥርቶ ወደ ሥራ መገባቱ ዘርፉን ለማሳደግ ከተሠሩ ሥራዎች ውስጥ ተጠቃሽ ነው ሲሉም ጠቅሰዋል።

በተለያየ ጊዜ የተከናወኑ ሁነቶች በሀገራችን



በቴክኖሎጂ እና ኢኖቬሽን መስክ የተሠማራው የግል ዘርፍ ያለውን እምቅ አቅም ያመላከተ መሆኑን ጠቅሰው፤ አቅምን በሚገባ ጥቅም ላይ ለማዋል እንዳይቻል እንቅፋት የሆኑ ጉዳዮች መኖራቸውንም አመላክቷል።

ከመንግሥት ፍላጎት አንጻር በዘርፉ የተሰማሩ የግል ዘርፍ እና የመንግሥት አስፈጻሚ አካላት በመደበኛ ሁኔታ ቀርበው የሚወያዩበት የራሱ አሠራር ያለው መደበኛ የውይይት እና የምክክር መድረክ በተፈለገው ደረጃ እንዳልተከናወነም ጠቁመዋል።

የመድረኩ ዋና ዓላማም ይህን የአሠራር ክፍተት ለመሙላት የተጠናውን ጥናት በባለድርሻዎች ግብዓት እና አስተያየት አዳብሮ ወደ ሥራ እንዲገባ ማድረግ ነው ብለዋል።

እንደ ሚኒስትሩ ገለጻ፤ መንግሥት በሚያወጣቸው ስትራቴጂዎች ላይ የግል ዘርፉን አቅም መገንባትና ተሳትፎውን ማረጋገጥ በሚሉ ስትራቴጂያዊ ጉዳዮች ላይ ሲያተኩር ነበር። በተለይ በቴክኖሎጂ እና ኢኖቬሽን ፖሊሲውም ሆነ በዲጂታል ትራንስፎርሜሽን ስትራቴጂው ላይ በግልጽ እንደተቀመጠው በቴክኖሎጂ እና ኢኖቬሽን ልማት ላይ የግሉ ዘርፉ የመሪነት ሚናውን ሊወጣ ይገባል በሚል እሳቤ የተቀመጠ ነው። የግል እና የመንግሥት አጋርነት ይህንን እሳቤ ወደ መሬት ለማውረድ ጉልህ አስተዋፅዖ ይኖረዋል።

የግልና የመንግሥት አጋርነትን ለማጠናከር የሚፈጠርባቸውን ዓውዶች መለየት፣ የሚፈጠርባቸው የአሠራር ሂደቶችን መዘርጋት እና መተግበር ከዛም ቀጣይነት ያለው የውጤት ምዘናና ወቅታዊ የማስተካከል እርምጃ መውሰድ እንደሚያስፈልግ ገልጸው፤ አጋርነቱ ውጤታም እንዲሆንም መደበኛ ቅርጽ እና የአሠራር ሥርዓት ሊበጅለት ይገባል ብለዋል።

በቴክኖሎጂ እና ኢኖቬሽን ዘርፍ የግል እና የመንግሥት አጋርነት መድረኮችን ለመመስረት እና መሥርቶም ወደ ተግባር ለመግባት እንቅስቃሴዎች እንደነበሩ አስታውሰው፤ በቀጣይ ወደ ተግባር የምናስገባው የግል እና የመንግሥት አጋርነት መድረክ ከዚህ በፊት ከነበሩ መድረኮች ጠንካራ ጎኖችን የሚያጎለብቱ እና በክፍተት ከታዩ ጉዳዮች ደግሞ ትምህርት የሚወስድ ይሆናል።

አጋርነቱ ውጤታማ እንዲሆን የግሉ ዘርፍ ከተሳታፊነት ባለፈ የአጋርነት መድረኩን በመምራት ንቁ ተሳትፎ ማድረግ ይጠበቅበታልም ብለዋል።

# የትጥቅ ትግል እያደረጉ ያሉ አካላት ጥያቄያቸውን በሠላማዊ መንገድ ለውይይትና ለድርድር እንዲያቀርቡ ጥሪ ቀረበ

**መዓዛ ማሞ**

አዲስ አበባ፡- የትጥቅ ትግል እያደረጉ ያሉ አካላት ጥያቄያቸውን በሠላማዊ መንገድ ለውይይትና ለድርድር እንዲያቀርቡ የአማራ ክልል የኅብረተሰብ ክፍሎች ጥሪ አቀረቡ፡፡

በአማራ ክልል ከሁሉም የክልሉ አካባቢዎች እና ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የተውጣጡ ልዩ ልዩ የኅብረተሰብ ክፍሎች ከሰኔ 17 እስከ ሰኔ 18 በባሕር ዳር ከተማ ያካሄዱትን ክልላዊ የሠላም ኮንፈረንስ ሲያጠናቅቁ ባለ 10 ነጥብ የአቋም መግለጫ አውጥተዋል፡፡

የኅብረተሰብ ክፍሎቹ በአቋም መግለጫቸው በትጥቅ ትግል ላይ የሚገኙት ወገኖች እንታገልለታለን የሚሉት ሕዝብ ችግርና የሕልውና ፈተና እንደገጠመው ገልጸው የትጥቅ ትግል እያደረጉ ያሉ አካላት ጥያቄያቸውን በሠላማዊ መንገድ በውይይትና በድርድር በማቅረብ ኅብረተሰቡን እንዲቀላቀሉ ጠይቀዋል፡፡

መንግሥትም ሆደ ሰፊ በመሆን ከታጣቂ ኃይሎቹ ጋር በመወያየት እና በመደራደር ለሕዝብ ሠላም ሲባል በይቅርታ እንዲቀበላቸውም ጥሪ አቅርበዋል፡፡

በሠላምና በፀጥታ፣ በፖለቲካ፣ በማኅበራዊ፣ በመልካም አስተዳደር፣ በማንነትና በራስ አስተዳደር ጉዳይ እንዲሁም ሕገ መንግሥትን ስለማሻሻል አስመልክቶ የተነሱ ጥያቄዎች በየፈርጃቸው ለፌዴራል መንግሥትና ለክልሉ መንግሥት እንዲቀርቡ ስምምነት ላይ መደረሱን የጠቆመው የአቋም መግለጫው መንግሥት የሕዝቡን ጥያቄ ለመፍታት ያለው ቁርጠኝነት እና ዝግጁነት እየታየ በሠላማዊ መንገድ በውይይት ጥያቄዎቹ እንዲፈቱ መጠየቃቸውን እንደሚቀጥሉ ተጠቁሟል፡፡

በክልሉ ውስጥ ያሉት የልማት ጥያቄዎች ያለ ሠላም ሊታሰቡ የማይችሉ በመሆኑ ጥቄዎች በሠላማዊ መንገድ ብቻ እንዲፈቱ የበኩላቸውን ድርሻ ለመወጣት መስማማታቸውን በአቋም መግለጫቸው ጠቁመው



የሚዲያ ተቋማትና ሙያተኞች እንዲሁም የማኅበረሰብ አንቂዎች የክልሉ ሕዝብ ያለበትን ዘርፈ ብዙ ችግር በመገንዘብ ሕዝቡን ወደ ሠላም የሚመልስ የሚዲያ ሥራ እንዲሠሩ ጠይቀዋል፡፡

የመንግሥት ባለሥልጣናት፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች፣ ምሑራን፣ የኪነጥበብ ባለሙያዎች፣ በውጭ ሀገራት የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ዲያስፖራዎች፣ እንዲሁም መላ ኢትዮጵያውያን በሙሉ፤ በክልሉ ከተፈጠረው ቀውስ በመውጣት አስተማማኝና ዘላቂ ሠላም ለመገንባት በሚደረገው ጥረት የሠላም ድጋፍ እንዲያደርጉ በአቋም መግለጫው የተጠየቀ ሲሆን ከመገፋፋትና ከመጠላለፍ ፖለቲካ በመውጣት ለክልሉ ሕዝብ ሠላማዊ እንቅስቃሴ በጋራ እንዲቆሙም ጥሪ ተላልፏል፡፡

በአማራ ክልል ማንኛውም ዜጋ በብሔሩ ወይም በእምነቱ ወይም በሌሎች ምክንያቶች የማይገለልበት ክልል እንዲሆን እኛም እንደቀደመው ሁሉ እንደምንሠራ ቃል እንገባለን ያሉት የሠላም ኮንፈረንሱ ተሳታፊዎች በክልሉ ውስጥ የሚንቀሳቀሱ የፌዴራልና የክልል የፀጥታ ኃይሎች የጀመርነው የሠላም ጥረት እንዲሳካ የበኩላችሁን ጥረት እንድታደርጉና ከጫካ የሚመጡ ወንድሞቻችሁን በፍፁም ሙያዊ ዲስፕሊንና ኢትዮጵያዊ ጨዋነት አቀባበል ታደርጉላቸው ዘንድ ጥሪያችንን እናስተላልፋለን ብለዋል በአቋም መግለጫቸው፡፡

በክልሉ ውስጥ በተፈጠረው ችግር ተጠርጥረው በሕግ ቁጥጥር ስር የዋሉ ፖለቲከኞች፣ ጋዜጠኞች፣ ምሑራን፣ እንዲሁም ተፅዕኖ ፈጣሪ ዜጎችን መንግሥት በይቅርታና በምሕረት ነፃ እንዲወጡ እና ለዘላቂ ሠላም ሚናቸውን እንዲወጡ እንዲያደርግም በመግለጫው ጥያቄ ቀርቧል፡፡

በጫካ የሚገኙ ወንድሞቻችን በሠላማዊ መንገድ በውይይትና በድርድር ወደ ማኅበረሰቡ ከተቀላቀሉ በኋላ በሀገራዊ የምክክር ኮሚሽኑ ውስጥ በንቃት እንዲሳተፉ በማድረግ ሁሉም አካል የበኩሉን እንዲወጣ በአቋም መግለጫው ጥሪ ተላልፏል፡፡

# የውጭ ባለሃብቶች እንዲገቡ የሚፈቅደው አዋጅ ለሚመለከተው ቋሚ ኮሚቴ ተመራ

## - የሀገር ውስጥ ባንኮች የመወዳደር ብቃታቸው ሲታይ እንደሚገባም ተጠቁሟል

**ዘሳለም ግዛው**

አዲስ አበባ፡- በባንክ ዘርፉ የውጭ ባለሃብቶች እንዲገቡ የሚያስችል ማዕቀፍ ይዘረጋል የተባለው አዋጅ ቁጥር 30/2016 የባንክ ሥራ ረቂቅ አዋጅ ለፕላን፣ በጀትና ፋይናንስ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ተመራ፡፡

የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ባካሄደው 34ኛ መደበኛ ስብሰባው የባንክ ሥራ ረቂቅ አዋጅን መርምሮ ለዝርዝር እይታ ለፕላን፣ በጀትና ፋይናንስ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ በሙሉ ድምፅ መርቷል፡፡

በረቂቅ አዋጁ ዙሪያ ማብራሪያ የሰጡት የመንግሥት ተጠሪ ሚኒስትር ተስፋዬ በልጅጌ (ዶ/ር)፤ የውጭ ባንኮችና ኢንቨስተሮች በዘርፉ ተሰማርተው ለኢኮኖሚው ቀጣይ ዕድገት የበኩላቸውን አበርክቶ እንዲሰጡ በር ከፋች መሆኑን ጠቁመዋል፡፡ በመንግሥት የተላለፈው ውሳኔ ወደ ተግባር ለማሸጋገር የተተገበረ መሆኑንም ተናግረዋል፡፡

በቅርቡ በተደረገው የፖሊሲ ሪፎርም የውጭ ሀገር ዜግነት ያላቸው ትውልደ ኢትዮጵያውያን በዘርፉ ኢንቨስት እንዲያደርጉ፣ በዲጂታል ዘዴዎች የፋይናንስ አገልግሎት የሚሰጡ ኩባንያዎች የፋይናንስ ተቋማት እንዲሆኑና ሙሉ በሙሉ ከወለድ ነፃ የሚሰጡ ባንኮች ኢንዱስትሪውን እንዲቀላቀሉ መደረጉን አስታውሰዋል፡፡

የዘርፉን አገልግሎት በዘመናዊ ዕውቀትና ቴክኖሎጂ ለመደገፍ፤ ከዓለም አቀፍ ገበያ ጋር ያለውን ትስስር ለማጠናከር፤ የዘርፉን ተወዳዳሪነት፣ ውጤታማነትና ቀልጣፋነት በማሳደግ በቂ የፋይናንስ አቅርቦት እንዲኖር እና የውጭ ምንዛሪ አቅርቦት እንዲያድግ ለማድረግ እንደሚጠቅም ጠቁመዋል፡፡

የሥራ ዕድል እንዲሰፋ እንዲሁም ቀጣይነት ያለውን



ተስፋዬ ቤልጂጌ (ዶ/ር)

የኢኮኖሚ ዕድገት ለማረጋገጥ እንዲቻል አዋጁን በአዲስ መልክ ማዘጋጀት አስፈላጊ ሆኖ መገኘቱንም አመልክተዋል፡፡

ረቂቅ አዋጁ ስለ ባንክ የሥራ ፈቃድ፣ የውጭ ዜጎች በባንክ ሥራ ስለሚሳተፉበት ሁኔታ፣ ስለአክሲዮኖችና የባለአክሲዮኖች ጉባኤ፣ ስለባንክ ሠራተኞችና ዳይሬክተሮች፣ የፋይናንስ ግዴታዎችና ገደቦችን የተመለከቱና ሌሎች የባንክ ዘርፉን የቀጣይ ዓመታት አሠራር የበለጠ ጤናማና የተረጋጋ እንዲሆን የሚያስችሉ ድንጋጌዎች መካተታቸውን አብራርተዋል፡፡

ከምክር ቤት አባላት ትኩረት ሊደረግባቸው ይገባል ያሏቸውን ጉዳዮች በተመለከተ አስተያየት ከሰጡ አባላት መካከል እሸቱ ተመስገን (ዶ/ር)፤ ባንኮች በእውቀት ላይ የተመሠረተ ሃብት ማፍራትን ትኩረት አድርገው እየሠሩ አይደለም፡፡ በጀትን መምራት ትተው ስጋት ላይ ይጨነቃሉ ብለዋል፡፡

የሀገር ውስጥ ባንኮች ከውጭ ከሚመጡ ባንኮች ጋር ተወዳዳሪ ለመሆን መሥራት እንዳለባቸው አስተያየት ተሰጥቷል፡፡

አዋጁን ስንመለከት፤ ዘመናዊ ቴክኖሎጂ የሚጠቀሙ፣ ሃብት ያላቸው፣ ክህሎትና ልምድ ያካበቱ የውጭ ባንኮች እንዲገቡ እያደረግን መሆኑን መገንዘብ ይገባል ያሉት ደግሞ አምባሳደር ዲና ሙፍቲ ናቸው፡፡

ይህንን ስናደርግ ደግሞ የሀገር ውስጥ ባንኮች ተወዳድረው የማሸነፍ አቅማቸው ምን ያህል ነው የሚለውን የሚመራለት ቋሚ ኮሚቴ ባግባቡ ማየት እንዳለበትም ነው የጠቆሙት፡፡

ሌሎች አስተያየት ሰጪዎችም ከውጭ የሚመጡት ተቋማት የውስጥ አቅምን እንዳይፈታተኑ ጠንካራ የቁጥጥር እና ክትትል ሥርዓት ሊዘረጋ ይገባል የሚል አስተያየት አቅርበዋል፡፡

በተጨማሪም የዲጂታል ከረንሲን በሚመለከት ዘመኑ ያመጣቸው እንደቢት ኮይን ያሉትን የዓለም አቀፍ ልምዶችን በመቀመር ለኅብረተሰቡ ጠቃሚ ከሆነ ሥርዓት ያለው አሠራር እንዲዘረጋም ማጭበርበር ከሆነም ባግባቡ ታይቶ እልባት እንዲሰጥ ቋሚ ኮሚቴው ባግባቡ ሊያየው ይገባል የሚሉና ሌሎችም ሀሳቦች ተነስተዋል፡፡

የመጀመሪያው ባንክ ከተመሠረተበት 1906 እ.ኤ.አ ጀምሮ በርካታ የባንክ ሥራ አዋጆች ወጥተው ሥራ ላይ መዋላቸውን ተስፋዬ (ዶ/ር) አስታውሰዋል፡፡

አሁን ሥራ ላይ ያሉ አዋጆች የባንክ ሥራ አዋጅ ቁጥር 592/2000 እና የባንክ ሥራ ማሻሻያ አዋጅ ቁጥር 1159/2011 ላለፉት 16 ዓመታት ሲሠራባቸው መቆየቱንም አንስተዋል፡፡

በተጀመረው ሀገራዊ የሪፎርም አጀንዳ ማዕቀፍም የባንክ ዘርፍ ለውጭ ኢንቨስተሮች ክፍት እንዲሆን ነሐሴ 08 ቀን 2014 ዓ.ም የሚኒስትሮች ምክር ቤት ውሳኔ ማስተላለፉን ተናግረዋል፡፡



# በከተማዋ አምስት ቢሊዮን ብር የሚገመት የበጎ ፍቃድ አገልግሎት ይሰጣል

**መስከረም ሰይፉ**

አዲስ አበባ፡- በከተማዋ በዘንድሮ ክረምት አምስት ቢሊዮን ብር የሚገመት የበጎ ፍቃድ አገልግሎት እንደሚሰጥ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የኅብረተሰብ ተሳትፎና በጎ ፍቃድ ማስተባበሪያ ኮሚሽን አስታወቀ፡፡

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የኅብረተሰብ ተሳትፎና የበጎ ፍቃድ ማስተባበሪያ ኮሚሽን የወጣቶች የክረምት በጎ ፍቃድ አገልግሎት ማስጀመሪያ የንቅናቄ መድረክ በትናንትናው እለት አካሂዷል፡፡

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የኅብረተሰብ ተሳትፎና በጎ ፍቃድ ማስተባበሪያ ኮሚሽን የበጎ ፍቃድ አገልግሎት ቡድን መሪ ቢኒያም ጊቻ እንደገለጹት፤ ባለፉት ዓመታት በበጎ ፍቃድ አገልግሎቶች በከተማዋ በርካታ የኅብረተሰብ ክፍሎችን ተጠቃሚ ማድረግ ተችሏል፡፡

አቶ ቢኒያም በከተማዋ የበጎ ፍቃድ አገልግሎት ልምድ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተሻሻለ መምጣቱን የገለጹ ሲሆን በዘንድሮው ክረምትም 15 የበጎ ፍቃድ መርሐግብሮች በመቅረጽ ወደ ሥራ ተገብቷል ብለዋል፡፡

በሰብዓዊ አገልግሎቶች፣ በማኅበራዊ አገልግሎቶች፣ ቤት በማደስና በመገንባት፣ በአረንጓዴ ዐሻራ፣ በደም ልገሳ እንዲሁም በሌሎች መርሐ ግብሮች ከሁለት ነጥብ ሁለት ሚሊዮን በላይ ወጣቶች በድግግሞሽ ይሳተፋሉ ተብሎ እንደሚጠበቅም ተናግረዋል፡፡

ይህም አንድ ነጥብ ሁለት ሚሊዮን የሚደርሱ የከተማዋ ነዋሪዎች ተጠቃሚ የሚያደርግ ሲሆን በመንግሥት ይሸፈን የነበረን 5 ቢሊዮን ብር የሚደርስ ወጪ ደግሞ እንደሚያድን ገልጸዋል፡፡

አቶ ቢኒያም በከተማዋ የበጎ ፍቃድ አገልግሎት ልምድ እየተሻሻለ በመምጣቱ የሚሰጡ አገልግሎቶችም እየተሻሻሉ መምጣታቸውንና ተደራሽ የሚያደርጉት የኅብረተሰብ ክፍልም እየጨመረ መምጣቱን ገልጸዋል፡፡

ሌላኛው በመርሐ ግብሩ ላይ የተገኙት የአዲስ አበባ ብልፅግና ፓርቲ ወጣቶች ሊግ ፕሬዚዳንት መለሰ አባተ በበኩላቸው የበጎ ፈቃድ አስተሳሰብ በወጣቱ ዘንድ እንዲጎለብት እና ባሕል እንዲሆን ወጣቶች ድርሻቸው መወጣት እንዳለባቸው ገልጸዋል፡፡

የበጎ ፈቃድ አገልግሎት በዜጎች መካከል አብሮነት እና አንድነት እንዲጎለብት የሚያደርግ መሆኑን የገለጹት ፕሬዚዳንቱ ወጣቶች በበጎ ፍቃድ አገልግሎቶች ላይ መሳተፍ እንደሚኖርባቸው አሳስበዋል፡፡

አቶ መለሰ በዘንድሮው የበጎ ፍቃድ አገልግሎት ወጣቶቹ በ15 ተግባራት ላይ እንደሚሠማሩ የተናገሩ ሲሆን የወሰን ተሻጋሪ የበጎ ፈቃድ አገልግሎት መካተቱንም አንስተዋል፡፡

# ቴክኒክና ሙያ ተቋማት በዓመት ከ3 ነጥብ 5 ሚሊዮን በላይ ሠልጣኞችን የመቀበል አቅም ፈጥረዋል

**ልጅዓለም ፍቅሬ**

አዲስ አበባ፡- ቴክኒክና ሙያ ተቋማት በመደበኛ እና በአጫጭር ሥልጠናዎች በዓመት ከ3 ነጥብ 5 ሚሊዮን በላይ ሠልጣኞችን የመቀበል አቅም መፍጠራቸው ተገለጸ፡፡

የቴክኒክና ሙያ ሥልጠና ዘርፍ ከፊላንድ መንግሥት ጋር በትብብር ሲሠራ የነበረው ፕሮጀክት ያስገኛቸው ውጤቶችና የወደፊት አቅጣጫዎች ላይ ትናንት ምክክር ተካሄዷል፡፡

የሥራና ክህሎት ሚኒስትር ዴኤታ ተሻለ በሬቻ (ዶ/ር) በምክክሩ ወቅት እንደገለጹት፤ በኢትዮጵያ የቴክኒክና ሙያ ሥልጠና ተቋማት በመደበኛ ከ500 ሺህ በላይ ዜጎችና በአጫጭር ሥልጠናዎች ከሦስት ሚሊዮን በላይ ዜጎች በየዓመቱ ተቀብሎ የማሠልጠን አቅም ገንብቷል፡፡

መርሐግብሩን ለማስኬድ ከአንድ ሺህ 500 በላይ የቴክኒክና ሙያ ተቋማት ውስጥ ከ30 ሺህ በላይ አሠልጣኞች መኖራቸውን ጠቅሰው፤ ዘርፉ ከሥራ ዕድል ፈጠራ ረገድም ድርሻው የጎላ ነው ብለዋል፡፡

ብቁ እና ለዘርፉ የሚመጥኑ መምህራንን ማሠልጠን ከተቻለ ዘርፉን በአጭር ጊዜ መቀየር ይቻላል በሚል እሳቤ ላለፉት አራት ዓመታት ከፊላንድ መንግሥት ጋር ሲሠራ መቆየቱን ጠቅሰው፤ ዋናውን ኢንስቲትዩት ጨምሮ በስድስት ክልሎች ላይ 15 ሳተላይት ያላቸው ተቋማት መኖራቸውን አስረድተዋል፡፡

በፕሮጀክቱ የቴክኒክና ሙያ ተደራሽነትና ጥራትን ለማሳደግ አሠልጣኞች የኤሌክትሮኒክስና የገፅ ለገፅ ማስተማሪያ ዘዴዎችን አዋሕደው እንዲያሠለጥኑ የአሠልጣኞች ሥልጠና ሲሰጥ እንደነበር አስታውቀዋል፡፡

በተጨማሪም ባለፉት ዓመታት የቴክኒክና ሙያ ሥልጠና ዘርፉን ለማዘመን በመንግሥት በጀት ተይዞ እንዲሁም ከተለያዩ ባለድርሻ አካላት ሲሠራ ነበር ያሉት ተሻለ (ዶ/ር)፤ በዚህም በይዘትም ሆነ በብዛት ዘርፉ ከጊዜ ወደ ጊዜ መሻሻል እያሳየ መሆኑን ተናግረዋል፡፡

ተሻለ (ዶ/ር) አክለውም፤ ይህንን ሥርዓት ማዘመንና ጥራቱን ማስጠበቅ ሀገሪቱን ይበልጥ ተጠቃሚ የሚያደርግ ነው ያሉ ሲሆን አሁን ላይ በዘርፉ ቀድሞ የነበረውን የማስተማሪያ ሥነ-ዘዴ ከዘመናዊው ጋር በማጣመር ውጤት እያስገኘ እንደሚገኝ ጠቁመዋል፡፡


ተሻለ በሬቻ(ዶ/ር)

በኤሌክትሮኒክስ መንገድ ያለው የማስተማሪያ ዘዴ ቀድሞ ከነበረው የገጽ ለገጽ ማስተማሪያ ዘዴ ጋር በማቀናጀት በዋናው ጊቢ ተጀምሮ በክልል ተቋማት ላይ መተግበር ተጀምሯል ያሉ ሲሆን፤ በሚቀጥሉት ሁለት ዓመታት ውስጥ በሁሉም ቴክኒክና ሙያ ሥልጠና ተቋማት ላይ ለማስፋፋት እየተሠራ መሆኑንም ነው ተሻለ (ዶ/ር) ያብራሩት፡፡

ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ የተለያዩ የመሠረተ ልማት ምቹ ሁኔታዎች ለመፍጠር የትኩረት አቅጣጫዎችን ለይቶ እየሠራ እንደሚገኝም ነው የተናገሩት፡፡

የቴክኒክና ሙያ ሥልጠና ኢንስቲትዩት ምክትል ዋና ዳይሬክተር ሃፍቶም ገብረእግዚአብሔር በበኩላቸው፤ በፕሮጀክቱ የአሠልጣኞች ሥልጠና ተሰጥቶ ውጤታማ መሆን ተችሏል ብለዋል፡፡

አቶ ሃፍቶም አክለውም፤ ፕሮጀክቱ ከባለፉት አራት ዓመታት ጀምሮ በፊላንድ መንግሥት፣ በሥራና ክህሎት ሚኒስቴር እንዲሁም በፌደራል ቴክኒክና ሙያ ሥልጠና ኢንስቲትዩት በትብብር ሲተገበር ነበር ያሉ ሲሆን ዓላማውም የሥልጠና ጥራትን ለማረጋገጥ ነው ብለዋል፡፡

በተጨማሪም የሰው ኃይል ልማትና የተለያዩ መሠረተ ልማት ማሟላት ላይ ይበልጥ ትኩረት ማድረጉን ገልጸዋል፡፡

# ርዕሰ አንቀፅ

## ረቂቅ ሕጉ ልማታችን በጠንካራ የሕግ እና የሞራል መሠረት ላይ እንዲዋቀር ይረዳል!

እንደ ሀገር የጀመርነው ድህነትን ታሪክ የማድረግ ትግል በሁለንተናዊ መልኩ በጠንካራ የሕግ እና የሞራል መሠረት ላይ ካልተዋቀረ፣ ውጤቱ የተጠበቀውን ያህል መላው ሕዝባችንንን ፍትሐዊ ተጠቃሚ እንዲሁም እንደ ሕዝብ ተስፋ የምናደርጋቸውን ነገዎች ተጨባጭ ያደርጋቸዋል ተብሎ አይታሰብም።

በተለይ በሕገወጥ መንገድ የተገኘን ገንዘብ ሕጋዊ አስመስሎ ማቅረብ (መኒ ላውንደሪንግ)፣ ሙስና፣ ኮንትሮባንድ፣ የታክስ ስወራ፣ ሕገወጥ የሰዎች ዝውውር፣ ጥቁር ገበያ ...ወዘተ አሁን ላይ ተገቢውን ትኩረት ሰጥተን በአግባቡ መከላከል ካልቻልን ድህነትን ለማሸነፍ የጀመርነው ትግል ትርጉም ሊያጣ ይችላል ።

በአቋራጭ ከፍተኛ ሀብት ለማፍራት የሚፈፀሙት እነዚህ ወንጀሎች፣ በሀገር ኢኮኖሚ ላይ የከፋ አደጋ ከማስከተላቸውም በላይ የፖለቲካ አለመረጋጋት በመፍጠር፣ መንግሥታዊ ሥርዓትን በመፈታተን የሕግ የበላይነትን ስጋት ውስጥ በመክተት የዴሞክራሲ ሥርዓት ግንባታን ሊያቀጭጩ የሚችሉ ናቸው።

በተለይም እንደኛ ባሉ የተለያዩ ማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ፍላጎቶች ባሉባቸው ሀገራት፣ እነዚህ ወንጀሎችና በወንጀሎቹ የሚገኙ ሀብቶች የፍላጎት ተቃርኖዎችን በመፍጠርና በማስፋት እና የግጭትና የሁከት ምንጭ በመሆን ዘላቂ ሠላምና መረጋጋት እንዳይኖር ሀገራዊ ፈተና ሊሆኑ እንደሚችሉም ይታመናል።

በሕገወጥ መንገድ የተገኘ ገንዘብና ንብረት የሽብር ወንጀል ማስፈጸሚያ የመሆን ዕድሉ ከፍተኛ ነው። እንደ የሽብር ቡድኑ አደረጃጀት፣ ዓላማና ሁኔታ ይለያይ እንጂ አብዛኞቹ የሽብር ወንጀሎች የሚፈጸሙት ሕጋዊ ባልሆነ መንገድ የተገኘ ገንዘብና ንብረትን በመጠቀም ነው። ይህም ለዓለም አቀፍ ሠላም እና ደኅንነት ስጋት እየሆነ ከመጣ ውሎ አድሯል።

በወንጀል ድርጊት የተገኘ ገንዘብ ወይም ንብረት ሕጋዊ አስመስሎ ማቅረብ እና ሽብርተኝነትን በገንዘብ የመርዳት ወንጀል የኢኮኖሚ ደኅንነት ስጋት ብቻ ሳይሆን የአጠቃላይ የፋይናንስ ሥርዓቱ የተረጋጋ፣ ግልጸኝነት ያለውና ጤናማ እንዳይሆን በማድረግ የፋይናንስ ሥርዓቱን የሚያናጋ ወንጀል ነው፡፡

መንግሥት የዋጋ ንረትን በቀላሉ እንዳይቆጣጠርና በኢኮኖሚ ውስጥ ምን ያህል ገንዘብ እየተዘዋወረ እንደሚገኝ የተጣራ መረጃ እንዳይኖረው በማድረግ፣ የገንዘብ አቅርቦት እና ዝውውርን የሚቆጣጠርበትን አቅም ይፈታተናል፤ መሰብሰብ ያለበትን ግብር እንዳይሰበስብ ያደርገዋል፡፡ በዚህም አጠቃላይ በሆነው የልማት እንቅስቃሴ ላይ ሊያሳድር የሚችለው አሉታዊ ተፅዕኖ የከፋ ነው።

ከዚህም ባለፈ የሀገር ውስጥ የፋይናንስ ተቋማት መልካም ስም እንዳይኖራቸው በማድረግ፣ በዓለም አቀፍ ደረጃ ከሌሎች የፋይናንስ ተቋማት ጋር በተዓማኒነት እንዳይሠሩ ያደርጋል፡፡ የሀገሪቱን የፋይናንስ ሥርዓት በማዛባት የኢኮኖሚና የፖለቲካ አለመረጋጋትን በመፍጠር ለሀገራዊ ልማት እንቅፋት ይሆናል፡፡

ሀገራት ይህንን በሁለንተናዊ መንገድ አደጋ የሆነ ወንጀልን ለመከላከል የተለያዩ ሕጎችን በማውጣት ተፈጻሚ ያደርጋሉ። ዓለም አቀፍ የትብብር ማዕቀፎችን በመተግበርም በጋራ ይንቀሳቀሳሉ። ሀገራችንም የወንጀሎቹን አደገኝነት በማጤን የሽብር ወንጀሎችንና ተዛማጅ የፋይናንስ ወንጀሎችን መከላከል የሚያስችል ሕግ፣ በአዋጅ ቁጥር 780/2005 ተግባራዊ አድርጋ እየተንቀሳቀሰች ነው፡፡

ሀገራችን አሁን ላይ ካለችበት ተጨባጭ እውነታ እና ዓለም አቀፍ የትብብር ማዕቀፎችን ታሳቢ ያደረገ፣ በወንጀል ተግባር የተገኘ ገንዘብን ወይም ንብረትን ሕጋዊ አስመስሎ ማቅረብ እና ሽብርተኝነትን በገንዘብ የመርዳትን ወንጀልን ለመከላከል እና ለመቆጣጠር ሰፋፊ ሥራዎችን ውጤታማ በሆነ መንገድ መሥራት ይጠበቅባታል፡፡ አሠራሩን መደገፍ የሚያስችሉ ተጨማሪ የሕግ ድንጋጌዎችንም ማውጣት ይኖርባታል።

ከዚህ በፊት በሥራ ላይ የነበረው አዋጅ ወንጀሎችን ለመከላከል እና ለመቆጣጠር የሚያስችሉ በርካታ ጉዳዮችን ይዞ ሲሠራበት የቆየ ቢሆንም፣ በሚፈለገው ደረጃ ሥራውን ውጤታማ አድርጎ ለመምራት የሚያስችሉ ማሻሻያዎችን ማድረግ አስፈልጎታል፡፡ ይህንን ታሳቢ በማድረግም በቅርቡ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ባካሄደው 32ኛ መደበኛ ስብሰባ በወንጀል የተገኘን ንብረት ሕጋዊ ማስመሰል እና ሽብርተኝነትን በገንዘብ መርዳት መንጀልን ለመከላከል እና ለመቆጣጠር በተዘጋጀው ረቂቅ አዋጅ ላይ ተወያይቶ ረቂቅ አዋጁን ለተወካዮች ምክር ቤት መርቷል ።

ረቂቅ አዋጁ ዓለማቀፍ ስጋት የሆነውን ወንጀል በተሻለ መንገድ ለመከላከል የሚያስችል፣ እንደ ሀገር የጀመርነው ድህነትን ታሪክ የማድረግ ትግል በሁለንተናዊ መልኩ በጠንካራ የሕግ እና የሞራል መሠረት ላይ እንዲዋቀር ስትራቴጂክ አቅም በመሆን፣ ሕዝባችን ተስፋ ከሚያደርገው ልማት ፍትሐዊ ተጠቃሚ እንዲሆን የሚያስችል የሕግ አግባብ ነው።

በተለይ ከሀገራዊ ልማት ፍትሐዊ ተጠቃሚ ለመሆን ባላቸው አቅም የሚንቀሳቀሱ ዜጎችን በተሻለ መልኩ የሚያበረታታ፣ ለልማት የሚሆን የተሻለ ሀገራዊ ምኅዳር መፍጠር የሚያስችል፣ ለሀገራዊ ሠላም እና መረጋጋት ተጨማሪ ጉልበት የሚሆን ነው። ሀገር እና ሕዝብን በሚጎዱ የተለያዩ ወንጀሎች እየተሳተፉ ያሉ ዜጎች ከድርጊታቸው እንዲቆጠቡና ወደ ሕጋዊ ሥርዓት እንዲመጡ ተገቢውን ማስጠንቀቂያ ማስተላለፍ የሚያስችልም ነው!

**አዲስ ዘመን**
ኢፕድ
ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22
ኢሜል ፡- epa@press.et

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4200
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የዜና ማዕከል ዋና አዘጋጅ**
ወርቁ ማሩ
Email:- workumaru2@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- እስማኤል አረቦ
- ቦጋለ አበበ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** ፡- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70

## በአማራ ክልል በሠላም ጉዳይ የተካሄደው ኮንፈረንስ ያወጣው ባለ 10 ነጥብ የአቋም መግለጫ

ኢትዮጵያ ሀገራችን ረጅም ታሪክ ያላት ሀገር፣ የበርካታ ባሕል እና ቋንቋ ባለቤት፣ የነፃነትና የአንድነት ተምሳሌት፣ በገፀ ምድርና በከርሰ ምድር ሀብት የበለፀገች፣ የብዙ ብሔር ብሔረሰቦች መገኛና ድንቅ የባሕል እሴቶች ባለቤት መሆኗ እንደተጠበቀ ሆኖ በሌላ በኩል ደግሞ ሀገራችን በተለያዩ ጊዜያቶች በርካታ የተፈጥሮና ሰው ሠራሽ ችግሮች ሲፈትኗት ቆይተዋል::

ይሁን እንጂ እነዚህን በየጊዜው የገጠሟትን ፈተናዎች በሕዝቦቿ ትብብርና አንድነት በከፍተኛ የድል አድራጊነት መንፈስ በመታገል እየተሻገረች እዚህ የደረሰች ሃገር መሆኗ ግልፅ ነው::

የአማራ ሕዝብ፣ ከክልሉ ውጭ የሚኖሩ የክልሉ ተወላጆችን ጨምሮ ይህን የኢትዮጵያዊነት እሴት የተላበሱ ናቸው:: በሀገረ መንግሥት ግንባታ ሂደትም ከሌሎች ወንድምና እህት ኢትዮጵያውያን ጋር በመሆን የራሱን አስተዋፅዖ ያበረከተ እና በርካታ ዋጋ የከፈለ ሕዝብ ነው::

ስለሆነም የሕዝቦችን የአብሮነትና የአንድነት ገመድ ለመበጣጠስ የተለያዩ ግጭቶች በተለያዩ የሀገራችን አካባቢዎች እያጋጠሙ ቆይተዋል:: በአማራ ክልልም ገጥሞን የቆየው ችግር ለበርካታ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ማኅበራዊ ምስቅልቅሎች ዳርጎን ቆይቷል::

ሆኖም ግን በአሁኑ ወቅት በሁሉም የክልሉ አካባቢዎች አንፃራዊ ሠላምና መረጋጋት የተፈጠረ ቢሆንም ወደ ቀድሞ ሠላሙና ወደ ዘላቂ ልማት ለመመለስ እንዲሁም ሕዝቡ የተረጋጋ ሕይወት እንዲመራ በማድረግ ረገድ በርካታ ቀሪ ሥራዎች እንደሚያስፈልጉን ይታወቃል::

በመሆኑም ክልሉ ሠላማዊና የተረጋጋ፣ እንደቀድሞ ታሪኩ ለሀገር ሁለንተናዊ እድገትና አንድነት የድርሻውን እንድወጣ ለማስቻል ይህን የሠላም ኮንፍረንስ ያደረግን ሲሆን በውይይታችንም የተገኙ ግብዓቶች ሕዝቡ በሠላም ለመኖር ያለውን መሻት በጉልህ የተረዳንበት እንዲሁም አሉን የምንላቸውን ጥያቄዎች በግልፅ ያቀረብንበት ነው::

ጀግናው የሀገር መከላከያ ሠራዊታችን የክልሉን ሠላም ወደነበረበት ለመመለስ ሲከፍል ለቆየው መስዋዕትነት በአማራ ሕዝብ ስም ታላቅ ክብር እየሰጠን የክልሉ ተወላጅ የሆኑ ጄኔራል መኮነኖች ለነበራቸው የመሪነት ሚና ከፍተኛ ምስጋና እያቀረብን ለመላው የሀገር መከታ እና አለኝታ ለሆነው የሀገር መከላከያ ሠራዊታችን ያለንን አክብሮትና አድናቆት ለመግለፅ እንወዳለን:: ከሰኔ 17 ቀን 2016 ዓ.ም እስከ ሰኔ 18 ቀን 2016 ዓ.ም ለተከታታይ ሁለት ቀናት በባሕር ዳር ከተማ ያደረግነውን ክልላዊ የሠላም ኮንፍረንስ አስመልክቶ ባለ 10 ነጥብ የአቋም መግለጫ በማውጣት የጋራ ማድረጋችንን እናረጋግጣለን::

1. በሠላምና በፀጥታ፣ በፖለቲካ፣ በማኅበራዊ፣ በመልካም አስተዳደር፣ በማንነትና በራስ አስተዳደር ጉዳይ እንዲሁም ሕገመንግሥትን ስለማሻሻል አስመልክቶ ያነሳናቸውን ጥያቄዎች በየፈርጃቸው ለፌደራል መንግሥትና ለክልሉ መንግሥት እንዲቀርብልን ስምምነት ላይ ደርሰናል:: ሁሉም ጥያቄዎች በአንድ ጊዜ እንደማይመለሱ ስለምናምን መንግሥት የሕዝቡን ጥያቄ ለመፍታት ያለውን ቁርጠኝነት እንዲሁም በፍጥነት መመለስ ያለባቸውን ለመፍታት የሚኖረውን ዝግጁነት በጋራ እያየን እንዲሁም በሠላማዊ መንገድ እየተወያየን ጥያቄዎቹ እንዲፈቱልን መጠየቃችንን እንቀጥላለን::
2. በክልሉ ውስጥ በርካታ የልማት ጥያቄዎች መኖራቸው ይታወቃል:: እነዚህ የልማት ጥያቄዎች ያለ ሠላም ሊታሰቡ ስለማይችሉ ቅድሚያ በክልላችን ውስጥ ማንኛውም ጥያቄ በሠላማዊ መንገድ እንዲፈታ የበኩላችንን ድርሻ ለመወጣት በውይይታችን የተስማማን መሆኑን እናሳውቃለን::
3. ለሚዲያ ተቋማትና ሙያተኞች እንዲሁም ለማኅበረሰብ አንቂዎች የክልሉ ሕዝብ በርካታ ሁለንተናዊ ችግሮች ተጋርጠውበት ቆይተዋል:: በርካታ ምስቅልቅሎችም ደርሰውበታል:: ስለሆነም ይህን ዘርፈ ብዙ ችግር ተገንዝባችሁ ሕዝቡን ወደ ሠላም የሚመልስና የክልሉ ሕዝብ ከሌሎች ወንድምና እህት ሕዝቦች ጋር በጋራ የገነባናት ሀገር ተከባብሮና በነፃነት ተዘዋውሮ እንዲሠራባት ለማስቻል የሚዲያውን አየር በሠላም እንድትሞሉልን በታላቅ አክብሮት እንጠይቃለን::
4. የመንግሥት ባለሥልጣናት፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች፣ ምሑራን፣ የኪነጥበብ ባለሙያዎች፣ በውጭ የምትኖሩ ኢትዮጵያውያን ዲያስፖራዎች፣ እንዲሁም መላ ኢትዮጵያውያን በሙሉ፤ በክልላችን ከተፈጠረው ቀውስ በመውጣት አስተማማኝና ዘላቂ ሠላም ለመገንባት በምናደርገው ጥረት ለክልላችን ሠላም ስትሉ ሁሉንም አይነት የሠላም ድጋፍ እንድታደርጉ፣ ከመገፋፋትና ከመጠላለፍ በመውጣት ለክልሉ ሕዝብ ሠላማዊ እንቅስቃሴ በጋራ እንድትቆሙ እንጠይቃችኋለን::
5. ታጥቃችሁ ጫካ የገባችሁ ወንድሞቻችን እና እህቶቻችን እንታገልለታለን የምትሉት ሕዝብ ያለበትን ችግርና የክልሉ ሕዝብ ሕልውና እንዴት እንደተፈተነ በግልፅ ታውቃላችሁ:: ስለሆነም ጥያቄያችሁን በሠላማዊ መንገድ በውይይትና በድርድር እንድታቀርቡ እንዲሁም የወገናችሁን ስቃይ ለመቀነስ እንዲቻል መገዳደል ይብቃን ብላችሁ ወደ ወገኖቻችሁ እንድትቀላቀሉ የሠላም ኮንፈረንሳችን ተሳታፊ በሙሉ ወገናዊ ጥሪ እያስተላለፍን መንግሥትም ሆደ ሰፊ በመሆን እነዚህ ወንድሞቻችን እና እህቶቻችን ጋር በመወያየት እና በመደራደር ለሕዝባችን ሠላም ሲባል በይቅርታና በክብር እንዲቀበላቸው ጥሪያችንን እናቀርባለን::
6. የክልል መንግሥታት፣ እንዲሁም የዞንና የከተማ አስተዳደሮች በምታገለግሉት ሕዝብ ውስጥ የክልላችን ተወላጆች እናንተን የመንግሥት አስተዳደሮችን እና አብሮ ለዘመናት የኖረውን ወገኖቹን አምኖ እየኖረ መሆኑን በመገንዘብ ሕዝባችን ባይተዋርነትና ብቸኝነት እንዳይሰማው፣ ጥቃት እንዳይደርስበት፤ በክልላችን ለሚኖረው ሕዝብ የጥያቄ ምንጭ እንዳይሆን እንዲሁም የሀገረ መንግሥት ግንባታ ሂደታችንን በአስተማማኝ ሁኔታ መሠረት እንዲኖረው በጋራ እንዲንቀሳቀስ በሠላም ኮንፈረንሳችን ጥሪያችንን እያስተላለፍን በአማራ ክልል ማንኛውም ዜጋ በብሔሩ ወይም በእምነቱ ወይም በሌሎች ምክንያቶች የማይገለልበት ክልል እንዲሆን እኛም እንደቀደመው ሁሉ እንደምንሠራ ቃል እንገባለን::
7. በክልላችን ውስጥ የምትንቀሳቀሱ የፌዴራልና የክልል የፀጥታ ኃይሎች በማንም ይጠንሰስ ማንም ይጀምረው በክልላችን ውስጥ እየሆነ ያለው ነገር ወንድም ወንድሙን እየገደለና ሕዝባችን የከፋ ችግር እየደረሰበት በመሆኑ ነው:: በመሆኑም የጀመርነው የሠላም ጥረት እንዲሳካ የበኩላችሁን ጥረት እንድታደርጉና ከጫካ የሚመጡ ወንድሞቻችሁ ወንድም መሆናቸውን አውቃችሁ በፍፁም ሙያዊ ዲሲፕሊንና ኢትዮጵያዊ ጨዋነት አቀባበል ታደርጉላቸው ዘንድ የከበረ ጥሪያችንን እናስተላልፋለን::
8. በጫካ የሚገኙ ወንድሞቻችን በሠላማዊ መንገድ በውይይትና በድርድር ወደ ማኅበረሰቡ ከተቀላቀሉ በኋላ የሀገራችንን ሁለንተናዊ ችግር በዘላቂነት ይፈታል ተብሎ በታሰበውና ተስፋ በተጣለበት የሀገራዊ የምክክር ኮሚሽኑ ውስጥ በንቃት እንዲሳተፉ በማድረግ ያላቸውን ጥያቄ በሠላማዊ መንገድ አቅርበው የሕዝቡን ችግር በትክክለኛው መንገድ እንዲፈታ በማድረግ ታሪካዊ ኃላፊነታቸውን እንዲወጡ ሁሉም አካል የበኩሉን እንዲወጣ ጥሪያችንን እናስተላልፋለን::
9. በክልሉ ውስጥ ከተፈጠረው ችግር ጋር ተያይዞ ተጠርጥረው በሕግ ቁጥጥር ስር የዋሉ ዜጎች ማለትም ፖለቲከኞች፣ ጋዜጠኞች፣ ምሑራን፣ እንዲሁም ተፅዕኖ ፈጣሪ ዜጎች በክልሉ ውስጥ ለምንገነባው ዘላቂ ሠላም የበኩላቸውን እንዲወጡ ለማስቻል መንግሥት በይቅርታና በምሕረት ነፃ እንዲወጡ በማድረግ ሚናቸውንና ድርሻቸውን እንዲወጡ እንጠይቃለን::
10. በሰሜኑ የሀገራችን ክፍል የተደረገውን ደም አፋሳሽ ጦርነት በሠላማዊ መንገድ ለመቋጨት መንግሥት በሆደ ሰፊነት የፕሪቶሪያውን የሰላም ስምምነት ማድረጉ ይታወሳል:: የፕሪቶሪያውን ስምምነት ተግባራዊ ለማድረግ የፌደራል መንግሥትና የክልላችን መንግሥት ከፍተኛ ጥረት እያደረጉ በሚገኙበት በዚህ ወቅት በሕወሓት በኩል ገና ከጅምሩ ጀምሮ ስምምነቱን እንደ ጊዜ መግዣ በመጠቀም የማንነት እና የራስ አስተዳደር ጥያቄ ባለባቸው አካባቢዎች ወረራ በመፈፀም ላይ ይገኛል:: በመሆኑም መንግሥት የፕሪቶሪያውን ስምምነት ሙሉ በሙሉ ተግባራዊና ተፈፃሚ እንዲሆን በማድረግ ወራሪ ኃይሎች ከወረሩበት ቦታ በፍጥነት እንዲወጡ እንዲሁም ጥያቄዎች በሠላማዊና በሕጋዊ መንገድ እልባት እንዲሰጣቸው ስንል የሠላም ኮንፈረንሳችን ይጠይቃል::

**ሠላም ለኢትዮጵያ፣ ሠላም ለክልላችን**
**ሰኔ 18/2016 ዓ.ም**
**ባሕር ዳር**

# ነፃ ሃሳብ



በቁምላቸው አበበ ይማም (ሞሼ ዳያን)
fenote1971@gmail.com

ቁምላቸው አበበ በአማራ ባህል፣ ቱሪዝምና ማስታወቂያ ቢሮ፤ በኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት፤ በደቡብ መገናኛ ብዙኀን፤ በጋዜጠኝነትና በታሪክ ባለሙያነት ያገለገሉ ሲሆን፤ የደቡብ ኤፍ ኤምን ከባልደረቦቻቸው ጋር በመሆንም አቋቁመዋል።በፌዴራል ውሃ ስራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅትና በአለ በጅምላ በኮሙዩኒኬሽን ዳይሬክተርነት አገልግለዋል። ከአአዩ በቋንቋና ታሪክ የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን የሰሩ ሲሆን፤ በዚሁ ዩኒቨርሲቲ በጋዜጠኝነትና ኮሙዩኒኬሽን ሁለተኛ ዲግሪያቸውን በማጠናቀቅ ላይ እያሉ ባጋጠማቸው ድንገተኛ ህመም ተስተጓጉሏል። ጥልቅ ሀሳብ ያዘሉ ወቅታዊ ጉዳዮች ላይ የሚያተኩሩ ፁሑፎችን በማህበራዊ ሚዲያና በተለያዩ ጋዜጦች በማውጣት ይታወቃሉ።

## የኑሮ ውድነቱን ለማረጋጋት

መንግሥት የዋጋ ግሽበቱንና እሱን ተከትሎ የተከሰተውን የኑሮ ውድነት ለማረጋጋት የገንዘብና የፊስካል ፖሊሲውን በማስተካከል፤ ነዳጅንና ማዳበሪያን በመደጎም፣ የምግብ ዘይትና መሠረታዊ የምግብ ሸቀጦች በፍራንኮ ቫሉታ እንዲገቡ በማመቻቸት፣ አምራቹንና ሸማቹን በቀጥታ ለማገናኘት የገበያ ማዕከልና የሽያጭ ቦታ በመስጠት፤ ደላላውን ሙሉ በሙሉ ባይሆን ከግብይት ሥርዓቱ በማስወጣት የተሻለ አፈጻጸም ሒደት ላይ ነው።

የቤት ኪራይ አስተዳደርና ቁጥጥር አዋጅ በማውጣት፣ የጅምላና የችርቻሮ ንግዱን ለውጭ ዜጎች በመክፈት፤ ለሸማች ሕብረት ማህበራት ተዘዋዋሪ ፈንድ በመፍቀድ አቅማቸውን በማጎልበት እያደረገ ካለው ጥረት ጎን ለጎን ፍላጎቱንና አቅርቦቱን ለማቀራረብ የበጋ፣ የኩታ ገጠምና የሜካናዝድ ግብርናን በማስፋፋት፤ አረንጓዴ ዐሻራን በመተግበር፤ ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ ጥረት እያደረገ ነው።

ይህም ሆኖ ፤ የግብይት ሥርዓቱን ከማዘመንና እሴት ከማይጨምሩ ተዋናዮች ነጻ ከማድረግ፤ ሕገ ወጥ ኬላዎችን ከማስነሳት እና ጊዜያቸውን ያልጠበቁ የታሪፍ ማሻሻያዎች እንዲቆዩ ከማድረግ፤ ብልሹ አሠራሮችንና ሙስናን ከመከላከልና ከመቀነስ፤ ግሽበቱን ታሳቢ ያደረገ የደመወዝ ማሻሻያ ከማድረግ፤ ከሁሉም በላይ በሀገሪቱ ሰላምንና መረጋጋትን ከማስፈን አንጻር የሚስተዋሉ ክፍተቶች ከላይ የተዘረዘሩና ሌሎች ጥረቶቹን ውሃ ቅዳ ውሃ መልስ እያደረጉት ይገኛሉ። ሁኔታው መንግሥትንም አመድ አፋሽ እያደረገውም ይገኛል።

የዓለም የንግድ ድርጅት አባል ለመሆን እየተደራደርን ባለበት፤ የአፍሪካ ነጻ ንግድ ስምምነትን ወደ ሥራ ለማስገባት እየጣርን ባለበት፤ ባንኩን፣ ንግዱን፣ ቴሌኮሙን እየከፋፈትን ባለበት፤ ለዛውም በ21ኛው ክፍለ ዘመን / በ2016 ዓ.ም በየ 10 ኪ/ሜትሩ ስለ ተዘረጉ የገመድ ሕገ ወጥ ኬላዎች መስማት ያሳፍራል። ሌላውን እናቆየውና በሸቀጦችና ምርቶች ዝውውር ወይም ሎጂስቲክ ላይ የሚፈጥሩትን ተጽዕኖ እንመልከት።

ምርት ወይም ሸቀጥ የጫኑ ተሽከርካሪዎች በየኬላው እንዲቆሙ ሲደረግ ቢያንስ በሌላ የውጭ ምንዛሬ የተሸመተ ነዳጅ ይባክናል። በሚፈለጉበት ሰዓት እንዳይደርሱ ስለሚያደርጉ የመጓጓዣ ዋጋቸው ይጨምራል። ይህ አልበቃ ብሎ በየኬላው ሲቀረጡ ሌላ ተጨማሪ ወጭ ስለሚያስወጣቸው በእነዚህ መስመሮች ለማጓጓዝ ፈቃደኛ አይሆኑም። ግድ ሆኖባቸው ቢሄዱ እንኳ በዚህ መስመር የሚባክንባቸውን ጊዜ፣ ነዳጅ፣ እንግልትና ለቀረጥ የሚያወጡትን ወጪ አስልተው ስለሚጭኑ የጭነት ዋጋ በእጅጉ ያሻቅባል።

አምራቹ ምርቱን ለማስጫን ከፍተኛ ዋጋ ስለሚጠየቅ በርካሽ ለመሸጥ ይገደዳል። ነጋዴውም በበኩሉ በውድ ስለሚረከብ ሸማቹ ላይ ዋጋ ይቆልላል። ሸማቹ ለባሰ የኑሮ ውድነት ይዳረጋል። በዚህ የተነሳ የባሰ ኑሮውንም መንግሥትንም ያማርራል። ይሄን ምሬት ይዞ ደግሞ ጥሩ አገልጋይ ሊሆን አይችልም። መንግሥት ዋጋን ለማረጋጋት የሚያደርገው ጥረትም እንዲህ ባሉ ሕገ ወጥ ተግባራት ይጨናገፋሉ።

ይህንን አሁን ላይ የሚስተዋል ችግር ለመሻገር የጉምሩክ ኮሚሽን ከሚቆጣጠራቸው ኬላዎች ውጪ ያሉ ሕገ ወጥ ኬላዎች ነገ ዛሬ ሳይሉ ሊነሱ ይገባል። ምርቶችና ሸቀጦች በነጻነት መዘዋወር ካልቻሉ ዋጋን ለማረጋጋት የሚደረጉ ጥረቶች ውጤታማ ሊሆኑ አይችሉም።

ከዚህ ጎን ለጎን ሸማቹ፣ ሻጩም ሆነ መላ ሕዝቡ መንግሥት የኑሮ ውድነቱን ለማረጋጋት የሚያደርገውን ጥረት ሊያግዝ ይገባል። የቤት ኪራይ አስተዳደርና ቁጥጥር አዋጅ የታለመለትን ግብ እንዳይመታ በአንዳንድ ደላላዎች አከራዮችና ተከራዮች የኪራይ ዋጋን አጋኖ የመዋዋል ጥረት የመኖሪያ ቤት ኪራይ ዋጋን ይበልጥ እንዳያንረውና አዋጁን ከመንገድ እንዳያስቀረው ተሠግቷል። የዋጋ ግሽበቱንና የዜጎችን የመክፈል አቅም ያገናዘበ የመኖሪያ ቤት ኪራይ ታሪፍ በአስቸኳይ ሊወጣና አጠቃላይ የኑሮ ውድነቱን የማረጋጋት ሥራ በበለጠ ፖለቲካዊ ቁርጠኝነት ሊሠራ ይገባል።

> **አዋጁ ተግባራዊ ከመደረጉ በፊት የነበሩ የአከራይ ተከራይ ውሎችን የሚያስቀር አለመሆኑ የተገለጸ ሲሆን፣ አዋጁ ሲወጣ የነበረ ውል እስከ ቀጣዩ ሦስት ወራት ድረስ እንዲመዘገብ ይጠበቃል**

መንግሥት የሸማቹን ወገብ ያጎበጡ ሸክሞችን የሚያቀሉ ርምጃዎችን መውሰድ መጀመሩ ይበል የሚያሰኝ ነው። የችርቻሮ ንግድን ለውጭ ኩባንያዎች ለመክፈት መወሰኑ በችርቻሮ ገበያው ላይ ማርሽ ቀያሪ ነው። ሸማቹ ዋጋ አወዳድሮ፣ጥራት አማርጦ እንዲሸምት ከማስቻሉ ባሻገር አቅርቦቱን ፍጹም ያሻሽለዋል ተብሎ ይጠበቃል። በአቦሰጥ የሚመራውን የችርቻሮ ንግድም ያዘምነዋል ተብሎ ይጠበቃል።

እጥፍ ስንጥቅ ካላተረፈ የነገደ ለማይመስለው የሀገራችን ነጋዴም ትምህርት ይሆናል ተብሎ ይታመናል። ሌላው ሰሞኑን በሚኒስትሮች ምክር ቤት የጸደቀው ደንብ ዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ላይ የሚገኘውን የሕብረተሰብ ክፍል ከተጨማሪ እሴት ታክስ ነጻ የሚያደርግ ነው። ይህ በተለይ በመሠረታዊ የፍጆታ እቃዎች ላይ ተጥሎ የነበረውን የተጨማሪ እሴት ታክስ የሚያቀል ነው።

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አምራቹን ከሸማቹ በቀጥታ ያለ ደላላ ጣልቃ ገብነት ለማገናኘት የሚያስችሉ የመሸጫ መደብሮችን በመስጠቱና የገበያ ማዕከላትን ገንብቶ በማስረከቡ የአትክልትና ፍራፍሬ ዋጋ የተወሰነ ቅናሽ ሊያሳይ ችሏል። አሁንም ተመልሶ የማሻቀብ አዝማሚያ እያሳየ ስለሆነ ቁጥጥርና ክትትል ይፈልጋል።

ደላላ ከግብይት ሥርዓቱ ተወግዶ አምራችና ሸማች በቀጥታ ሲገናኝ እንዲሁ ሁለቱም ተጠቃሚ ስለሚሆኑ አጠናክሮ መቀጠል ያሻል። በእህልና ጥራጥሬም አምራቹን ከሸማቹ በቀጥታ መገናኘት ከተቻለ ዋጋውን ማረጋጋትና መቀነስ ይቻላል። የኢትዮጵያ ፖሊሲ ጥናት ኢንስቲትዩት ባካሄደው ጥናት ምርት ሸማቹ ጋ የሚደርሰው 58 በመቶ ተጨምሮበት ነው ይላል።

የሚገርመው ይህ ጭማሬ ከአምራቹ ሳይሆን ከደላላውና ከነጋዴው ኪስ ነው የሚገባው። የግብይት ሰንሰለቱ አምራቹንም ሆነ ሸማቹን ተጠቃሚ እያደረገ አይደለም። ለዚህ ነው የሕገ ወጥ ደላላና የስግብግብ ነጋዴ ሲሳይ ነው እየተባለ የሚተቸው። ለዚህ መንግሥት አሁንም ደላላውን ከግብይት ሰንሰለቱ የሚያስወጣ ሕግ ሥራ ላይ ሊያውል ይገባል።

በዚያ ሰሞን የግብይት ሰንሰለቱ ላይ እንቅፋት በመፍጠር የዋጋ ንረት እንዲባባስ ያደረጉ 790 ደላላዎች ላይ አስተዳደራዊ ርምጃ መወሰዱን፤ በእህልና ጥራጥሬ ፣ በአትክልትና ፍራፍሬና በቁም እንስሳት ግብይት ውስጥ የነበሩ ደላላዎችን ፈቃድ በመሰረዝ ከግብይት ሒደቱ እንዲወጡ መደረጉን፤ በቀጣይ የደላላን ጣልቃ ገብነት በዘላቂነት እልባት ለመስጠት የሚያስችል መመሪያ እየተዘጋጀ መሆኑን የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር ገልጾ ነበር።

እኛም ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱን መመሪያውን ከምን አደረስሽው ስንል እንጠይቃለን። የከተማና መሠረተ ልማት ሚኒስቴር አርቅቆ ለሚኒስትሮች ምክር ቤት አቅርቦ ከተሻሻለ በኋላ በኢፌዴሪ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ወደ አጸደቀው ከሰኔ አንድ ጀምሮ ሥራ እየዋለ ስላለው የመኖሪያ ቤት ኪራይ አስተዳደርና ቁጥጥር አዋጅ አንድምታና አፈጻጸም እንለፍ።

የአከራይ ተከራይ አዋጁ ደግሞ ጨዋታ ቀያሪና የተከራዩን ሸክም የሚያቀልና መብቱን የሚያስከብር ነው። የነጻ ገበያ ሃዋሪያና ደቀ መዝሙር በሆኑት እንግሊዝና አሜሪካ ሳይቀር ነጻ ገበያ ስድ አይለቀቅም። ፈር ሲለቅ መንግሥታት ጣልቃ በመግባት ፈር ያሲዙታል። በዩናይትድ ኪንግደም ለንደንን ጨምሮ በዩናይትድ ስቴትስ ግዛቶች፣ በአውሮፓ በርካታ ሀገራት፣ በላቲን አሜሪካ እንዲሁ በርካታ ሀገራት የአከራይ ተከራይ ሕግ አላቸው።

አከራይ ከመሬት ተነስቶ ዋጋ አይጨምርም፣ ተከራይ አያስለቅቅም። ከዚህ አልፈው የኪራይ ተመንና የዋጋ ጣራ አላቸው። በመንግሥት በተለምዶ የኪቤአድና የቀበሌ ቤቶች ኪራይ ዋጋ በተወሰነ ደረጃ የዋጋ ተመን ያላቸው ሲሆኑ፣ ዋጋቸውም ከግል ቤቶች ርካሽ ነው ማለት ይቻላል። በአንጻሩ የግለሰብ ቤቶች ኪራይ ግን ስድ የተለቀቀና ተከራዩን የሚያማርር ነው። በሰበብ አስባቡ ዋጋ በየጊዜው የሚጨመርበት፣ የተከራዩን መብት የማያከብር ነው።

አከራይ እንዳሻው ኪራይ የሚጨምርበት፣ ከቤት የሚያስለቅቅበት፣ ከሁሉም በላይ ደላላ ጣልቃ እየገባ ዋጋ የሚተምንበት ተከራዩን ያማረረ ነበር። ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ቀውስ እየጎነቆለ ያለ ቁልፍ ችግር ነበር ማለት ይቻላል። አሁን ግን ምንም እንኳ የዘገየ ቢሆን ይሄን አንገብጋቢ ችግር የሚቀርፍ አዋጅ ጸድቋል።

ከሰኔ አንድ ጀምሮ ተግባራዊ እየሆነ ቢሆንም በአዋጁ መሠረት የከተማ አስተዳደሩ የውል ምዝገባ ማካሄድ የጀመረ ሲሆን፣ ምዝገባው በአንድ ወር ውስጥ እንደሚጠናቀቅ ተመላክቷል:: ይሁንና ገና ከአሁኑ ቅሬታ እየተሰማበት ነው። በርካታ አከራዮች ለሚቀጥሉት ሁለት ዓመታት የኪራይ ዋጋ መጨመር አንችልም በማለት አሁን ከፍተኛ የኪራይ ዋጋ ጭማሪ እያደረጉ መሆናቸውን ቅሬታ አቅራቢዎች ይናገራሉ:: አፈጻጸሙን ከስር ከስር በመከታተል መፍትሔ ማስቀመጥ ያሻል የሚባለው ለዚህ ነው።

መንግሥት ጣልቃ ገብቶ የመኖሪያ ቤት የኪራይ ዋጋ መናርን ለማስተካከል፣ የቤት ኪራይ ውል በሕግ እንዲመራ ለማድረግ የሚያስችለውንና በአከራይና ተከራይ ላይ ተፈጻሚ የሚሆን አዋጅ፣ ባለፈው መጋቢት 24 ቀን 2016 ዓ.ም በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ፀደቀ። አዋጁ ‹‹የመኖሪያ ቤት ኪራይ ቁጥጥርና አስተዳደር›› የሚል ስያሜ የተሰጠው ሲሆን፣ ዓላማው ግልጽና ተገማች የሆነ የመኖሪያ ቤት ኪራይ አስተዳደር፣ እንዲሁም የአከራይና ተከራይን መብት ሚዛናዊ በሆነ መልኩ የሚያስተናግድ ሥርዓት ለመዘርጋት ያለመ ነው።

በኢትዮጵያ ሕገ መንግሥትም ሆነ በዓለም አቀፍ ሕጎች ከሚታወቁ ሠብዓዊ መብቶች መካከል አንዱ መኖሪያ ቤት የማግኘት መብት ሲሆን፣ መንግሥት የመኖሪያ ቤት አቅርቦት ለማሻሻል የተለያየ ጥረት ቢያደርግም ከፍላጎቱ ጋር መጣጣም እንዳልቻለ ይታወቃል።

በቤት ፍላጎትና አቅርቦት መካከል ያለውን ሰፊ ልዩነት በመጠቀምም ምክንያታዊ ያልሆነ የቤት ኪራይ ዋጋ ጭማሪዎች በሀገሪቱ ከተሞች እየተስተዋሉ መምጣታቸውን፣ በዚህም ሳቢያ ዝቅተኛ ገቢ ያላቸው ነዋሪዎች መቸገራቸውንና ተረጋግተው ኑሯቸውን እንዳይመሩ ማድረጉን፣ በተጨማሪም የመኖሪያ ቤት የኪራይ ዋጋ መናር በከተሞች የሚስተዋለውን የኑሮ ውድነት እያባባሱ ከሚገኙ ቁልፍ ጉዳዮች አንዱ መሆኑ፣ ይህንን ችግር ለመቅረፍ የመንግሥት አስተዳደራዊ ጣልቃ ገብነት አስፈላጊ ሆኗል:: የኪራይ ዋጋ ጭማሪን በተመለከተም በተቆጣጣሪው አካል ከሰኔ 30 ቀን ጀምሮ ለአንድ ዓመት የፀና የዋጋ ጭማሪ እንደሚደረግ ተገልጿል::

አዋጁ ከመታተሙ በፊት ከፀደቀበት ዕለት ጀምሮ የፀና እንደሚሆን፤ አንድ የውል ዘመን ከሁለት ዓመት ሊያንስ እንደማይችል ገልጸዋል:: የቤት ኪራይ ውልና ዋጋ እንደ ክልሎች ነባራዊ ሁኔታ መወሰን እንዳለበት የተደነገገ ሲሆን፣ ይህንንም የሚቆጣጠር በክልል ደረጃ የሚሰየም አካል እንዲኖር መደረጉን፤ በዚህ መሀል በሁለቱ ወገኖች መካከል አለመግባባቶች ሲፈጠሩ ጉዳዩን ተቆጣጣሪው አካል እንደሚመለከተውና ወደ ፍርድ ቤት እንደማይሄድ፤ ይህም የሆነው በመደበኛ የሕግ ሒደት ላይ ጫና እንዳይፈጠር በማሰብ መሆኑ በጸደቀበት ወቅት ተብራርቷል::

አዋጁ ስለቤት ኪራይ ሲያብራራ፣ ለመኖሪያ ቤት የሚያገለግል ከአንድ ክፍል ቤት ጀምሮ መሆኑን፣ ለአጭር ጊዜ የኪራይ አገልግሎት የሚሰጡ ማለትም ሆቴል፣ ሪዞርት፣ እንዲሁም አልጋ ቤቶችን እንደሚያካትት፤ አዲስ የተገነባ ወይም ለመጀመሪያ ጊዜ የሚከራይ ቤት የኪራይ ዋጋ በአከራይና በተከራይ ስምምነት የተዋዋይ ውል እንዲፀና ይደረጋል::

ተከራዩ ውሉን ማቋረጥ ቢፈልግ ከሁለት ወራት በፊት ቀድሞ ማሳወቅ እንደሚኖርበት በአዋጁ ላይ የተቀመጠ ሲሆን፣ ቤቱን ተከራይቶ ሲኖር የኪራይ ክፍያውን ለመጀመሪያ ጊዜ ለ15 ቀናት ካሳለፈና ለሁለተኛ ጊዜ ለሰባት ቀናት ካሳለፈ፣ አከራዩ ውሉን ማቋረጥ እንደሚችል ተደንግጓል:: ተከራይ ሊጠየቅ የሚችለው ቅድመ ክፍያም ከሁለት ወራት የቤቱ ኪራይ ዋጋ ሊበልጥ አይችልም::

አከራዩ ቤቱን ለመሸጥ ሲፈልግ ለተከራዩ የማሳወቅ ግዴታ ባይኖርበትም፣ ቤቱን የሚገዛው ግን ውሉ እንዲቀጥል ካልፈለገ ለተከራዩ የስድስት ወራት ጊዜ መስጠት እንደሚኖርበት፣ ለአዲስ ተከራይ ሲያከራይም ከዚህ በፊት ከነበረው የኪራይ ዋጋ በላይ አድርጎ ማከራየት እንደማይችል ተደንግጓል። ነገር ግን ቤቱ የሚተላለፈው በስጦታ ከሆነ የውል ዘመኑ እስኪጠናቀቅ ድረስ ውሉ ቀጣይነት ይኖረዋል::

በሌላ በኩል ቀደም ሲል ሲከራይ የነበረ የመኖሪያ ቤት ወይም ግንባታው የተጠናቀቀ አዲስ ቤት ያለ አገልግሎት ከስድስት ወራት በላይ እንዲቀመጥ ከተደረገ፣ ቢከራይ አከራዩ ሊከፍል ይችል የነበረውን የኪራይ ገቢ ግብር ተሠልቶ እንዲከፍል ይደረጋል:: የቤት ኪራይ ክፍያን በተመለከተም በባንክ ወይም በሌላ ሕጋዊ የኤሌክትሮኒክ ዘዴ ብቻ እንዲፈጸም በአዋጁ ተደንግጓል::

አዋጁ ተግባራዊ ከመደረጉ በፊት የነበሩ የአከራይ ተከራይ ውሎችን የሚያስቀር አለመሆኑ የተገለጸ ሲሆን፣ አዋጁ ሲወጣ የነበረ ውል እስከ ቀጣዩ ሦስት ወራት ድረስ እንዲመዘገብ ይጠበቃል:: ይህን አዋጅ የጣሰ አከራይና ተከራይ የወንጀል ቅጣት እንደማይጣልበት፣ ነገር ግን አስተዳደራዊ ቅጣት እንደሚጣልበት ተገልጿል::

አዋጁ የአከራዩንና የተከራዩን መብት በማጣጣም የሚያስከብር ስለመሆኑ፣ በሁለቱ መካከል አለመግባባት ካለ በተቆጣጣሪው አካል በሚደረግ አስተዳደራዊ ፍትሕ የሚቀረፍ መሆኑ፤ አዋጁ የመኖሪያ ቤት ችግር በስፋት በሚስተዋልባቸው ከተሞች ተግባራዊ የሚደረግ ስለመሆኑና ዝርዝር አፈጻጸሙ ግን ለከተማ መስተዳድሮችና ለክልሎች እንደሚሰጥ፤ አዋጁ አነስተኛ ገቢ ያላቸው የመንግሥት ሠራተኞችና የከተማ ነዋሪዎች በአሁኑ ወቅት ያጋጠማቸውን የኑሮ ጫና ለመቀነስ ታስቦ የተዘጋጀ ነው። አፈጻጸሙ በሒደት የሚታይ ነው።

ዜጎች ከሚያገኙት ገቢ ከ25 እስከ 30 በመቶ በላይ ለቤት ኪራይ ማዋል የለባቸውም። አንድ ተከራይ ምንም ዓይነት የዋጋ ጭማሪ ሳይደረግበት በተከራየው ቤት ውስጥ ለሁለት ዓመታት ያህል ተረጋግቶ መኖር እንዲችል አዋጁ መብት ይሰጠዋል::

የቀረበው አዋጅ የመኖሪያ ቤቶችን ኪራይ ብቻ የሚመለከት እንደሆነ፣ የንግድ ቤቶችን የኪራይ ዋጋና ውልን በተመለከተ በሒደት እንደሚታይ መገለጹ የሚታወስ ቢሆንም በከፍተኛ የዋጋ ግሽበት ላይ ላለች ሀገር ለነገ ይደር የሚባል ጉዳይ መኖር የለበትም:: አዋጁ ከመኖሪያ ቤት የኪራይ ዋጋና የኪራይ ውል ጋር የተገናኙ ችግሮችን ለመፍታት የሚያስችል ሥርዓት የሚያበጅ ከመሆኑ ባሻገር፣ መንግሥት ከቤት ኪራይ ገቢ ሊያገኝ የሚገባው የኪራይ ግብር በአግባቡ እንዲከፈል በማድረግ የከተሞችን ገቢ ለማሳደግ ያስችላል ።

ሆኖም አዋጁ ዋና የዋጋ ግሽበትና የኑሮ ውድነት አባባሽ የሆነውን የንግድ ሱቅና ሕንጻ ኪራይ አለማካተቱ ሙሉኡ እንዳይሆን አድርጎታልና መንግሥት እንደገና ሊያጤነው ይገባል ስንል በአክብሮት እናሳስባለን። በተረፈ የኑሮ ውድነትና የዋጋ ግሽበት በዘላቂነት እንዲፈታ በማዕቀፍ ማየት ይገባል።

ሰላምን ማረጋገጥ፣ ምርትና ምርታማነትን ማሳደግ፣ ብልሹ አሠራርንና ሙስናን ማስወገድ፣ ጠንካራ የፊስካልና የገንዘብ ፖሊሲን በመከተል የፋይናንስ ሥርዓቱን ማረጋጋት፣ አምራቹንና ሸማቹን ይበልጥ በቀጥታ ማገናኘት እና የሕግ የበላይነትን በተለይ በግብይት ሥርዓቱ ማስፈን ይጠይቃል።

**ሻሎም ! አሜን ።**

# ወቅታዊ

# ‹‹አመራሩ ሕዝቡን አስተባብሮ በመሥራቱ በፈተናዎች ውስጥ አመርቂ ስኬቶችን ማስመዝገብ ተችሏል››

-አቶ እንዳሻው ጣሰው
የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ርዕሰ መስተዳድር



ፎቶ፡- በረሁን ታደሰ

ፋንታነሽ ክንዴ

**የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ለውጡን ተከትሎ በአዲስ መልክ ከተደራጁ ክልሎች አንዱ ነው፡፡ በአዲስ መልክ ከተደራጀ ዓመት ያልሞላው ክልል ቢሆንም ክልሉ ላይ የሚስተዋለው አጠቃላይ የልማት እንቅስቃሴና የሰላም ሁኔታ ግን ልብን የሚሞላ ነው፡፡**

**አዲስ ዘመንም በዛሬው ወቅታዊ እትሙ በክልሉ እየተከናወኑ ስላሉ የሰላም፣ የልማት፣ የመልካም አስተዳደር ሥራዎች እንዲሁም እንደሀገር ለውጡን ተከትሎ በተገኙ ስኬቶች፣ ፈተናዎችና የታለፈባቸው መንገዶች ዙሪያ የክልሉ ርእሰ መስተዳድር አቶ እንዳሻው ጣሰው በክልሉ ለተገኙት የጋዜጠኞች ቡድን የሰጡትን ቃለ ምልልስ እንደሚከተለው አጠናቅሮ አቅርቧል፡፡ መልካም ንባብ፡፡**

**አዲስ ዘመን፡- ባለፉት ዓመታት የለውጥ አመራሩ ሰላምን ለማስፈንና ልማትን ለማረጋገጥ ያከናወናቸው ሥራዎችና የነበረው ቁርጠኝነት ምን ይመስላል?**

**አቶ እንዳሻው፡-** የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል የተመሠረተው ነሐሴ 12 እና 13 ቀን 2015 ዓ.ም በተካሄደው የክልሉ ምክር ቤት ጉባዔ ነው:: ነሐሴ 12 ቀን ክልሉ ተመስርቶ ነሐሴ 13 ደግሞ ልዩ ልዩ አዋጆች ለሥራ አስፈላጊ የሆኑ ጉዳዮች ከጸደቁ በኋላ ወደ ሥራ ገብተናል:: የክልሉ በአዲስ መልክ መደራጀት የለውጡ ቱርፋቶች መካከል አንዱ ነው::

ባለፈው ስድስት ዓመት የነበረው ለውጥ የተመራበት መንገድ የሚባለው ፣‹ሪፎርም› ነው:: ሁለት ዓይነት የሚታወቁ ለውጦች አሉ:: አንዱ ‹ሪፎርም› ሲሆን፣ ሁለተኛው ‹ሪቮሉሽን› ነው:: ‹ሪቮሉሽን› አንድ መንግሥት ተቀይሮ ሌላ መንግሥት ሲመጣ አጠቃላይ ያለፈው መንግሥት ሲሠራባቸው የነበሩ የፀጥታ ፣ የፋይናንስ፣ የደህንነትና የመከላከያ መዋቅሮች እና ሌሎችም መንግሥታዊ አገልግሎት ሲሰጡ የነበሩ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቶችን ጨምሮ ሁሉንም አፍርሶ በአዲስ ማደራጀት ነው::

የእኛ መንግሥት የተከተለው ሪፎርም ነው:: በሪፎርም ሂደት ከነበሩት ነገሮች የተሻለ ነገር ካለ ይወሰዳል:: ለዘመኑ የሚሆኑ አዳዲስ ሃሳቦች እንዲገቡ ይደረጋል:: ወደፊት ደግሞ ሊያሻግሩ የሚችሉ ስትራቴጂክ የሆኑ ነገሮች ይታከላሉ:: ከነበረን ነገር ይወስድና ራሱ ጨምሮ ለወደፊት ደግሞ የሚሄድበትን ነገር አይቶ የሚሠራ የለውጥ ዓይነት ነው:: ስለዚህ መንግሥት አጠቃላይ የተከተለው የለውጥ ሂደት ሪፎርም ነው::

በዚህ ሂደት ያለፉትን አምስትና አራት ዓመታት ያሳለፍነው በደቡብ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል ሥር ነው:: ከዛ በኋላ ማዕከላዊ ኢትዮጵያና ደቡብ ኢትዮጵያ በሚል ለሁለት ተከፍሏል:: በዚያን ወቅት በጋራ የተጀመረውን ሥራ ማእከላዊ ኢትዮጵያ ከሆነ በኋላ አንዳንዶችን ሥራዎች በላቀ ሁኔታ አንዳንዶችን ሥራዎች ደግሞ ከተጀመሩበት ባሕሪና ይዘት አንጻር እያየን የማስቀጠል ሥራ ሠርተናል:: ሪፎርም በባህሪው ከባድ ነው:: ብዙ የነበሩ ነገሮችን በጥቅሉ ይዞ ስለሚሄድ አመለካከቶችን ለማጥራት ሥራ የሚሠራው በአስተሳሰብ ነው፤ እሱን አጥርተን ተገቢው ደረጃ ላይ ማድረስ ይኖርብናል:: በርካታ ያላለቀላቸው ጉዳዮች ደግሞ በየጊዜው ይነሳሉ:: ለእነሱ በቂ ምላሽ መስጠት አንድ ነገር ሆኖ ሳለ፤ ሕብረተሰቡ የደረሰበት ደረጃ አዳዲስ ጥያቄዎች የሚያነሳበት ጊዜ ነበረ:: እነርሱ ላይ በደንብ አስቦ ለጥያቄዎች መልስ መስጠት የመሳሰሉት ጉዳዮች በለውጡ ሂደት ውስጥ በደንብ ታስበው የተሠሩ ናቸው:: ክልላችንን ጨምሮ ሌሎች አዳዲሶቹ ክልሎች የዚህ ለውጥ ቱርፋቶች ናቸው ብለን መውሰድ እንችላለን::

የክልሎቹ በአዲስ መልክ መደራጀት ዋንኛ ዓላማዎች ለሕዝቡ አገልግሎትን በቅርበት መስጠት፣ ተመሳሳይ ሥነልቦና ያላቸው አካላት በጋራ ሆነው ክልል መመስረት፣ በቅርበት ተገቢውን ክትትል አድርጎ ዜጎችን ወደ ልማት ለማስገባትና ሰላም ማስፈን ተግባራትንም በአግባቡ ለማከናወን ነው::

ሌላኛው ለውጡ ካስገኛቸው ቱርፋቶች አንዱ ተሳትፎን ማሳደግ ነው:: በአንድ ሀገር ግንባታ ውስጥ ሁሉም ዜጎች በተለይ እድሜያቸው 18 እና ከ 18 ዓመት በላይ የሆናቸው በሙሉ በራሳቸው ማሰብ ይችላሉ ተብሎ ስለሚታሰብ የእነርሱን ተሳትፎ በሁሉም መስክ ማጠናከር ያስፈልጋል:: ሀገራችን ያለፈችባቸው ሁለትና ሦስት ዓመታት ምንም እንኳን ከውስጥም ከውጭም የተለያዩ ችግሮች ያጋጠሙን ቢሆንም እነርሱንም እየመከትን ግን ደግሞ የተሳትፎ መጠንን ማሳደግ እጅግ በጣም ያስፈልግ ነበር:: በዚህ የሴቶች፣ የወጣቶችና የአረጋውያን ተሳትፎና የመሳሰሉት ጉዳዮች ተጠናክረው እየሄዱ እናያለን:: በተጨማሪም ተሳትፎ የወለደው ሀገራዊ ምክክር በየቦታው እየተከናወነ ነው ያለው:: እኛም እንደ አንድ ፓርቲ መንግሥት በሚወክለን ቦታ ላይ እየተሳተፍን እነዚህ ጉዳዮች ቢነሱ ብለን ሃሳብ እናቀርባለን:: መጨረሻ ላይ ተሰብስቦ የኢትዮጵያ አጀንዳ የሆኑ ጉዳዮች ይወሰዳሉ ብለን እናስባለን:: ይህ ተሳትፎ ያመጣው ውጤት ነው::

በለውጡ ሂደት ላይ በጣም ፈተና የነበረው ሁላችሁም እንደምታስታውሱት ከሰሜኑ ወንድሞቻችን ጋር ወደከፍተኛ ግጭት ገብተን ነበር:: ይህ ግጭት በርካታ የሰው ሕይወት ቀጥፏል:: በርካታ ንብረቶችን አውድሟል:: ኢኮኖሚያችንም እዛ ላይ እንዲውል ተደርጓል:: በአንድ በኩል ይህ እየተመራ በሌላ በኩል ደግሞ በሀገሪቱ ውስጥ የተጀመሩ ትልልቅ የመንግሥት ፕሮጀክቶች ሳይቋረጡ እንዲሠሩ ማድረግ ተችሏል:: ስለዚህ ጦርነትና ሌሎችም ችግሮች ውስጥ ባንሆን በለውጡ የተጀመሩ ሥራዎች የት ይደርሳሉ ብሎ ማሰብ ይቻላል::

ለውጡ በጣም የተደራጀ የአመራር አንድነትን ይፈልጋል:: ሪፎርም በደንብ ጠርቶ የሆነ ደረጃ እስኪደርስ በሕዝቡ ውስጥ ብቻ ሳይሆን በአመራሩ ውስጥም ብዙ ውዥንብር ይፈጠራል:: የሚጻፉ በርካታ ነገሮች አሉ:: ማህበራዊ ሚዲያ እንደምታውቁት ዛሬ የትኛውም ኮርነር ላይ የኢንተርኔት ግንኙነት ያለውና እጁ ላይ ላፕቶፕ ወይም ሌላ አይነት መሣሪያ ያለው ሰው የፈለገውን ነገር ጽፎ በቀላሉ ማስተላለፍ ይችላል:: እነዚህ ሁሉ የሚፈጥሩትን ጫና ተቋቁሞ የአመራርን አንድነት ጠብቆ ሁሉም በብልጽግናዊ አስተሳሰብ ውስጥ ገብቶ ቅድሚያ ለሕዝብና ለሥራ ሰጥቶ የመንቀሳቀስ ሁኔታ ከጊዜ ወደ ጊዜ እያደገ መጥቷል::

በአመራሩ መካከል ልዩነት ያለ በማስመሰል ሲነዙ የነበሩ ውዥንብሮችን ወደጎን ትቶ አመራሩ ጥሩ ቁመና ላይ ደርሶ በየቀኑ ስለሚሠራው ሥራ እያሰበ ነው:: በብልጽግና የተቀመጡ ፕሮግራሞች አሉ:: ማኒፌስቶው አለ:: እሱን መሠረት አድርጎ መንግሥት ደግሞ ከማኒፌስቶው የቀረጻቸው ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች አሉ:: እነዚህን ተግባራዊ ለማድረግ የአመራር ቁመናን ማስተካከል በጣም ፈታኝ የነበረ ቢሆንም ተሻግረነዋል:: የለውጡ ሂደት ተሳትፎና አመራርን በጣም አመጣጥኖ መሄድ እጅግ በጣም ያስፈልግ ነበር::

ፍትሐዊ ተጠቃሚነት ለውጡ እንዲመጣ ካደረጉ ጉዳዮች አንዱ ነው:: ሰዎች በአንድ ሀገር ላይ በጋራ ሲኖሩ በሁሉም መስክ ፍትሐዊ ተጠቃሚነትን እያረጋገጥን መሄድ አለብን:: አንዱ ቦታ በተለየ ሁኔታ ለምቶ አንዱ ቦታ ደግሞ የልማት ጉድለት ከታዬ መተማመን አይኖርም:: ኢትዮጵያ የምትባለው ሀገር የጋራ ጎጆ ነች:: ሁሉም ሰው የጋራ ተሣትፎ ኖሮት የሚሠራ ሆኖ ኢትዮጵያ ከምታመነጨው ኢኮኖሚ ደግሞ የሁሉንም አካባቢ ተጠቃሚነት እያረጋገጡ መሄድ ያስፈልጋል::

በትምህርት፣ በጤና፣ በግብርና ግብዓት፣ በመንገድ መሠረተ ልማት ግንባታዎች፣ በኤሌክትሪክ፣ በስልክና በመሳሰሉት ነገሮች ሕዝቡን እያስተሳሰሩ መሄድ ያስፈልጋል:: ያልገባባቸው ቦታዎች ካሉ ማሳተፍ ያስፈልጋል:: ፍትሐዊነት በዚህ ብቻ ሳይሆን ሀገርን ከመምራት አንጻር ተሳትፎ ባልነው ላይ ማንሳትም ይቻላል፤ ነገር ግን በዋናነት የሚያተኩረው ፍትሐዊነት ወደሚለው ነው::

የብልጽግና ፓርቲ ከተመሠረተ ጀምሮ ወይም ከመመሥረቱ ዋዜማ ጀምሮ በፕሮግራሞቹ ውስጥ ከያዛቸው ነገሮች አንዱ ግማሹ በደንብ በፓርቲ ውስጥ የሚሳተፍ ግማሹ ደግሞ ውጪ ሆኖ የሚመለከት እንዳይሆን አድርጎ ነው:: ዋና እና አጋር የሚባል የለም፤ ሁሉም ለኢትዮጵያ ዋና ነው በሚል አስተሳሰብና ፕሮግራም መሠረት ከተቀረጸ በኋላ በሁሉም ክልል ያሉ አመራሮች ክልላቸውን እየመሩ በፌዴራል መንግሥቱ ላይም በቂ አስተዋጽኦ እንዲያደርጉ ተደርጓል:: አሁን ሁሉም ለሀገሩ እኩል ይንቀሳቀሳል:: በዚህም የሥልጣን ፍትሐዊ ክፍፍሉ ላይ በብልጽግና ዘመን ብዙ ነገር ተሻሽሏል::

እነዚህንና ሌሎችንም ጉዳዮች በሪፎርም ውስጥ አሳክቶ በሌላ በኩል ደግሞ የሀገር ልማቶችን ማከናወን ከባድ ነበረ፤ ቢሆንም ባለፍንባቸው ዓመታት ምንም እንኳን በተለያዩ ችግሮች ውስጥ ብንሆንም ከፍተኛ የኢኮኖሚ እድገት ማስመዝገብ ተችሏል:: እድገቱን እኛ ብቻ ሳንሆን የኢኮኖሚ እድገት የሚመዝኑ ሀገራት መዝነው ያረጋገጡት በጦርነት ውስጥም ሆነን ከስድስት ነጥብ አምስት እስከ ሰባት ነጥብ አምስት እያስመዘገብን መሆኑን ነው:: ይህ የአመራሩ መግባባትና ውህደት የፈጠረው ነው:: ለወደፊትም ይህችን ሀገር ወደተሻለ ደረጃ ለማድረስ ተጠናክረን መቀጠል ይኖርብናል:: አሁን የምንሰጠው አመራር ብቻ በቂ አይደለም:: አዳዲስ ሃሳቦችን ማምጣትና ማፍለቅ፣ የሕብረተሰቡን ተሳትፎ በየጊዜው ማሳደግና የጎደሉ ነገሮችን ቆጥረን መሙላት አለብን:: ይህን ማድረግ የምንችል ከሆነ የሕዝባችንን ኑሮ ለመቀየርና ብልጽግናን በኢትዮጵያ ለማረጋገጥ የጀመርነው ሥራ የሚሳካበት ጊዜ ሩቅ አይሆንም ብዬ አስባለሁ::

**አዲስ ዘመን፡- ከለውጡ ወዲህ ትኩረት ተሰጥቷቸው እየተተገበሩ ካሉ ኢንሼቲቮችና የልማት ፕሮግራሞች አንዱ የአረንጓዴ ዐሻራ መርሃግብር ነው:: በክልሉ ያለው የአረንጓዴ ዐሻራ መርሃግብር አተገባበር ምን መልክ አለው? ምን አይነት ውጤቶችስ ተመዘገቡ?**

**አቶ እንዳሻው፡-** የአረንጓዴ ዐሻራ ሥራን ስናከናውን የሚጠቀሰው ያከናወነውን ሀገር ብቻ አይደለም:: ለምሳሌ በዓለም አቀፍ ደረጃ ትልልቅ ደን ያለባቸው እንደ አማዞን ያሉ አካባቢዎች አሉ:: አማዞን በደንብ በመጠበቁ የሚጠቀሙት ደቡብ አሜሪካ ወይም ሰሜን አሜሪካ አካባቢ ያሉ ሰዎች ብቻ አይደሉም:: የአማዞን አካባቢ አየር ሲስተካከል የእነሱ አየር መስተካከል ቱርፋቱ ለእኛም ይጠቅመናል::

ሩቅ መሄድ አያስፈልግም:: ከአዲስ አበባ 550 ወይም 600 ኪሎ ሜትር ስንጓዝ ኢሉአባቦር መቱን እንዳለፍን የጎሬ ደን የሚባል አለ:: እሱን ይዘን ወደታች ወደ ደቡብ ምዕራብ ስንገባ ማሻ የሚባል አካባቢ አለ:: በጣም ግዙፍ ደን ነው:: ይህ ደን ለአርባ ለሃምሳ ዓመት ተጠብቆ የቆየ ነው:: ይህ ደን እዛ አካባቢ መኖሩ ለአካባቢው ማህበረሰብ ዝናብ በማምጣት የአየር ሁኔታውን በማስተካከል ሌሎች አካባቢዎች ድርቅና ረሀብ ሲከሰት እዛ አካባቢ እንዳይከሰት የሚያደርግ ነው::

የአረንጓዴ ዐሻራ ፕሮግራም እጅግ በጣም አስፈላጊ ፕሮግራም ነው:: አረንጓዴ ልማት እየተሠራ ያለው በእቅድ ነው:: በየዓመቱ በዚህ ክልል ከመከፈሉ በፊት መረጃ አለ:: ከ300 ሚሊዮን በላይ ችግኞች እየተዘጋጁ ይተከላሉ:: የችግኞቹ አይነት አንዳንዱ የአየር ጸባዩን ለመጠበቅ በኋላም ለመድሃኒትነት የሚያገለግሉ ተቆርጠው ለጣውላ የሚሆኑ የመሳሰሉት ችግኞች ይተከላሉ:: በተጨማሪም ለምግብነት የሚውሉ ችግኞችም በግለሰብ ጊቢ ውስጥ እንዲሁም ማሳ ላይ እንደማንጎ እና አቮካዶ የመሳሰሉት የፍራፍሬ ተክሎች እየተተከሉ ነው:: ችግኞችን መትከል ብቻ አይደለም:: ዋናው ጉዳይ ከተተከለ በኋላ እንክብካቤ ይፈልጋል፤ ከእንክብካቤ በኋላ የመጽደቅ መጠኑ በየዓመቱ እያረጋገጡ መሄድ ያስፈልጋል::

አሁን ባለንበት ማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ሰባት ዞኖች፣ ሦስት ልዩ ወረዳዎች አሉ:: ይህ የአረንጓዴ ዐሻራ ፕሮግራም ሁሉም ዘንድ ተግባራዊ እየተደረገ ነው:: ለምሳሌ የያዝነውን የ2016 ዓ.ም ብናነሳ ከጥቂት ጊዜ በኋላ ወደዚህ ፕሮግራም እንሻገራለን:: ለተከላ የሚሆን ወደ 350 ሚሊዮን ችግኝ ተዘጋጅቷል:: ችግኙ የሚዘጋጀው በሁለት አካላት ነው:: አንደኛው በክልሉ ግብርና ቢሮ ሲሆን፣ ሁለተኛው ደግሞ ደንና አካባቢ ጥበቃ ባለሥልጣን አማካኝነት ነው::

በክልሉ ከአንድ ሺህ 800 በላይ ችግኝ ማፍያ ቦታዎች አሉ:: በእነዚህ ቦታዎች ላይ ችግኞችን የማዘጋጀት ሥራ ሲሠራ ቆይቷል:: በተለይ ችግኝ ከሆኑ በኋላ ምን አይነት ችግኝ ነው መተከል ያለበት በሚለው ላይ በቂ ሥራ እየተሠራ ነው:: ያደገ ችግኝ የሆነ ቦታ ላይ ሲተከል ወዲያው ሊጸድቅ የሚችል መሆን አለበት:: አንዳንድ ችግኞች በጣም አነስተኛ ሆነው ስንተክላቸው የማይጸድቁ ሊሆኑ ይችላሉ:: ይሄ ጥንቃቄ ተደርጎበት እየተሠራ ነው:: ለምግብነት በሚውሉ ችግኞች ላይም ትልቅ ትኩረት ተሰጥቶ እተሠራ ነው:: ይህ ሥራ አየሩ እንዲስተካከል፣ ዝናብ እንዲፈጠር በማድረግ ሂደትም ትልቅ አስተዋጽኦ ያበረክታል:: ከውበት ባሻገር ተፈጥሮን፣ አካባቢን በመጠበቅ ትልቅ ሥራ አላቸውና ይህን ሥራ እያስፋፋን መሄዳችን የህልውና ጉዳይ ነው::

ከዚህ በፊት ነበረው የኢትዮጵያ የደን ሽፋን ከ23 በመቶ በላይ እንደነበር ይገለጻል:: አረንጓዴ ዐሻራን በደንብ ለመሥራት ሲታሰብ የኢትዮጵያ የደን መጠን ከሦስት በመቶ በታች ወርዶ ነበር:: ይህን ተከትሎም ኢትዮጵያ ውስጥ በየአስር ዓመቱ የሚከሰት ድርቅ ነበር:: አንዳንዶችም ወደ ረሃብ ተቀይረዋል:: የዚህ የአረንጓዴ ዐሻራ ፕሮግራም በደንብ መስፋፋት ከጀመረ በኋላ ድርቅ የሚከሰትባቸው አካባቢዎች በደንብ እየቀነሱ፣ በረሃማነት ባለባቸው ቦታዎች ጭምር ውሃዎችን ጠልፎ በመውሰድ የአረንጓዴ ልማት በማልማት ለውጥ ለማምጣት ተሞክሯል::

የእኛ አካባቢ በተፈጥሮው ሲታይ ሦስት አይነት የአየር

ወደ ገጽ 8 ዞሯል

# ወቅታዊ

# ‹‹አመራሩ ሕዝቡን አስተባብሮ በመሥራቱ ...

ከገጽ 7 የዞረ

ንብረት አለው:: ይኸውም የደጋ፣ ወይና ደጋ እና ቆላማ ነው:: አብዛኛውን ቦታ የሚይዘው ደጋና ወይና ደጋ ነው:: ከመጀመሪያውም ጀምሮ ዛፎች ነበሩት፤ ተክሎች ነበሩት ማለት ይቻላል:: ግን የተወሰኑ ቦታዎች ደግሞ ወደ በረሃማነት እየተለወጡ ነበር:: ስለሆነም ቶሎ ከስር ከስር መትከል ጥቅም ስለነበረው ይህ ፕሮግራም ተጠናክሮ እንዲቀጥል ይፈለጋል:: በመሆኑም በጠንካራ ክትትልና በጥብቅ ዲሲፕሊን እየተተገበረ ነው::

**አዲስ ዘመን፡- ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በስውጥ አመራሩ በትኩረት እየተሠራባቸው ከሚገኙ ሥራዎች አንዱ የሌማት ቱርፋት ይጠቀሳል:: በማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ያለው አተገባበርና እየተመራበት ያለው መንገድ ምን ይመስላል?**

**አቶ እንዳሻው፡-** የልማት ቱርፋት ዋና ዓላማው በገጠርና በከተማ የምግብ ዋስትናን ማረጋገጥ ነው:: አሁን ባለንበት ደረጃ ከተረጅነት አልወጣንም:: ኢትዮጵያ ብዙ የሰው ኃይል ያላት፣ አፈሯ በጣም ለም የሆነ፣ ብዙ ወንዞች ከዳር እስከዳር የሚፈሱባትና ብዙ ጉልበት ያላት ሀገር ናት፤ ነገር ግን ተረጅነት ውስጥ ያለች ሀገር ናት:: ተረጅነት ደግሞ በጣም አንገት የሚያስደፋ ተግባር ነው::

አንገት ማስደፋት ብቻ ሳይሆን የሕዝብን ክብር አሳልፎ የሚሰጥበት ሁኔታ እንዲፈጠርም ያደርጋል:: የሚረዱ ሀገሮች ርዳታ ሲሰጡ ዝም ብለው ርዳታ አይሰጡም:: ርዳታ ሲሰጡ ይህን አድርጊ ያንን አድርጉ ብለው ነው:: አንዳንድ የሚያቀርቧቸው ጉዳዮች ፖሊሲ እስከማስቀየር የሚደርሱ ናቸው:: በዚህ መልኩ ነው መቀጠል ያለብን ወይስ ያለንን ሀብት በማወቅ ሀብታችንን በአግባቡ በማስተዳደር የሕብረተሰቡን ኑሮ መቀየር አለብን ተብሎ ምርጫ ሲቀመጥ ሁለተኛውን ምርጫ ነው የወሰድነው:: ሀብት አለን፤ ሀብታችንን በአግባቡ መለየትና በአግባቡ ማስተዳደር አለብን የሚል ቁርጠኛ አቋም ነው ያለው መንግሥት:: በዚህ መሠረት በትኩረት እየተተገበሩ ከሚገኙ የልማት ፕሮግራሞች አንዱ የሌማት ቱርፋት ነው::

የሌማት ቱርፋት ቀለል ባለ መንገድ ለመግለጽ አንድ የከተማም ሆነ የገጠር አባወራ ዶሮ ቢኖረው እንቁላል ያገኛል:: ላም ቢኖረው ወተት ያገኛል:: ድንች፣ ስኳር፣ ድንች የመሳሰሉ ሥራ ሥሮችን ቢተክል ሌላ ተጨማሪ ምግብ ያገኛል:: ጓሮው ላይ ቀፎ ቢሰቅል ማር ማግኘት ያስችለዋል:: እነዚህ ወደሌማት ሲመጡ አንድ ላይ ተጠራቅመው የሌማት ቱርፋት ይባላሉ:: የየቀኑን የምግብ ፍጆታ ይችላል ማለት ነው:: የቀን የምግብ ፍጆታ መቻል ብቻ ሳይሆን የተረፈውን ነገር ደግሞ ወደ ገበያ ያወጣል::

ከዚህ አንጻር እንደ ክልል እየተተገበሩ ያሉ ሁለት ኢንሼቲቮች አሉ:: የመጀመሪያው ሰላሳ፣ አርባ፣ ሰላሳ ይባላል:: ይህም ማለት አንድ አርሶ አደር በመጀመሪያው ዓመት ሰላሳ የፍራፍሬ ዛፎችን ይተክላል:: በሁለተኛው ዓመት አርባ ይተክላል:: በሦስተኛው ዓመት ሰላሳ ዛፎችን ይተክልና በሦስት ዓመት አንድ መቶ የፍራፍሬ ዛፎች ይኖሩታል ማለት ነው:: ከመቶው ውስጥ ግማሹ አቮካዶ፣ ሙዝ፣ ፓፓያና ሌሎችንም የፍራፍሬ ተክሎች የሚያካትት ነው:: እነዚህ ዛፎች ምርት መስጠት ሲጀምሩ የቤተሰቡን የምግብ ፍላጎት ማሟላት ብቻ ሳይሆን ወደ ገበያ የሚወጣም ይኖራል::

ሁለተኛውና ከዶሮ ጋር የተያያዘው ኢንሼቲቭ ደግሞ አምስት፣ አስር፣ ሃያ አምስት ይባላል:: አንድ አርሶ አደር በመጀመሪያው ዓመት አምስት በሁለተኛው ዓመት አስር እንዲሁም በሦስተኛው ዓመት ሃያ አምስት ዶሮዎች እየጨመረ ይሄዳል:: አምስት ዶሮዎች ያለው ሰው በቀን አምስት እንቁላል ይኖረዋል:: ይህን እንቁላል ለቤተሰቡ ምግብነት ቢያውለው አልያም ወደ ገበያ አውጥቶ ቢሸጠው ትልቅ ጥቅም ያስገኝለታል:: በዚህ መልኩ ሌማት ቱርፋትን በሰፊው ተግባራዊ በማድረግ ውጤታማነትን ማሳደግ ያስፈልጋል:: ከተማ ላይ ብዙ መሬቶች ባዶ ናቸው:: ይህን ቦታ ቆፍሮ ጎመን፣ ሰላጣ፣ ድንች፣ ቲማቲምና ሌሎችንም የጓሮ አትክልቶች ማምረት ይቻላል:: በዚህም ሌማታችንን ሙሉ ማድረግ እንችላለን:: እንደ ክልል በዚህ ላይ በጣም የተጠናከረ ሥራ እየተሠራ ነው::

አንዳንድ ቦታ በደንብ የገባቸው ሰዎች ፕሮግራሙን በአግባቡ ተረድተውና የሚደረግላቸውን ድጋፍ በአግባቡ ተጠቅመው ትልልቅ ውጤት እያስመዘገቡ ነው:: አንዳንድ ቦታ በአግባቡ ያልገባቸውና ተጨማሪ ሥራዎችን የሚፈልጉትን በአግባቡ የማንቃት ግንዛቤ በመፍጠር ወደዚህ ሥራ ለማስገባት እየሠራን እንገኛለን::

በአጠቃላይ ሲመዘን በጥሩ መልኩ እየተገበረ ያለና ከተረጅነት አንዱ የመውጫ መንገዳችን ሊሆን የሚችል ነው:: በቀጣይነትም ሥራው ተጠናክሮ የሚቀጥል ይሆናል::



**አዲስ ዘመን፡- እንደ ክልል ከተሞችን ስኑሮና ስሥራ ምቹ ከማድረግ አንጻር እየተሠሩ ያሉ ሥራዎችስ ምን ይመስላሉ?**

**አቶ እንዳሻው፡-** የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ወደ 126 ሺህ የሲቪል ሰርቪስ ሠራተኛ አለው:: ከወረዳ ጀምሮ እስከ ክልል ድረስ አራት ሺህ 900 የሚደርስ አመራር አለ:: እነዚህን አመራሮች በማደራጀት በገጠርም በከተማም የሚከናወኑ ተግባራትን በተገቢው መንገድ ለማከናወን እየተሠሩ ያሉ ሥራዎች አሉ:: ከተሞችን ምቹ ለማድረግ መሠረታዊ ተብለው ከሚሠሩ ሥራዎች አንዱ አረንጓዴ ማድረግ ነው:: ሁለተኛው የከተሞችን የመጸዳጃ ቦታዎችን መሥራት፣ ከተሞችን ጽዱ ማድረግ እንዲሁም ከተሞች በማስተር ፕላን እንዲመሩ ማድረግን ያጠቃልላል::

ክልሉ በአዲስ መልክ ከተመሠረተ በኋላ በክልሉ የሚገኙ ሁሉም ከተሞች ማስተር ፕላናቸው እየተሠራ ነው:: የትኞቹ ከተሞች ስማርት መሆን አለባቸው ተብሎ ተለይቶ ለምሳሌ ቡታጅራና ሆሳዕና ከተሞች የስማርት ከተማ ባህሪ እንዲኖራቸው ለማድረግ ዲዛይን ተሠርቶ አልቋል::

ሌላው ከአዲስ አበባ ከተማ በቅርብ ጊዜ የተወሰደው ልምድ የኮሪደር ልማት በሦስት ከተሞች ይጀመራል:: ሆሳዕና፣ ቡታጅራና ወራቤ ከተሞች ላይ:: ሆሳዕና ላይ ጊዜውን አልጠበቅንም፤ አሁን ላይ ተጀምሯል:: በከተማዋ ከሚሠሩ መንገዶች ላይ አያይዞን ሥራው እንዲጀመር ተደርጓል::

ከተሞችን ምቹ ማድረግ ለከተሞች ገቢ ጥቅም አለው:: ለልዩ ልዩ ጉዳዮች ተመራጭ እንዲሆኑም ስለሚያደርግ ከተሞች ላይ በደንብ አቅደን እየሠራን ነው:: በማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ሰባት መቀመጫ ከተሞች አሉ:: ሆሳዕና የአስተዳደርና ፖለቲካ መቀመጫ፣ ቡታጅራ የኢኮኖሚ ክላስተር፣ ወራቤ ማህበራዊ ክላስተር፣ ወልቂጤ የመሠረተ ልማት እና የምክር ቤት መቀመጫ ናቸው:: በተጨማሪም ዱራሜ የግብርና ክላስተር መቀመጫ፣ ሳጃ የፌዴሬሽን ምክር ቤት እና የባህልና ቱሪዝም መቀመጫ ሆነው ያገለግላሉ:: እነዚህ ከተሞች የሚያድጉት ተያይዘው ነው:: ሆሳዕና ላይ የሚታሰብ ነገር ካለ ቡታጅራ ላይም ይታሰባል:: ቢሮ ግንባታ ከታሰበ ሁሉም ዘንድ ይታሰባል፤ ልዩ ልዩ ከተማን ሊያሳድጉ ሊያዘምኑ የሚችሉ ቴክኖሎጂዎች የምንጠቀም ከሆነ ሰባቱም ከተሞች ላይ እንጠቀማለን:: ይህን እየሠራን ሌሎች ደረጃ አንድ፣ ደረጃ ሁለት፣ ደረጃ ሦስትና ደረጃ አራት ያሉ ከተሞች ላይ ደግሞ የተለያዩ ፕሮግራሞች ተግባራዊ ይደረጋሉ:: በጥቅሉ ከተሞችን ማዘመን፣ ማሳደግና ለነዋሪዎች ምቹ ማድረግ ትኩረት ከሰጠናቸው ጉዳዮች መካከል አንዱ ነው::

**አዲስ ዘመን፡- ስሁሉም ሥራዎች መሠረቱ ሰላም ነውና የክልሉን ሰላም አስጠብቆ ስመቀጠል የተከናወኑ ተግባራትና የምትከተሉት ስትራቴጂ ምን ይመስላል? በቀጣይነትስ ይህን ሰላም አጽንቶ ስመቀጠል ምን ታስባል?**

**አቶ እንዳሻው፡-** ክልሉ ሥራ ከጀመረ በኋላ ቅድሚያ ትኩረት የሚሰጣቸው ብለን ሰባት ጉዳዮችን ለይተናል:: የመጀመሪያው ሥራ ሰላምና ፀጥታ፣ ሁለተኛው ግብርና፣ ሦስተኛው ገቢ፣ አራተኛው ትምህርት፣ አምስተኛው ጤና ሲሆን፣ ስድስተኛው አንድ ፓኬጅ አድርገን ንግድ ኢንቨስትመንትና የሥራ እድል ፈጠራ እንዲሁም ሰባተኛው የትኩረት መስክ መሠረተ ልማት ነው:: እነዚህ ሰባቱ ጉዳዮች በየዕለቱ የክልሉን ርዕሰ መስተዳድር፣ የዞን ዋና አስተዳዳሪዎች፣ የልዩ ወረዳዎችና የወረዳ አስተዳዳሪዎችን ትኩረት የሚፈልጉ ሥራዎች ተብለው ተለይተው በየቀኑ ተገናኝተን የምንፈትሻቸው ሥራዎች ናቸው::

ሰላም የሁሉም ነገር መሠረት ነው:: ለታቀዱት ሥራዎች ተግባራዊነት ሰላም በጣም አስፈላጊ ነው:: ስለዚህ እኛ እንደመጣን መጀመሪያ ያደረግነው ክልሉ ላይ ችግር ያለባቸውን ቦታዎች መለየት፣ የችግሩን መጠን መረዳት፣ ችግሩን ለመቀልበስ ምን መሥራት አለብን በሚለው ላይ በደንብ መወያየትና ለዚህ የሚመጥን እቅድ ማውጣት እንዲሁም የሥራ ስምሪት መስጠት ነበር::

ክልሉ ላይ ሰላምን ለማስጠበቅ የምጠቀምባቸው መንገዶች ሦስት ናቸው:: ማስተማር፣ ማወያየትት እና ሕግ ማስከበር ናቸው:: በዚህ መሠረት የማስተማር ሥራው በትምህርት ቤትና ለተለያዩ የማህበረሰብ ክፍል አደረጃጀቶች ይሰጣል:: ማወያየቱ ደግሞ እድሮች፣ የሸማግሌ ህብረቶች፣ የሸማች ማህበራት የመሳሰሉትን በማወያየት ይተገበራል:: ከዚህ ከፍ ያሉ ጉዳዮች ሲያጋጥሙ ደግሞ ሕግ እናስከብራለን:: ወንጀለኞች ተጠርጣሪዎች ይያዛሉ:: በሕጉ መሠረትም ይቀጣሉ::

የተወሰኑ አካባቢዎች ላይ ለምሳሌ ወደ አዲስ አበባ መሄጃ መንገዶች ከቡታጅራ ወደ ሌመን ስንወጣ የተወሰኑ ችግሮች ነበሩ:: በቱሉ ቦሎ በወሊሶ ወደ ወልቂጤ ስንመጣም እንዲሁ ችግር ነበር:: በባቱ አቋርጦ ወደ ቡታጅራ የሚመጣ አንድ መንገድ አለ:: እሱም ላይ የተወሰነ ችግር ነበር:: ይህ ችግር ከሸኔ እንቅስቃሴ ጋር የሚያያዝ ነበር:: የሀገር መከላከያ ሠራዊት፣ የኦሮሚያ ፖሊስና የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ፖሊስ በጋራ በመሆን መንገዶችን ነጻ ለማድረግ ተሞክሯል:: አልፎ አልፎ የሚከሰቱ ነገሮች አሉ:: አሁን ያለበት ደረጃ ግን አስተማማኝ፣ የመኪናዎች ዝውውር እንደልብ የሆነበት እና ቁሳቁስ ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ የሚሄድበት ሁኔታ ተፈጥሯል:: ይሄ ከማዕከላዊ መንግሥት ጋር የምንገናኝበት መንገድ ነው::

አጠቃላይ በውስጣችን አጀንዳቸው የተለያዩ የሆኑ ጉዳዮች ይነሱ ነበር:: አንዳንዱ የመዋቅር ጥያቄ፣ የወረዳ መዋቅር ጥያቄ፣ አንዳንዱ የማንነት ጥያቄ እና የመሳሰሉ ጥያቄዎች ይነሳሉ:: በውይይት ሁሉም ቦታ ያሉ ችግሮችን ለመፍታት ተሞክሯል:: ሌላው እንደማንኛውም አካባቢ ስርቆትን የመሰሉ ደረቅ ወንጀሎች አሉ:: እነዚህን ከሕብረተሰቡ ጋር በደንብ በመወያየት በየከተማው በየገጠሩ ችግር የሚፈጥሩ ሰዎችን በመምከርና በማስተካከል በተለይ በማህበራዊ ሚዲያ አላስፈላጊ ዘመቻ የሚዘምቱ ሰዎችን በመለየትና በማጥናት በርካታ ቁጥር ያላቸው ሰዎችን በቁጥጥር ስር አውለን ምርመራ እያከናወን ነው:: በወንጀላቸው መጠን ይቀጣሉ ማለት ነው::

ስለዚህ የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል መንግሥትና ሕዝብ ለሰላም ቁርጠኛ አቋም አለው:: ምክንያቱም ሰላምን ባላረጋገጥንበት ሁኔታ የግብርና፣ የትምህርት፣ የጤና ሥራዎችን መሥራትና ሌሎችንም ተግባራት ማከናወን አንችልም:: በመሆኑመ ሰላም ማረጋገጥ ላይ ቁርጠኛ አቋም ይዘን ነው እየሠራን ያለነው::

በአሁኑ ወቅት በክልሉ ያለምንም ችግር በነጻነት መንቀሳቀስ የሚቻልበት ሁኔታ ተፈጥሯል:: አሁን ያለው ሁኔታ ግን ለነገ ዋስትና አይሆንም:: ሰላምን ማረጋገጥ የሚቻለው በሁለት መንገድ ነው:: የመጀመሪያው ሰላምን በመጠበቅ በማስተዳደር ነው:: ሁለተኛ ተጨማሪ ልማት በመሥራት ነው:: ብዙ ጊዜ ችግር ውስጥ ገብተው የምናያቸው በእድሜ ትንሽ የሆኑ ልጆች ናቸው:: ስለሆነም ለእነዚህ ልጆች ተከታታይ ሆነ የሥራ እድል ፈጠራ ሥራ መሥራት ያስፈልጋል::

ሰው ሥራ ከያዘ፣ ራሱን ማስተዳደር ከጀመረና ቤተሰብ ከመሠረተ በኋላ ብዙ ጊዜ ወደ ችግር አይገባም:: ስለዚህ የሥራ እድል ፈጠራ በጣም በተፋዘዘባቸው አካባቢዎች ችግሮች ይጨምራሉ:: የሥራ እድል ፈጠራ በደንብ በተስፋፋባቸው አካባቢዎች ደግሞ ችግሮች ይቀንሳሉ:: የሥራ እድል ፈጠራን በደንብ በማጠናከር የዩኒቨርሲቲ ምሩቃን፣ ከቴክኒክ ሙያ የተመረቁ ልጆችን በሙሉ ወደ ሥራ ለማስገባት የተለያዩ እቅዶችን ይዘን እየሠራን ነው::

በአንድ በኩል ያለውን ሰላም በደንብ ማስተዳደር በሌላ በኩል ደግሞ ተጨማሪ ልማት መሥራት የሚሉትን አንድ ላይ ደምረን በመሥራት የክልሉን ሰላም ለማጽናት እየሠራን ነው:: ሰላምን ካላጸናነው ችግር አለበት:: የሆነ ጊዜ አንድ አካባቢ ሰላም አለ ብለን ልናወራ እንችላለን:: ያ ሰላም ዘላቂነት እንዲኖረው በተከታታይ የሚሠሩ ሥራዎች አሉ:: እነዛን ሥራዎች እየሠራን እንገኛለን::

**አዲስ ዘመን፡- በቀጣይነት እስከሁን በሁሉም መስክ የተመዘገቡ ውጤቶችን አጠናክሮ ከመቀጠልና የዜጎችን ተጠቃሚነት ከማረጋገጥ አንጻር ምን ታቅዷል?**

**አቶ እንዳሻው፡-** የተጀመሩ በርካታ ሥራዎች አሉ:: ሥራዎቹ ከበድ ከበድ ያሉ ናቸው:: ከበድ እንዲሉ ያደረጋቸው ዋናው ጉዳይ የህብረተሰብ ፍላጎት ጨምሯል:: የህብረተሰብ ፍላጎት ከመጨመሩ ባሻገር የእኛ ውድድር ኢትዮጵያ ውስጥ ብቻ አይደለም::

አሁን ያለንበት ዘመን የግሎባላይዜሽን ዘመን በመሆኑ ዓለም ወደ አንድ መንደር መጥታለች:: ይህም ውድድራችን ከብዙ ሀገራት ጋር እንዲሆን ያደርገዋል::

ስለዚህ የመጀመሪያው ጉዳይ የሚሆነው ይህን ውድድር በአግባቡ መረዳት ነው:: ሌላው ኢትዮጵያ ካለችበት ቦታ አንጻርና ከምናስተዳድራቸው ውሃዎች አንጻር አካባቢው የትኩረት አቅጣጫ እንዲሆን አድርጎታል:: ይህን አካባቢ የማይፈልገው ኃይል የለም::

ብዙ ሀገሮችም ወደ አፍሪካ ለመግባት ሲያስቡ መግባት የሚፈልጉት ኢትዮጵያን አቋርጠው ነው:: ኢትዮጵያ፣ የአፍሪካ ህብረትና የብዙ ዓለም አቀፍ ተቋማት መቀመጫ በመሆኗ ብዙ ሀገሮች ኢትዮጵያን የሚመለከቱበትን መንገድ በደንብ መረዳት ያስፈልጋል:: እኛ እንዴት ነው እምናያቸው ብቻ ሳይሆን እነሱ እንዴት ነው የሚያዩን የሚለውን ሁልጊዜ መተንተን ያስፈልጋል:: የውስጣችንን ነገር መተንተን የውጭውንም ነገር መተንተን ያስፈልጋል::

ሀገራችን ውስጥ ባለፉት ሦስት አራት ዓመታት የነበሩ ጦርነቶች ሲተነተኑ ኢትዮጵያውያን ፈልገው ያደረጉት ጦርነት ሳይሆን ሁሉም የውክልና ጦርነቶች ናቸው::

እነዚህን በደንብ ከተረዳን በኋላ ለውጡ እየተሻሻለ እንዲሄድ የአመራር ቁርጠኝነት መኖር አለበት:: ህብረተሰቡን አስተባብሮ ማሠራት፣ በየጊዜው በሚገኙ ድሎች አለመርካት ከዛ ይልቅ አዳዲስ ነገሮችን ለመሥራት መጣጣር ያስፈልጋል::

የህብረተሰብ ተሳትፎም በየጊዜው እያሳደገ መምጣት አለበት:: አሁን የደረሰበት ደረጃ በቂ አይደለም፤ ማደግ አለበት::

ሁሉም ዜጋ ኢትዮጵያ ውስጥ በሚነሱ የልማት፣ የማህበራዊና ሌሎች አጀንዳዎች ላይ መሳተፍ አለበት:: የፍትሐዊነትን ጥያቄ እያረጋገጡ መሄድም ሌላኛው የቤት ሥራችን መሆን አለበት::

ሌላውና ወሳኙ ጉዳይ የኢትዮጵያን ትርክት እያስተካከልን መሄድ ነው:: በተሳሳተ መልኩ እየቀረቡ ያሉ ትርክቶችን እያስተካከልን ሁላችንንም ሊያግባባ የሚችለውን መካከለኛውን መንገድ ይዘን መሄድ አለብን:: እነዚህንና ሌሎችንም አስፈላጊ ተግባራት የምናከናውን ከሆነ ለውጡ በታለመለት መንገድ ይሄዳል:: በተባለበት ጊዜም የኢትዮጵያ ብልጽግና ይረጋገጣል:: ለዚህ ደግሞ አመራሩና መላው የሀገሪቱ ሕዝብ እጅና ጓንት ሆኖ መሥራት ይገባዋል እላለሁ::

**አዲስ ዘመን፡- ስሰጡን ሰፋ ያስ ማብራሪያ በጣም እናመሰግናስን::**

**አቶ እንዳሻው፡-** እኔም አመሰግናለሁ::

ኢኮኖሚ

# ኢንቨስትመንት

## አምራችነት - የኢኮኖሚው ቀኝ እጅ የኢንቨስትመንት ትከሻ

መልካምሥራ አፈወርቅ





በሀገራችን የሆልቲካልቸር ኢንዱስትሪ በተቀናጀ መልኩ መንቀሳቀስ ከጀመረ ከአስራስምንት ዓመታት በላይ ዕድሜን አላስቆጠረም። በአበባው ዘርፍ የተሻለ የሚባል እንቅስቃሴ ቢኖርም የአትክልትና ፍራፍሬው ዘርፍ ግን ሀገራችን ካላት እምቅ ሀብት አኳያ በትኩረት ሊሠራበት እንደሚገባ ይታመናል።

መረጃዎች እንደሚጠቁሙት በአሁኑ ጊዜ በአትክልትና ፍራፍሬ ሽያጭ በዓለም አቀፍ ደረጃ ያለው ዋጋ ከአምስት መቶ ቢሊዮን ዶላር በላይ ሆኖ ተመዝግቧል። በዚሁ ዘርፍ ኢትዮጵያ በየዓመቱ ወደ ውጭ ልካ የምታገኘው ገቢ ግን ከ 50 ሚሊዮን ዶላር ያልበለጠ ነው። ሀገራችን ለምለምና ሰፊ የተፈጥሮ ጸጋዎችን የታደለች ምድር ናት። በማህጸኗም ጥራት ያላቸው የገጸ ምድርና ከርሰ ምድር እምቅ ሀብቶችን ይዛለች። ሌሎች በወጉ ያልታደሉትን ዓመቱን ሙሉ ጸሀይ የማግኘት በረከት ርቋት አያውቅም። በሚሊዮን የሚቆጠር አምራች ሃይልም በእጇ ነው። ለአውሮፓና ለመካከለኛው ምስራቅ ገበያ መዳረሻ አመቺነቷም ተፈላጊና ተመራጭ ደርጋታል።

ከዚህ አኳያ ዘርፉን በስፋት መጠቀም ከቻለች የዓለም ገበያን የመቆጣጠር ዕድል በደጇ ነው። በአሁኑ ጊዜ በመንግሥት በኩል ለኢንዱስትሪው የተሰጡ ማበረታቻዎች መልካም የሚባሉ ናቸው። ይህ እውነታም በዓለም ላይ በዘርፉ ተሠማርተው ከሚገኙ ጥቂት ሀገራት መካከል ኢትዮጵያ አንዷ እንድትሆን አስችሏታል።

የኢትዮጵያ አበባ አትክልትና ፍራፍሬዎች አምራች፣ ላኪዎች ማህበር 130 አባላቶችን ይዞ የሚንቀሳቀስ ግዙፍ የኢንቨስትመንት ዘርፍ ነው። ማህበሩ በአበባ፣ አትክልት፣ በቅንጥብ አበባና ፍራፍሬ ዘርፍ አምርቶ መላክ ላይ የተሠማሩ ዓለምአቀፍ ኢንቨስተሮችን ያሳትፋል። ከእስራኤል፣ ከኔዘርላንድ፣ ከህንድና ኢኳዶር ኢንቨስተሮች ጋር በመቀናጀት ይሠራል ።

በቅርቡ ማህበሩ በስፋት በሚንቀሳቀስባቸው የቆቃና ቢሾፍቱ የልማት ማሳያዎች ከተለያዩ ሚዲያዎች የተውጣጡ የጋዜጠኞች ቡድን በሥፍራው ተገኝቶ ጉብኝት አድርጓል። የመጀመሪያው ቆይታ የተከወነው ቆቃ በሚገኘውና «ሬድ ፎክስ ኢትዮጵያ» በተሰኘው ኩባንያ ነበር። ይህን ኩባንያ ለየት የሚያደርገው በጠንካራዎቹ ሴት የሥራ መሪዎች መዘወሩ ነው። ቀዳሚ መረጃዎች እንደሚጠቁሙት ኩባንያው ባለፉት ዓመታት ሲመራ የቆየው በውጭ ሀገራት ዜጎች ብቻ ነበር።

የድርጅቱ ዋና ስራ አስኪያጅ ዮርዳኖስ ጀማል እንደሚሉት መገኛው ቆቃ ምድር ላይ የሆነው «ሬድ ፎክስ ኢትዮጵያ» የሥራ ጅማሬ የሚነሳው እኤአ በ2003 ላይ ነው። በጀርመናውያን ዱበን ቤተሰቦች መሥራችነት ስሩን የሰደደው ሬድ ፎክስ አርባ ሄክታር መሬትን በምርቱ በረከት ይሸፍናል።

ኩባንያው በምርት ዘመኑ ከ2500 በላይ ትጉህ ሠራተኞችን ያሰማራል። በቋሚነትም 1 ሺህ 300 ሠራተኞች አሉት። ሬድ ፎክስ 72 በመቶ የሚሆነውን ድርሻ የሚሸፍነው በሴት ሠራተኞቹ ጠንካራ ክንድ ነው። በቆቃ ምድር በብዛት የሚመረተው ቅንጥብ አበባ ከዓመት እስከ ዓመት በተለየ ጥንቃቄና የአመራረት ሂደት በሰፊው የእርሻ ቦታ ተንጣሎ ይታያል።

በየዓመቱ ኩባንያው «ዱመን አሬንጅ» በተባለ የእርሻ ቦታው ከ120 ሚሊዮን በላይ የተለያዩ ቅንጥቦችን እያመረተ ለዓለም ገበያ ያቀርባል። አበባን ከአበባ በማዳቀል ሂደትም ውጤታማ ለመሆን የቻለ ኩባንያ ነው። ለቅንጥብ አበባው ምርት ህልውና የውሃ ምንጭ ሆኖ የሚቀዳው የአዋሽ ወንዝ በረከት በዙሪያው ይፈሳል። በየጊዜው ከዚህ ወንዝ የሚደርሰው ውሃ ግን እንደደረሰ ወደ እርሻው አይለቀቅም። በወጉ ተጣርቶ፣ ታክሞ ለምርቱ አገልግሎት እንዲደርስ ይሆናል።

በኩባንያው አሠራር አንዲትም ጠብታ ውሃ አትባክንም። ውሃን ሳይባክን መልሶ የመጠቀም ሂደት በአረንጓዴው ሥፍራ በሳይንሳዊ ሂደት በተግባር ተረጋግጧል። በአቅራቢያው የሚገኙ ሌሎች ወንዞችን ጠልፎ መጋራትም የአገልግሎቱ ሌላው የማሳያ ግብዓት ነው ።

ከምንም በላይ በገሀድ የሚስተዋለው እውነታ ለቅንጥቦቹ ደህንነት ሲባል የሚደረገው ጥንቃቄ ነው። በዚህ ሥፍራ ምንጊዜም ከንክኪ ነጻ የሚባል የንጽህና አጠባበቅ ሂደትን መተግበር ግድ ነው። በምርት ቦታው ከመነሻ እስከፍጻሜው ንጹህ ሆኖ ጀምሮ ንጹህ ሆኖ ማጠናቀቅን ይጠይቃል። ይህ እውነት ደግሞ እንደ መርህ ሆኖ በጽናት ይተገበራል።

አሁን የጋዜጠኞቹ ቡድን ወደ አረንጓዴው የአበባ ቅንጥቦች መንደር ለማምራት በዝግጅት ላይ ነው። ወደ ዱመን ኦሬንጅ ክልል ለመግባት ግን እግሮች እንደዋዛ ጉዞ አይጀምሩም። እያንዳንዱ ሰው ጥንቃቄ በሞላው ልዩ የንጽህና ሂደት ማለፍ ይጠበቅበታል። ወደ ውስጥ ለመሻገር ቀድመው የተዘጋጁ ሽርጦች፣ የእጅ ጓንቶችና ነጠላ ጫማዎች ጥቅም ላይ ይውላሉ። የግል ንብረቶችም በአደራ ይቀመጣሉ።

በየቦታው በሚኖር ዝውውር እጅን እስከ ክንድ በሳሙና መታጠብና ራስን ለቅንጥቦቹ ደህንነት በወጉ ማዘጋጀት ግድ ይላል። ወደ ውስጥ ማለፍ የሚቻለው ሞባይል ስልኮችን ጨምሮ በእጅ የሚገኙ ንብረቶች በአልኮል ታጥበውና ተጠርገው ከስጋት ነጻ መሆናቸው ሲረጋገጥ ብቻ ነው። ይህ ልምድ በየቀኑ በሠራተኞቹ ጭምር የሚተገበር አይቀሬ ግዴታ ነው።

ምርቱ ለሽያጭ ከመድረሱ አስቀድሞ የሚያልፍባቸው የራሱ ሂደቶች አሉ። እያንዳንዱ መስመርም ቅንጥቦቹን ከበሽታ በመከላከል፣ ንጽህናን መርህ ባደረገ ርምጃ መሀል ይጓዛል። ሁሉም ጎብኚ በተነገረው መመሪያ መሠረት ግዴታውን በአግባቡ እየተወጣ ወደ አረንጓዴው ግዙፍ ቤት ማምራቱን ይዟል።

የጉብኝቱ ቀዳሚ እይታ የጀመረው የቅንጥቦቹ የመጀመሪያ መሠረት ወደሚጣልበት ሰፊ ማሳ ላይ ነው። በዚህ ቦታ ቅንጥቡ ተቆርጦ በተለየ ዝግጅት ዘር ሆኖ እስከሚያወጣበት ደረጃ ያለው ሂደት ይታያል።

ቅንጥቡ ለአራት ሳምንታት ከቆየና ዘር መሆኑ ከተረጋገጠ በኋላ ምርታማነቱ ከሚጠበቅበት የዳበረ ሥፍራ በመትከል ሊያመጣ የሚችለውን ተጠባቂ ለውጥ በባለሙያዎች መከታተል ግድ ነው። ቅንጥቡ በቀጣዩ ሶስት ወራት በራሱ ሙሉ ሆኖና አካሉን ገንብቶ እንዲታይ ልዩ ክትትልና ቁጥጥር ይደረግለታል።

ቅንጥቡ ወደታሰበው ቁመና እንዲደርስ የተለያዩ ግብዓቶች ሊሟላለት ያስፈልጋል። የአየር ፀባዩ ልኬታ፣ የውሃ አጠቃቀሙ ሂደት ፣ የተመጣጠነ ምግብ አቅርቦት፣ የጸረ ቅንጣት ነፍሳት መከላከልና ሌሎችም ጥንቃቄዎች በአግባቡ ይተገበራሉ። በየሳምንቱ በሚኖረው ክትትልም በተክሉ ላይ የሚኖሩ የአበባ ቅንጣቶች በወጉ ተስተካክለውና አምረው ዕድገታቸው ጤናማ ሆነው መታየት ይኖርባቸዋል።

ቅንጥቦቹ ለዓለም ገበያው ፍላጎትና ለደንበኞች እይታ ከነወዘናቸው ይቀርቡ ዘንድ በወጉ እየተቆረጡ ባሉበት የጥራት ደረጃ ወደ ውጭ ሀገራት ገበያ የሚላኩበት ሁኔታ ይመቻቻል። ቅንጥቦቹ አንደ አይነትና ባህሪያቸው በተለያየ የሰው ሃይል ቁጥር የሚመረቱ ናቸው። የምርት ሂደታቸው የሚከወነውም በተለመደው አይነት በአፈር ላይ ተክሎ በማብቀል አይደለም።

ለእያንዳንዳቸው በተዘጋጀ ልዩ የመትከያ ዕቃ፣ ያለምንም የመሬት ንክኪ በአሸዋ ላይ ቆይተው ዕድገታቸውን ይጨርሳሉ። እንዲህ መሆኑ በተለምዶ ምርቱ በአፈር ላይ የከፋ ጉዳት ያስከትላል፣ የሚባለውን ስጋት ለመታደግ አስችሏል።

የአበባ ቅንጥቡ በምርት ደረጃ ሂደቱን ካጠናቀቀ በኋላ ወደውጭ ገበያ እንዲደርስ በተገቢው ሥፍራ ሊያልፍ ግድ ይለዋል። ይህ ቦታ በሃይለኛ ድምጽ የታጀበና ልብን ሰቅዞ በሚይዝ ከባድ ቅዝቃዜ የተሞላ ነው። በዚህ ክፍል ታሽጎ ሲዘጋጅም እያንዳንዱ ቅንጥብ የተመረተበት ጊዜ፣ ግራሙና ስያሜው ከሙሉ መረጃ ጋር በደማቅ ጽሁፍ ታትሞበት ይሆናል።

ሬድ ፎክስ ኢትዮጵያ ማህበራዊ ሃላፊነትን ለመወጣት በቆቃና አካባቢው በተለያዩ ገጽታዎች ይንቀሳቀሳል። ለማህበረሰቡ የአጸደ ህፃናትን ጨምሮ የአንደኛና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርትቤቶችን በማስገንባት ተደራሽነቱን እያሳየ ነው። በራሱ ክሊኒኮችም ትኩረቱን ኤች አይ ቪ ኤድስ ላይ በማድረግ ይሠራል።

ወላጅ አልባ ለሆኑ ልጆች ከሌሎች ተቋማት ጋር ተቀናጅቶ አስፈላጊውን ድጋፍ የሚያደርገው፤ ሬድ ፎክስ ለአካባቢ ጥበቃ ባለው ተሞክሮ ሰፊ ቦታን የሚሸፍን የአረንጓዴ ልማት ሥራዎችን እያለማ ቀጥሏል። ለቀድሞ ሠራተኞቹ ድጋፍ በማድረግና ጡረታ ወጥተው መኖሪያ ለተቸገሩ ቤት በመሥራትም አርአያነቱን አስመስክሯል።

በኩባንያው የሬድ ፎክስ ኢትዮጵያ ዋና ስራ አስኪያጅ ዮርዳኖስ ጀማል እንደሚያረጋግጡት በአካባቢው ለሚያስፈልጉ ማንኛውም የልማት ግብአቶች ድርጅቱ እስከ ሃያ ሚሊዮን ብር ወጪ በመሸፈን ማህበራዊ ሃላፊነቱን በመወጣት ላይ ነው።

የጋዜጠኞቹ ቡድን የጀመረው የመስክ ጉብኝት አልተጠናቀቀም። የቆቃው ሬድ ፎክስ ቆይታ እንዳበቃ ቀጣዩ ጉዞ ቢሾፍቱ ወደሚገኘው «ጆይ ቴክ» ኩባንያ ጊቢ አምርቷል።

ጆይ ቴክ መገኛውን ቢሾፍቱና ለገዳዲ ላይ አድርጎ የሚሠራ ኩባንያ ነው። በዋንኛነት ሳይንሳዊ ዘዴን ተግባራዊ በማድረግ የቲሹ ካልቸር ምርት ማባዛት ላይ ያተኩራል። ልክ እንደ ሬድ ፎክስ ሁሉ ይህ ኩባንያም ቀድሞ በውጭ ሀገር ዜጎች ሲመራ ቆይቷል።

ወደ ኩባንያው የማምረቻ ሥፍራ ለማለፍ አሁንም የተለየ ጥንቃቄ ማድረግ ግድ ነው። ማንም ወደ ውስጥ ባለፈ ጊዜ ነጭ ካፖርት፣ መልበስ፤ ጸጉርን መሸፈንና እጆቹን በአልኮል ማጽዳት ይጠበቅበታል። ይህን አልፈው ወደ ውስጥ ሲዘልቁ አፍንጫን በልዩ መአዛ የሚያውደው የቅጠላቅጠል ውህድ ውስጠትን ይቆጣጠራል።

ሠራተኞቹ እረፍት የለሽ ናቸው። ቅጠሎቹን እየቀነጠሱ፣ እየከተፉ፣ እያሹ፣ ይጣደፋሉ። ምርቶቹ በተለያዩ ሂደቶች አልፈው ለገበያ እስኪቀርቡ በየደረጃው አሠራራቸው ይለያያል። ከፍተኛ በሚባል የቅዝቃዜ ቆይታም ያልፋሉ።

የጆይ ቴክ ኩባንያ ቺፍ አፊሰር ብስራት ሃይለስላሴ እንደሚሉት በአበባ ኢንዱስትሪው ዘርፍ ሲንቀሳቀስ የቆየው ይህ ኩባንያ በአሁኑ ጊዜ በ100 ሄክታር መሬት ላይ አትክልትና ፍራፍሬዎችን በማምረት ለውጭ ሀገራት ገበያ በማቅረብ ላይ ይገኛል። ጆይ ቴክ ምርቶቹን ከአውሮፓ ገበያ በዘለለ በእስካንዲቪኒያና መካከለኛ ምስራቅ ሀገራት ተደራሽ በማድረግ ኢኮኖሚውን እየደገፈ ነው።

በኩባንያው ተመርተው የሚላኩትና በተለምዶ «እፀ-ጣዕም» ተብለው የሚታወቁት እንደ ድንብላል፣ በሶብላ፣ ጦስኝ ፣ናና ሮዝመሪኖ፣ ባሮ፣ ፐርስሊና ሌሎች ሀገር በቀል ምርቶች ባደጉት ሀገራት ገበያ በእጅጉ ተፈላጊ ሆነዋል። ምርቶቹ የሚበቅሉት በውሃ ላይ በመሆኑ ምርታማ፣ ለምለምና ፈጣን ናቸው።

እንደ አቶ ብስራት ገለጻም እነዚህ ምርቶች በሀገራችን እንደዋንኛ ምግብ የማይቆጠሩ ናቸው። ባደጉት ሀገራት ግን ከምግብነት ባለፈ ለማጣፈጫነትና ለመድሃኒትነት ጭምር ተፈላጊነታቸው ከፍተኛ እየሆነ ነው። ይህ እውነታም ለውጭ ምንዛሪውና ለኢንቨስትመንቱ ድርሻ ታላቅ አበርክቶ በማድረግ ላይ ይገኛል። በዓመትም እስከ 12 ሚሊዮን ዩሮ ማስገኘት ተችሏል።

የቲሹ ካልቸር ምርትን በማባዛት ለምግብ ዋስትናው መረጋገጥ ከፍተኛውን ሚና እየተወጣ ያለው ጆይ ቴክ አምራች አርሶአደሮችን በማበረታታት ጭምር ይታወቃል። ከ 1400 በላይ ሠራተኞችን ቀጥሮ በማሠራትም የሥራ ዕድል ፈጥሯል።

አቶ ቴዎድሮስ ዘውዴ የኢትዮጵያ አበባ አትክልትና ፍራፍሬዎች አምራች ላኪዎች ማህበር ዋና ዳይሬክተር ናቸው። የሚዲያ ባለሙያዎቹ የመስክ ጉብኝት የግብርናውን የልማት እንቅቃሴ በማረጋገጥ፣ ቴክኖሎጂንና መረጃን ተደራሽ ለማድረግ እንደሚያግዝ ይናገራሉ።

ከዛሬ ሃያ ዓመታት በፊት ኢትዮጵያ ከዘርፉ ታገኘው የነበረው ገቢ ከ24 ሚሊዮን ዶላር የበለጠ አልነበረም። በአሁኑ ጊዜ ግን ገቢው በእጥፍ በማደጉ ከቡና ቀጥሎ ከፍተኛውን ገቢ ማስመዝገብ ተችሏል።

መንግሥት 25 ቢሊዮን ብር በማውጣት አራት የኢንዱስትሪ ፓርኮችን ገንብቷል። ዳይሬክተሩ እንደሚሉት ባለፉት አስራ አንድ ወራት በአበባ ምርት ብቻ 494 ሚሊዮን ዶላር ማግኘት ተችሏል። ኢትዮጵያ ካላት ዕምቅ ሀብት አኳያ ግን ይህ ገቢ በቂ ነው የማይባል በመሆኑ ኢንዱስትሪውን በማስፋት አገልግሎቱን ይበልጥ ተደራሽ ማድረግ እንደሚገባ ይናገራሉ።

በጉብኝቱ ወቅት የጋዜጠኞችን ቡድን የተቀላቀሉት የመንግሥት ኮሚዩኒኬሽን ሚኒስትር ዴኤታ ሰላማዊት ካሳ በዕለቱ በሰጡት ማጠቃለያ የመስክ ምልከታው አስፈላጊነት ለዘርፉ የተሰጠውን ትኩረት በመጠቆም በጥረትና ተሳትፎ እየታየ በሀገራችን ያለውን ለውጥ ለማመላከት ነው።

እንደ ወይዘሮ ሰላማዊት ገለጻ ባለፈው ዓመት ከሆልቲካልቸር ዘርፍ ከአንድ መቶ 22 ሚሊዮን ኩንታል በላይ ምርት ለማግኘት ተችሏል። በዘንድሮ ዓመት ለማግኘት የተቃደው 318 ሚሊዮን ኩንታል ቢሆንም በክንውኑ ግን ወደ 344 ሚሊዮን ኩንታል ምርት ተገኝቷል።

እንደ ሚኒስትር ዲኤታዋ ይህ የተሻለ አፈጻጸም ሊገኝ የቻለው በመንግሥት በኩል በተደረገው ተለየ ትኩረትና ድጋፍ ነው። መንግሥት የግል ኢንቨስትመንቱን በማበረታታት አስተዋጽኦው ከፍ ያለ ነው። ሚኒስትሯ ቀደም ሲል ከግል ባለሀብቶች የሚነሱ የመሬት፣ የግብዓትና የውጭ ምንዛሪ ጥያቄዎች እንደነበሩ አስታውሰዋል።

እነዚህን ጨምሮ ለዘርፉ አስፈላጊ የሚባሉ ቀዝቃዛ የማጓጓዣ ግብዓቶችና ማከማቻዎች፣ የመሠረተ ልማትና የሃይል አቅርቦቶች አስፈላጊ መሆናቸውን መንግሥት እንዲገነዘብ ለማድረግ የመስክ ጉብኝቱን ወሳኝነት አጽንኦት ሰጥተውታል።

በግል ኢንቨስትመንቱ የአምራችነት ዘርፍ የሀገርን ኢኮኖሚ በአጋርነት የሚመራ ሃይል ነው። ዘርፉ ከመንግሥት ተገቢውን ድጋፍና ይሁንታ ባገኘ ቁጥር የዓለም ገበያውን ለመምራትና ተወዳዳሪ ሆኖ ለመዝለቅ ዕድሉ የሰፋ ይሆናል። እንዲህ በሆነ ጊዜ ሀገራችን ለማደግ መንገዷ ይቀናል። የመንግሥትን የድካም ትከሻ በመጋራትም የኢኮኖሚው ቀኝ እጅ ሆኖ ለመቀጠል ያግዛል።

ፖለቲካ እና ልዩ ልዩ

# ጎሜ

# ፖለቲከኞቻችን የበጎ ፈቃድ ሥራ አይመለከታቸውም ወይ ?

እስማኤል አረቦ

የበጎ ፈቃድ አገልግሎት ሰዎች በራሳቸው ተነሳሽነትና መልካም ፈቃድ ለኅብረተሰቡ ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴዎች ውስጥ በማሳተፍ ነፃ አገልግሎት የሚያበረክቱበት ተግባር ነው::

የበጎ ፈቃድ አገልግሎት የሰው ልጅ ምንም አይነት ክፍያ የማያገኝበት ይበጃል፣ ይሆናል፣ ያስደስታልና የህሊና እርካታ ያስገኛል ብሎ ያለምንም ቀስቃሽና ጎትጓች በእራሱ ተነሳሽነት የሚፈፅመው ተግባር ነው:: ይህ ተግባር ሰዎች ዘር፤ ቀለም ብሄርና ኃይማኖት ሳይለያቸው የሚሳተፉበት በጎ ተግባር ነው::

ሆኖም በገቢር እንደሚታየው የበጎ ፈቃድ በተነሳ ቁጥር ሁልጊዜ ግንባር ቀደም ሆነው የሚገኙት የተወሰኑ የህብረተሰብ ክፍሎች እና የመንግሥት አካላት ብቻ ናቸው:: ለቁጥር የሚያዳግቱት አብዛኞቹ የፖለቲካ ፓርቲዎች ግን በጎ ፈቃድ ሥራ ሲመጣ የት እንደሚገቡ አይታወቅም::

የፖለቲካ ፓርቲዎች መመሥረት ዋነኛ ጉዳይ የሀገር ልማት እና እድገት እስከሆነ ድረስ አብዛኞቹ ፓርቲዎች በበጎ ፈቃድ ለመሳተፍ ዳተኛ የሆኑበት ምክንያት እንቆቅልሽ ነው:: የፖለቲካ ፓርቲዎች ከምስረታቸው ጀምሮ እስከ ሥልጣን ድረስ ያሰቡትን ዓላማ ማሳካት የሚችሉት ሀገር ስትለማ ነው:: ሀገር የምትለማው ደግሞ በፖለቲካ ዲስኩር ወይም በፖለቲካ ሽኩቻ አይደለም::

በሠለጠኑት አለማት የፖለቲካ ፓርቲዎች አንዱና ዋነኛ መመዘኛ የበጎ ፈቃድ ሥራ ነው:: ተወዳድሮ ለማሸነፍና ሥልጣን ለመያዝ የመጀመርያው መመዘኛ ፓርቲው ወይም ግለሰቡ የሰራቸው በጎ ፈቃድ ሥራዎችና ያመጣው ውጤት ነው:: ያለበለዚያ በፖለቲካ ፓርቲነት መመዝገብና የመንግሥትን ህጸጽ እየፈለጉ ብቻ በመውቀስ ሥልጣን ላይ ፊጥጥ ማለት አይታሰብም::

የእኛ ሀገር የፖለቲካ ፓርቲዎች እሳቤ የሚመነጨው በተገኘው አማራጭ ሁሉ ወደ ሥልጣን መምጣት እንጂ ባከላቸው ጊዜ ለሕዝብ እና ለሀገር በጎ ሥራ መስራት አይደለም :: ለማንም ክፍት የሆነውና ሁሉም በሠብዓዊነት የሚሳተፍበትን የበጎ ፈቃድ ሥራ ለፖለቲከኞቻችን የተከለከለ ይመስል በአጠገቡም ዝር አይሉም:: እነሱ ሥልጣን ካልያዙ በስተቀር ሀገር የሌለች ይመስል ከፖለቲካ ወቀሳና ማጣጣል በስተቀር አባሎቻቸውን አስተባብረው ይህ ነው የሚባል የበጎ ፈቃድ ሥራ ሲሠሩ አይታይም::

አሁን በእጃቸው ያለውን የበጎ ፈቃድ ሥራ ሳይሠሩ ነገ ሥልጣን ጨብጠው የሚሠሩትን ሥራ እና የሚለውጡትን ሀገር ያልማሉ:: ይህ ደግሞ ህልም እንጂ እውን ሊሆን አይችልም::

ከ1960ዎቹ ጀምሮ ያለውን የፖለቲካ ባህል ስናይ በጎ ሥራ ሠርቶ ሀገር እና ሕዝብን ከመጥቀም ይልቅ የራስን ጥቅም፤ ከሕዝብ ፍላጎት ይልቅ የራስን ስሜት፤ ከሀገር ህልውና የፓርቲ ህልውናና ማስቀደም ላይ ትኩረት የሚደረግበት ነው:: ይህ ደግሞ ኢትዮጵያን ላልተገባ እሰጥ እገባና ግጭት አልፎ ተርፎም በማያባራ ጦርነት ውስጥ እንድትዘልቅ አድርጓታል::

የኢትዮጵያ ፖለቲካ ትልቁ ጉድለት ፖለቲካን ከሸፍጥ ጋር መቆራኘቱ ነው:: ፖለቲከኛ ወይም የፖለቲካ ፓርቲ አባል ሆኖ በጎ ሥራ መሥራት የተከለከለ ይመስላል:: ይልቁንም ሴራ መተንተንና መንግሥትን መውቀስ የአንድ የፖለቲካ ፓርቲ ጥንካሬ መለኪያ ተድርጎ እየተወሰደ ሀገር እና ሕዝብም ከፖለቲከኞች ማግኘት የሚገባቸውን ጥቅም እያጡ ነው፤ ይባሱንም ሀገርና ሕዝብን በማያራምድ አጀንዳ ሰቅዘው የኋሊት እንድንጓዝ እያደረጉን ነው::

> **የፖለቲካ ፓርቲዎች መመሥረት ዋነኛ ጉዳይ የሀገር ልማት እና እድገት እስከሆነ ድረስ አብዛኞቹ ፓርቲዎች በበጎ ፈቃድ ለመሳተፍ ዳተኛ የሆኑበት ምክንያት እንቆቅልሽ ነው**

የፖለቲካ ሥርዓታችን ለሀገር በጎ ማሰብና አለፍ ሲልም በበጎ ፈቃድ ሥራዎች ውስጥ ተሳትፎ ሕዝብና ሀገርን ከመጥቀም ሀገር በትብብር እንዳትቆም የጥላቻ መርዝ መንዛት ነው:: ተባብሮ ተደጋግፎ ሀገርን ማቆም ፖለቲከኞቻችን በሩቁ የሚሸሹት ጸበል ነው::

ተፎካካሪን እንደ ጠላት ማየትና ማሳደድ ለዓመታት የተፀናወተን ልማድ ነው:: አንዱ የፖለቲካ ፓርቲ ሲመሠረት ሌሎችን አጥፍቶና አንቋሾ፤ ጥላቻ ዘርቶና አኮስምኖ የራሱን ሥብዕና ለመገንባት ሲሞክር ማየት የተለመደ ነው::

በጋራ ሠርቶ ኢትዮጵያን ከድህነትና ከኋላ ቀርነት ከማላቀቅ ይልቅ መልካም ሥራ ሊሠራ የተነሳን ወገን ማንቋሸሽና በሕዝብ ዘንድም በጥርጣሬ እንዲታይ ማድረግ የኖርንበትና እየኖርንበት ያለ ሀቅ ነው:: በየጊዜው ጥላቻና ግጭትን መፈብረክ ሀገርን የኋሊት እንድትጓዝ ማድረግ አንዱ ፖለቲካ ታሪካችን ነው::

ሀገርን በተገኘው አጋጣሚ ሁሉ በመጠቀምና የአቅምን ያህል ሃሳብ ከማዋጣት ይልቅ ሀገርን በሚያፈርሱ አጀንዳዎች ውስጥ መጠመድ ፤ አለፍ ሲልም ሃሳብን በነፍጥ ለመጫን ማዳከር አንዱ የእኛነታችን መለያ ሆኖ ብዙ ዋጋ አስከፍሎናል፤ ዛሬም የሚታየው ሀቅ ይኸው ነው::

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ገና ወደ ሥልጣን እንደመጡ ኢትዮጵያ በአረንጓዴ ዐሻራ ዘመቻ 20 ቢሊዮን ችግኞችን ለመትከል ማቀዱን ይፋ ሲያደርጉ ከልቡ የተቀበለው ጥቂቱ ነበር፤ ለመዘባበት የሚሞክሩም ብዙ ነበሩ:: ሆኖም በመጀመርያ ዓመት ብቻ ከ 4 ቢሊዮን በላይ ችግኞችን በመትከል እንዲሁም በአንድ ጀንበር ደግሞ ከ350 ሚሊዮን በላይ ችግኞችን በዘመቻ በመትከል ኢትዮጵያ ታሪክ ጻፈች::

በቅን አሳቢ ኢትዮጵያውያን በተደረጉ ጥረቶችም እስከ አምና ድረስ 32 ነጥብ 5 ቢሊዮን በላይ ችግኞችን ማስተከል ችለዋል:: አምና በአንድ ጀንበር 569 ሚሊዮን ችግኝ በመትከልም ኢትዮጵያውያን በዓለም መድረክ ፋና ወጊ መሆን ችለዋል::

ጉዳዩን በቅርብ የተረዱ ወገኖች በጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ መሪነት የሚካሄደውን፣ የአረንጓዴ ዐሻራ እንቅስቃሴ ዘመቻን የሚደግፉ ሰዎች፣ የችግኝ ተከላው የሀገሪቱን የአረንጓዴ እጽዋት ሽፋንን እንዳሳደገ፣ የአየር ንብረት ለውጥን እየተከላከለ እና የሰዎች ሕይወት ላይ ለውጥ እያመጣ መሆኑን ቢናገሩም አብዛኞቹ የፖለቲካ ፓርቲዎች ለዚህ መልካም ሥራ ብዙም እውቅና ሰሲሰጡ አልታዩም።

እነዚህ የፖለቲካ ፓርቲዎች ከተቋቋሙ ጊዜ ጀምሮ ኢትዮጵያ በተደጋጋሚ በድርቅ ስትጎዳ ተመልክተዋል:: ድርቅ በየአመቱ እየደጋገመ እየመጣ በርካቶችን ከአካባቢያቸው ሲያፈናቅል፤ ሲያሳደድና ሰዎች በርሃብ ሲሞቱ ተመልከተዋል:: ሆኖም የእኛዎቹ የፖለቲካ ፓርቲዎች ችግሩን ቁጭ ብሎ ከመመልከት ወይንም ደግሞ ወቃሽ ከመሆን ድርቅን በዘላቂነት ለመፍታት የሚቻልበትን አማራጭ ሲጠቁሙ አይታዩም::

አለፍ ሲልም ያላቸውን ዕውቀትና የአባላት ብዛት በመጠቀም አስተባብረው ችግኝ ሲተክሉ አይታዩም:: አረንጓዴ ዐሻራ መትከል በጎ ፍላጎትንና ቅን አሳቢነትን እንጂ ሥልጣንን ወይንም ገንዘብን አይጠይቅም:: ስሙ እንዲህ የሚባል ፓርቲ አባላቱን አስተባብሮ ይሄን የሚያክል ችግኝ ተከለ የሚባል ዜና የምንሰማው መቼ ይሆን?

በተመሳሰይም አንድ ፓርቲ አባላቱን አስተባብሮ የድሃ ቤት ማደስ ለሀገር ለወገን ማሰብን እንጂ የተለየ ጥበብን አይጠይቅም:: እንዲሁ ለአፍ እና ለፖለቲካ ፍጆታ ብቻ ለድሃው የቆምኩ ነኝ የሚለው ፕሮፓጋንዳ ትዝብትን ከማትረፍ ውጪ የሚያስገኘው ፋይዳ የለም::

ኢትዮጵያውያን ተፈጥሯዊም ሆነ ሰው ሰራሽ ችግሮች ሲያጋጥማቸው በመረዳዳትና በመደጋገፍ የማለፍ ጥበብን የተለበሱ ሕዝቦች ናቸው:: በርሃብም ሆነ በድርቅ፤ በግጭትም ሆነ በጦርነት ወቅት በመረዳዳት አስከፊ ጊዜያቶችን አሳልፈዋል::

ኢትዮጵያውያን ዘር ፣ ቀለምና ኃይማኖት ሳይለዩ የተቸገረን መርዳት፣ የተራበን ማብላት፣ የተጠማን ማጠጣትና የታረዘን ማልበስ ያውቁበታል:: እንኳን እርስ በእራሳቸው ይቅርና ባህር አቋርጦ፣ ድንበር ተሻግሮ ለመጣ ስደተኛ ጭምር በራቸውን ክፍት አድርገው ፣ ያላቸውን አካፍለውና ፍቅር ለግሰው ማኖር የሚችሉ ሕዝቦች መሆናቸውን በርካታ የታሪክ መዛግብት የሚያወሱት ሃቅ ነው::

ይህ የመተሳሰብ ፣ የመረዳዳትና የመደጋገፍ እሴት በተለይም ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ተጠናክሮ ቀጥሏል:: በተለይም አቅመ ደካማ ለሆኑ ዜጎች ማዕድ ማጋራትና ድሃ ድሃ ቤት እድሳት በዚህ ረገድ ተጠቃሾች ናቸው::

በየዓመቱ ክረምት በመጣ ቁጥር የበርካታ አቅመ ደካማ ቤቶች እየታደሱ ከዝናብና ከጎርፍ ለመታደግ ብዙ ጥረቶች እየተደረጉ ነው:: በዚህም በርካቶች ከስቃይና ከመከራ ተላቀው በጎ አድራጊዎችን ሲያመሰግኑና ሲመርቁ ተሰምተዋል::

በየዓመቱም ክረምት በመጣ ቁጥር የበርካታ አቅም ደካማ ዜጎች ቤቶች እየታደሱ ዜጎችን ከዝናብና ከብርድ የመታደጉ ተግባር በመንግሥት፤ መንግሥታዊ ባልሆኑ ድርጅቶችና በነዋሪው ተሳትፎ እውን እየሆነ ነው::

በዚህ በጎ ፈቃድ ሥራ ውስጥ በርካታ ወጣቶችና ሴቶች አለፍ ሲልም በጎ አድራጊ ባለሀብቶች ሲሳተፉ ቢታዩም ፖለቲካ ፓርቲዎቻችን ግን ከሰልፉ ውስጥ አልታዩም:: በተለይም ተወዳድረን፤ ሥልጣን ይዘን ፤ ሀገር እንመራለን የሚሉ የፖለቲካ ፓርቲዎች በጎነታቸውንና ለሀገርና ለወገን ያላቸውን ተቆርቋሪነት ማሳያው ጊዜ አሁን ሊሆን በተገባ ነበር:: ግን በእድሉ ሲጠቀሙ አይታዩም::

በሌላም በኩል በአቅም ማነስ ምክንያት በቀን አንድ ጊዜ እንኳን እራሳቸውን መመገብ የማይችሉ ዜጎችን በጋራ ማእድ እንዲቆርሱ በማድረግ ረገድ የተጀመሩት በጎ ተግባራት የኢትዮጵያውያንን በጎ እሴቶች ማስቀጠያዎች እየሆኑ ነው:: በበጎ ፈቃድ ወጣቶች ጭምር የሚከናወኑ የማዕድ ማጋራት በጎ ሥራዎችን ለተመለከተ በኢትዮጵያውያን መካከል ያለውን መተሳሰብና መረዳዳት የሚያመላክት ነው:: እዚህስ ላይ የፖለቲካ ፓርቲዎቻችን የታሉ?

የፖለቲካ ፓርቲዎች መሠረትና ህልውና ወጣቱ የህብረተሰብ ክፍል ነው:: ወጣቱን ያልያዘ የፖለቲካ ፓርቲ ቀጣይ ሕይወት አይኖረውም:: ሆኖም አብዛኞቹ የፖለቲካ ፓርቲዎቻችን ወጣቱን በስሜት ከመቀስቀስና መንግሥት ላይ ከማነሳሳት በዘለለ ዘላቂ የሆነ መርሃ ግብር ቀርጸው የወጣቱን ሕይወት ለማሻሻል ሲጥሩ አይታዩም::

በአሁኑ ወቅትበ ወጣቱ በመጤ ባህሎችና በአጓጉል ሲሶች እየተጠቃ ይገኛል:: ይህ ደግሞ የነገ ሀገር ተረካቢ ብለን በየመድረኩ የምናነሳውን ወጣት ሕይወት በእጅጉ የሚጎዳና ጦሱም ለሁላችንም የሚተርፍ ነው::

ነገር ግን የወጣቱ በሱስ ውስጥ መዘፈቅና በመጤ ባህሎች መመረዝ አሳስቦት እንቅስቃሴ ያደረገ ፓርቲ አላጋጠመኝም:: ቢያንስ ወጣቱ ከአጓጉል ሱስ እንዲጠበቅ ግንዛቤ የሚፈጥሩ የግንዛቤ ማስጨበጫ መድረኮች ማዘጋጀትና ወጣቱ ላይ ንቃት መፍጠር የተለየ ክህሎት የሚጠይቅ አይደለም::

በተመሳሳይም ስለሚደፈሩ ሴቶች መከራከርና ጥብቅና መቆምም የእነዚሁ የፖለቲካ ፓርቲዎች አንዱ መለያ መሆን ነበረበት:: እዚህ ጉዳይም ላይ አልፎ አልፎ ከሚሰነዝሩት ትችት በስተቀር የሴቶችን መደፈርና ሠብዓዊ መብት መከበር በተመለከተ በተገኘው አጋጣሚ ሁሉ ጥረት ሲያደርጉ አላየናቸውም::

የኑሮ ውድነቱን ከፖለቲካ ፍጆታ ነጥሎ በመመልከት አባላቱን አስተባብሮ የሰው ኑሮ የሚቀነስበትን መላ መዘየድ እና ተግባራዊ እቅስቃሴ ማድረግስ እንደ ኒዩክለር ሳይንስ የከበደው ለምንድን ነው ?

ስፖርትና መዝናኛ

# የዘመን ጥበብ

## ቤኒ ሀርሻው በዙምባራ

ሙሉጌታ ብርሃኑ

ጥበብ እግሯ ረዥም፣ እጇቿ ለግላጋ፣ ጣቶቿም አለንጋ ናቸውና ከወዴት ታደርሺኝ አይባልም:: መድረስ ስንፈልግ ማድረሻዋ እልፍ ነው:: ዛሬን ወደ የኛዎቹ የምእራብ ፈርጦች (ምእራብ ኢትዮጵያ) መንደር በዘመን ጥበብ ሠረገላ ብንፈረጥጥ ጎልቁ መሳፍርት ጥበባት ከአበባ እቅፍ ጋር ቆመው በክብር ይቀበሉናል:: እናስ ለማን ብለን እንቅር ... እንሄዳለን እንጂ:: ጢም ካለው ባህል ጢቅ ያለ ጥበብ እያነሱ ማየት ስንፈለግን ሊያሳዩን፣ መስማት ስንፈልግም ሊነግሩን ብዙ አላቸው:: ጥበብ እየቀዱ ጥበብ ቢያጠጡን እንሰክር እንደሆን እንጂ በቃኝ፤ ጠገብኩ አንልም:: አብረን በፈሰስን ቁጥር ሁሉ እነርሱ ብቻም ሳይሆኑ እኛም ከውስጣቸው የተቀዳን ስለመሆናችን እናጤነዋለን:: ከጥበባቸው ጥበብን ከፍቅራቸው ኢትዮጵያዊነትን ነስተን እንወጣለን:: ሀገራችን የባለ አራት የሙዚቃ ቅኝቶች እናት ብትሆንም፤ ቅሉ ግን ብቻቸውን አስቀረናቸው እንጂ ብቸኛ አይደሉም:: ያወቅነው ጥቂት የማናውቀው ግን ብዙ ነው:: ገና ብዙ ያልታወቁና ያልተነገረላቸው የጥበብ ማድጋዎች በየማኅበረሰቡ ጓሮ ውስጥ ተቀብረው ይገኛሉ:: ጥያቄው ግን ማንስ ቆፍሮ ያውጣቸው? ያው እኛው ... እኛው እራሳችን ነን እንጂ ሌላ ማንንስ ልንጠብቅ...ቆፍረን ያገኘናቸው ዕለት ከወርቅ አልማዝ የገዘፉ ማዕድናት ስለመሆናቸው እንረዳለን:: ከብዙ ጥቂቱም እዚህ ናቸው፤ እዚያ በቤኒሻንጉሎቹ መንደር ውስጥ ማለት ነው::

ከዚያ ከጠረፍተኞቹ ዓለም ውስጥ ያልታዩና ያልተሰሙ በርካታ የጥበብ ፕላኔቶች አሉ:: ያልተማሩ፣ ገና ያላወቁ ቢመስሉንም ሕይወታቸውን ግን ለጥበብ የውል ቃልኪዳን አድርገው አስረዋታል:: እናም ጥንትም ዛሬም የሕይወት እስትንፋሳቸው ያለዚህች ነገር ለመኖር አትችልም:: ከእያንዳንዱ እንቅስቃሴያቸው ጀርባ ጥበብ በአክናፏ ትረብብባቸዋለች:: እንደ ህጻን ልጅ ያስፈነድቋታል:: ከሀገራችን ደረት ላይ ልጥፍ እንዳሉ ከጡቶቿ ላይ ወተቷን እየማጉ ከውብ የተፈጥሮ ልምላሜ ጋር ኖረዋል:: ባንመለከታቸውም የጥበብን ማድጋ እየሞሉ እልፍ ዘመናትን ተሻግረው፣ በእልፍ የዘመን ቅኝት ውስጥ ተጠበው ዛሬም ይኼው አቲቲሽ... አጹንጹኝ ይሉናል:: እነርሱ መንደር ውስጥ ለሙዚቃ ትንፋሽ አያጥርም፤ ምን በድባቴ ቢወቃ እንኳን ለጭፈራው ሰውነት አይለግምም:: ያላቸውንማ ማንስ ችሎ ይቆጥረውና...ዙምባራና አኖባ፣ አጸጸሁና ቢልተኛ፣ ቦሎና ነገራ፣ አለፌና ቁዋ፣ ሀርሻና ሂጸሌ ... ብሎ ጀምሮ መዝጊያ መንገዱ ይጠፋልና ከዚያማ ተደምሞ ዝም ማለት ብቻ ...

ምን አለሽ ቤኒሻንጉል? ከማለት የሌላትን መጠየቁ ይቀላል:: ወዲያ ግድም ሲያቀኑማ ጥበብ ከሙዳይዋ፣ ተፈጥሮም ከምድር ገጸ በረከቷ አትሰስትም:: ለጋስ ሕዝብ፣ ትኩስ ጥበብ፤ ሀድራው የተዋበ ምድረ ገነት ... ከእነርሱ መንደር ጎራ ብለው ከዘለቁ ሥራ መዋያው፣ ጥበብም ማደሪያው ነው:: ሥራና ኪነ ጥበብ ትቅፍቅፍ ብለው ፍቅርን ይሠራሉ:: ማኅበረሰቡ ብዙ ነው፤ በእያንዳንዱ ልብ ውስጥ ግን የእነኚህ ሁለት ነገሮች ኮከብ ገጥሞ አንዱን ያለ አንዱ ለማሰብ አይሞከርም:: የልባቸው ወርቅ አልፎም ከከርሰ ምድራቸው ላይ ተቆልሏል:: ቤኒዎቹ በጥበብ የሚፈሱበት ረዥም ቅጽበት አንድም የዚህን ጊዜ ነው ... የከርሰ ምድሩን የድንጋይ ወርቅ ለማውጣት የልባቸውን የጥበብ ሙዳይ ያንጠለጥሉታል:: ሃይለኛው ብረት በእሳት ወላፈን እንደሚቀልጥ ሁሉ ጥበብም የወርቅ ቁፋሮውን የብርታት መንገድ እየከፈተ ጋሬጣውንም አለት አንከባሎ ወዲያ ያሽቀነጥርላቸዋል:: ወርቁም ይህን የጥበብ አጀብ ለምዶ እንዲሁ በዋዛ የሚወጣ አይመስልም:: የጥበብን ወርቅ እየሰጡ ከአፈሯ የድንጋይን ወርቅ ይቀበላሉ:: ተፈጥሮን በጥበብ ያጌጠ እንደ እነርሱ ማን አለና ...

ቤኒሻንጉል ሲሉ አንድ ዓይነት ጥበብ፤ አንድ ዓይነት ማኅበረሰብ ብቻ አይደለችም:: ቤኒሻንጉል ጉሙዝማ ... በዋልታና ካስማ የቆመች፣ በማገርና ወጋግራ የታጠረች፣ በጥበብ ምሰሶ ተቃኝታ በኢትዮጵያ ጡቶች መሃል የተንፈላሰሰች ዋርካ ናት:: ኢትዮጵያዊ መልክን ሰጥቶ ከጠረፏ ጋር ቢያውዳት ጊዜ ብዙ ሳለች ተፈጥሮና ፍቅር በአንድ ኩለው እንደ አንድ አሳመሯት:: አምስቱም ማኅበረሰብ እንደ ገመድ ተጋምደው ውብ መልክና እጹብ አንድነትን ፈጥረዋል:: ጉሙዝ፣ በርታ፣ ሽናሻ፣ ማኦ እና ኮሞ በቤኒሻንጉል ልምላሜ ቆመው ለጥበብ እንኮይን ያረግፉላታል:: የሙዚቃ መሳሪያዎቻቸውን በፍቅር ህብረ ቀለማት ነክረው የሀገራቸውን የጥበብ ጥለት በወርቃማ ሸንተረር እያሸመኑ ከአይንና ከጆሮ በላይ የሆነውን ሳምራ ውበት ይኖሩታል:: ባህላቸው ብዙ ኪናዊ ጨዋታና ሙዚቃዎቻቸው ደግሞ ውለው አድረው እየሰሙት ቢከርሙበት በሀሴት ነብስን ያስታል እንጂ በቃኝ ብለው የሚጠግቡት አይደለም:: በአምስቱም ማኅበረሰቦች



ውስጥ ጥበብ የሕይወት እስትንፋስ ልኬት እንጂ ማድመቂያ ብቻ አይደለም:: እንደ አንድ የሚጠቀሟቸው ባህላዊ የትንፋሽ ሙዚቃ መሣሪያዎች በርካታ ቢሆኑም በተናጠል ደግሞ መታወቂያቸው የሆነ አንድ ወይም ከዚያ በላይ ይኖራቸዋል:: በየአካባቢዎቻቸው የሙዚቃና መሰል ጥበባት እንደ እጣን ጢስ እየተንቦለቦሉ መዓዛቸው ከሩቅ የሚጣራበት ጊዜም እንዲሁ አለ::

ልክ የክረምቱ ወራት ሲቃረቡ ቤኒዎቹ ከሙቼውም በላይ በጥበብ ዝናብ ይረሰርሳሉ:: ሰማይ ከላይ የደመና ጭጋጉን ለብሶ በመብረቅ ጉምጉምታ ድባቅ ሲያስመታ እነርሱ በዙምባራ ያጅቡታል:: የሚያስደነግጠውን ድምጽ በዜማ እያነኮሩ ወደ ውብ የዜማ ስልት ይቀይሩታል:: ለመውረድ አንድ ሁለት እያለ ጉምጉም ከሚለው የክረምት ዝናብ አስቀድሞ ለቤኒ ማህበረሰብ ታላቁ የሥራ ጊዜያቸው ነው:: ከማሳው እርሻቸውም ሆነ ከጋጥና ጉረኖው ከብቶቻቸው ጋር የዚህን ጊዜ የተለየ ቀጠሮ አላቸው:: ሁሉም በየፊናው ለሥራው ይሯሯጣል:: ምንም ይሥሩ ምን ያለሙዚቃና የሙዚቃ መሣሪያዎቻቸው ግን እንኳንስ እጅና እግራቸው ልባቸውም አይነሳም፤ ሃሳባቸው እሺ ብሎ ቀልባቸውም አይሰበሰብም፤ ገና ሳይጀምሩት ጉልበታቸው ዝሎ ሁለንተናቸው የሚለግም መስሎ ይሰማቸዋል:: ዘሩን ዘርተው አዝመራውም ሲያሸት ምርቱን ወደ ጎተራው ሲያግዙ ቆሚያ እየተነፋ ዜማው ወርዶ ጭፈራውም ይደራል:: ታዲያ በዚህ ሁሉ ግብር መሀል ለእነርሱ እንደ አበረታች መድሃኒት እየሆኑ ለጉልበታቸው ማንቂያ መቀስቀሻ ደወል እኚሁ በግጥምና ዜማዎች የሚታጀቡት የሙዚቃ መሣሪያዎቻቸው ናቸው:: በዚህ ጊዜ በዋናነትም ዙምባራ ይገኝበታል:: እንደሊማሊሞ ዋሻ ክብልል ብሎ ከአፍ እስከ ቁርጭምጭሚት የሚምዘገዘውን ያን ረዥም ዋዛ ከአፋቸው ላይ ደግነው ከትንፋሻቸው ጋር ሲያዋህዱት ድምጹ ኩልል እያለ ይፍለቀለቃል:: ልክ የዙምባራን ድምጽ የሰሙ ጊዜ ነብሳቸው ከሞት መሀከል ፈልቅቃ ወደ ገነት ትነጥራለች:: ከባህላዊ ግጥሞቻቸውና ዜማዎቻቸው ጋር እያማሰሉ ሲያዋህዱት ደግሞ በቃ የሥራ ወኔያቸው እየገነፈለ ድካምና ድባቴዎቻቸውን ወደ እንጠረጦስ ያወርደዋል::

ከምስራቃዊ የሱዳን ጎድን ከሆነው የየገሪን ተራራማ ስፍራ ተነስተው እስከ ዓባይና ዳቡስ ሸለቆዎች ድረስ ተንሰራፍተው ከዝንተ ዓለሙ የኖሩት ጉሙዞቹ (የቀድሞዎቹ በርታዎች) ለባቡሩ እንደምትነጠፍ ሀዲድ እንግዳ ለመቀበል የእነርሱም ልብ በረዥሙ ትዘረጋለች:: አመለ ወርቅ ናቸውና ከላይ ከጸባኦቱ ምድራቸውን በወርቅ ማዕድን አንቆጥቁጦታል:: በዙምባራ የዜማ ደሴት እያዞነበሩ ይህንንም ያንንም ደስታቸውን ያጣጥሙታል:: ከጉሙዝዎቹ የደስታ ደሴት ውስጥም ሁሌም በየትኛውም ጊዜና ቦታ ዙምባራ የተሰኘው የትንፋሽ የሙዚቃ መሳሪያቸው አለ:: ሁለት ክዋክብት በፍቅር ትዳር ገጥመው ሠርግና ምላሹን በፌሽታ ሲራጬበት ትንፋሻቸውን ከጥበብ ማሰሮ ውስጥ እየሳቡ በዙምባራው ጨረቃን ለምድር ያቀርቧታል:: ዙምባራም ያለ ህብራዊ አንድነት ተነጥሎ ለብቻ አይሆንለትም:: ትክክለኛውን የዙምባራ ጣፋጭ ድምጽና ዜማ ለማግኘት በአንድ ሆነው ጥምረት የፈጠሩ 12 አባላት ያስፈልጉታል። አሊያ ግን የዜማ ምቱ ተጓድሎ ውበቱ ይጠፋል:: አንዱ ቢጎድል አንድ አካል የጎደለ ያህል ነውና ትርጉም የማይሰጥ ጩኸት ብቻ ይሆናል:: የሙዚቃ ጠበብቱ የዙምባራ ሊቆች ያልተነገረለትን የዜማ ቀመር ቀምረው በአሥራ ሁለት የትንፋሽ ውህደት ላይ አሳርፈውታል:: የቤኒዎቹ በርታዎች ሴቶቹ ቶብ፤ ወንዶቹ ደግሞ ጀለቢያቸውን ለብሰው በሠርግና በዓላቱ ሁሉ ከአንድ የሙዚቃና የባህል ጨዋታ ላይ ሸር-ብትን ሲሉ መመልከትማ ማንነትን ያስረሳል:: ገንፎውንና ቄንቄሱን ከሸከላው፣ ጥበብን ከዙምባራው እያነሱ ጠግበው ያጠግባሉና ከእነርሱ ጋር ዘላለምን ያስመኛሉ::

ቤኒ ቤኒሻንጉል ብለው ከሮጡማ መንገዱ ወደ ጀግናዎቹና ጎበዛዝቱ የጉሙዝ ቁልቁለት ያደከድከናል:: መሄድ፣ መሮጥ ያስመኘናል:: ደርሰው የተመለከቷቸው እንደሆነ ባህላዊ የፍቅር ጥበብና የአኗኗር ዘያቸው ከዓይንና ልባችን ላይ ያበራል:: የልባችንን ጽለመት ገፎ ጸአዳውን የሕይወት ነጠላቸውን ያከናንበናል:: ድንገት ከተፍ ስንል፤ ጠላት አልፎ ከግዛት ላይ ሲገባ እንደሚጎሰመው ያለ የነጋሪት ድምጽ አያሰሙንም:: ይልቅስ ቆሚያቸውን ብድግ አድርገው በአፋቸው ትንፋሽ ልባችንን በፍቅረ ጥበብ ይማርኩታል:: የስሜት በራችንን በርግደው በደስታ ሀሴት ይሞሉናል:: በምን ካልን ደግሞ፤ ቆሚያ በተሰኘው ባህላዊ የትንፋሽ መሳሪያቸው ... በጉሙዞቹ መንደር ውስጥ የቆሚያ ድምጽ ሳይፍለቀለቅ ጀንበር ወጥታ ጀንበር አትጠልቅም:: በርከት ያሉ ባህላዊና መንፈሳዊ ክብረ በዓላትን የሚያዘወትሩት ጉሙዞቹ፤ ከእነዚህ ትውፊታዊ ክዋኔዎቻቸው መሳ ለመሳ ቆሚያ የነብስ አዱኛቸውን እየሰበሰበ የሕይወትን ዜማ ያዜምላቸዋል:: ለሙዚቃ መሣሪያው ያላቸው ክብር ገዘፍ ያለ በመሆኑ እንደተፈለገው በየትኛውም ሰዓት ማንም እየተነሳ አይጫወተውም:: የተቀመጠለት የራሱ የሆነ ጊዜና ቦታ አለው:: በብሔረሰቡ ውስጥ ትልቅ ስምና ዝና ያለው ሰው ሲሞት ቆሚያ የነጠላውን ጥለት ሸቅብ ሰቅሎ ይነሳል:: የዘመን መለወጫን ጨምሮ ልዩ ልዩ ክብረ በዓላት ሲኖሩም ድምጹ እረፍት አይኖረውም:: ከዚሁ ጎን ለጎን ደግሞ ሌላ የጥበብ ጽላሎት አላቸው:: ለሙዚቃዊ ጭፈራና ጨዋታው ማድመቂያ በሴቶቹ እግር ላይ ኤፂፃ ይታሠራል:: የጉሙዝ ሶታና ኮረዳ አንዴ ከጥበብ ትንፋሽ የሳቡ እንደሆን መላው እንቅስቃሴዎቻቸው ሁሉ ባህል ጥበብ ... ጥበብ ሙዚቃ ... ሙዚቃና ጨዋታ ነው::

ሴቶቹ ጨፋሪዎች ኤፂፃን እንደ እግር አልቦ ከቁርጭምጭሚታቸው አካባቢ በማሰር ዘለል ✦ ✦ ✦ ዘለል ✦ ✦ ✦ እያሉ እግራቸው ከመሬት ተነስቶ ወደ መሬት በተመለሰ ቅጽበት ሁሉ ልዩ ህብረ ዜማዊ የሙዚቃ ድምጽን ይፈጥራሉ:: ድምጹም ጽናጽል ከሚሰጠው ድምጸት ጋር ተመሳሳይነት ያለው ነው:: በብዛት ሴቶቹ ቆመው የሚታዩት በሁለት ረድፎች ለሁለት ሁለት በመጣመር ሲሆን፤ ይህ ደግሞ ሌላኛው ያልተመለከቱት የኬሮግራፊ ጥበባቸው ነው:: ትዕይንቱ ሲጀምር ተወዛዋዦቹ የድምጻዊውንና የቆሚያውን የሙዚቃ ምት እየጠበቁ ዘለል ዘለል በማለት በሆድ አሊያም በደረት ይነካካሉ:: ከስር ቅጭል! ቅጭል! ክሽ! ክሽ! የሚለው ኤፂፃው ደግሞ ውበትና ድምቀቱን ያፈካዋል:: በጉሙዞቹ ሰማይ ላይም ማራኪው የባህል ጥበብ ከምድር ሽቅብ እንደ እንፋሎት እየተንፎለፎለ ህብረቀለማዊ የጥበብ ቀስተደመናን ሠርቶ እየተዥጎረጎረ ያብረቀርቀዋል::

የዓባይን ወንዝ ሰማያዊ ጢስ እየተከተሉ በጉም በደመናው መሀል ከቀዘፉ መሄድን እንጂ መመለስን አያስመኝም:: ከወርቃማው የጉም ጢስ መሀል እልፍ ሆነው ለመጀመሪያ ጊዜ እየተመሙ ሲታዩማ ሺህ ናቸው ስለተባለላቸው ስለ ሺናሻዎቹ የጥበብ በረከት ካላነሱማ ምኑን አወሱ... "ሺኒ" የመጀመሪያ ወይም ቀደምትነትን የምታመለክት የእነርሱው ቃል ናት:: "አሻ" ማለት ደግሞ ሕዝብ ነው:: ቀደምቱ ሕዝብ ምንስ ጥበብ ይኖራቸው ይሆን ... እነዚህም በበዓላት ጊዜ ልዩ ትውፊታዊ የጥበብ ክዋኔ አላቸው:: በበዓሉ ቀናትም ዘመድ፣ ወዳጅና ጎረቤቱ ተሰባስቦ ጭምቦ የተሰኘውን ምግባቸውን ሲመገቡ በቦርዴ ጠላው ብቻ አይወርድላቸውም:: ይልቅስ የገበታውና የጨዋታው ማንሸራሸሪያ፤ ሙዚቃና ጥበባዊ ትዕይንት የተሞላበቱ ጭፈራ ነው::

አራተኞቹን የጥበብ ፈርጦች ፍለጋ ለወጣ አቅጣጫውን ተከትሎ በመሄድ ከሱዳን ድንበር አካባቢ ደርሶ ቆም ብሎ ማሰብና ማነፍነፍ ይጠበቅበታል:: የዚያን ጊዜ የኦሮሚያን ክልል ተዋስነው የሚገኙት የማኦዎቹ ገዳሾላና ሸጎጎና፣ ጫንጋላና ፓሽማ፣ ውስኩና ሸንታ በፍቅር እቅፍ ጥበብ ይቀበሉናል:: እነዚህኛዎቹ በየጊዜው ከተፍ እያሉ የጥበብን ጮቤ የሚያስረግጧቸው ፌስቲቫሎቻቸው በርከት ያሉ ናቸው:: እጅን ከጥበብ ላይ አሳርፈው የሚሠሯቸው የእደጥበብ ሥራዎቻቸው አካል ሰውነታችንን እያሞቀ በውበት ወላፈን ያቀልጠናል:: በሥጎቻቸው ላይ የመታደምን ዕድል ያገኘን እንደሆነማ ሙሽራይቱ እራሷ ጥበብ ስላለመሆኗ እርግጠኞች አይደለንም:: በጺል ጌጣጌጥና በጨሌዎች አምራና አሸብርቃ የጨረቃን እኩሌታ ከመሰለችው ሙሽሪትና ከጎምላሌው ሙሽራ ዙሪያ የሚከወኑት ትውን ጥበባት መደነቅ ያንሳባቸዋል:: ባህላዊ የሠርግ ዘፈኖቻቸውን መስማት ያነሆልላል:: የጭፈራ ስልታቸው ሲታከልበት ደግሞ አቧራው ብቻውን አይጨስም:: ወንዞች ሽቅብ እየፈሰሱ ፏፏቴዎች እንደ ሰው ቆመው ያጨበጭባሉ፤ ሳር ቅጠሉ ሁሉ ከንፋሱ ጋር እየተውረገረጉ በኬሮግራፊር ተጠንቶ የተሰናዳ የሚመስል የዳንስ ስልት ያሳያሉ፤ የሚንቀለቀለው እሳት እንኳን ከቤኒዚን ጭዱ ጋር እየተስማማ ብርሃን ብቻ ይሆናል:: በእነርሱ ጥበብ፤ በእነርሱ ፍቅር የማይሆን የማይታይ የለም:: አምስተኛዎቹ ኮሞዎችም ሁሉንም ከሌሎቹ ጋር የሚጋሩ፣ በጎበዝ ገበሬ የተዘሩ ውብ አዝመራዎች ናቸው::

የሀገራችን የሙዚቃ ጥበብ ተዝቆ የሚያልቅ፤ ተነግሮም የሚያበቃ አይደለም:: ከፊት ዓይኖቻችን ላይ ያሉትን እንጂ ከውስጣችን እንደ ከርሰ ምድር ወርቅ ተቀብረው ያሉትን ገና ምኑንም አልነካናቸውም:: ሌላውን ሁሉ ትተን በዛሬውን ትኩርታችን የቆምነው በቤኒሻንጉል ጉሙዝ የባህል ሙዚቃ መሣሪያዎች መስታየት ፊት ቢሆንም፤ የተመለከትነው ግን ፊትን የመመልከት ያህል ብቻ ነው:: በአሁኑ ሰዓትም ካሏት የባህል ሙዚቃ መሣሪያዎች ሁሉ ዙምባራ ዘውዱን ጭኖ እናገኘዋለን:: በተባበሩት መንግሥታት የሳይንስ፣ የትምህርትና ባህል ማዕከል በሆነው በዩኔስኮ ተቋም ውስጥ ለማስመዝገብ ከሁለት ዓመታት በፊት የተጀመሩ እንቅስቃሴዎችም በሂደት ጉዞ ላይ ናቸው:: ቀጥሎም ሌላ ታላቅ የጥበብ መዝገብ እንከፍት ይሆናል::

ወርቃማዎቹ የጥበብ ጀልባዎች ከተለያዩ የሀገራችን ክፍሎች የተሰባጠሩ ብሔር ብሔረሰቦችን አሳፍረው "ቤኒ ቤኒ ... ቤኒ ሀርሻው ... አለፌ ቁዋ በዙምባራ" እያሉ ከዓባይ ወንዝ እስከ ስናር ሱዳንና መላው ኢትዮጵያ በፍቅር ይሽከረከራሉ:: ዓይን አይቶ ልብ ይፈርዳል፤ ሙዚቃዊ የጥበብ ማር ልውሳቸውን ግን ጆሮ ሰምቶና አጣጥሞ አይጠግበውም:: ከሙዚቃ መሣሪያዎቻቸው ጠብ እያለ የሚፈሰው ትኩስ የጥበብ ወተታቸው እንኳንስ ሌላውንና ቁሱንም ጾም ያስፈታል:: ሲያወሩም መሽቶ ይነጋልና ከብዙ ቃላት በጥቂቱ ይህችን ስንኝ ቋጥሬ ልቋጭ::

ወርቃ ድንቁን እዩ ከጉሙዝ-ከበርታ፤
በኮሞ ሺናሻ የጥበብ እንቢልታ፤
በማኦ ጠበብት ደጅ ጦማሩ ሲፈታ፤
ይኼኔ ነው ጀባው አኖባው ለማታ::
አጹንጹኝ አጸጸሁ በዙምባራ ቁዋ፤
አቲቲሽ አጀረግ ቢልተኛው መረዋ፤
ዜማው ስልቱ ሀርሻ ኮዎ በጉብልዋ፤
ደጭ! ደጭ! ማለት ነው ይዞ ጥበብ ጽዋ::

ማህበራዊ

# ልዩ ልዩ

## የኢትዮጵያ ባሕል ለስደተኞች የሕግ ማዕቀፍ

ዋለልኝ አየለ

ስደተኝነት (refugee) ዓለም አቀፍ ጽንሰ ሀሳብ ነው:: የተባበሩት መንግሥታት የስደተኞች ከፍተኛው ኮሚሽን እንደሚለው፤ ስደተኛ ማለት አንድን የተፈጠረ ችግር ለማምለጥ ሀገሩን ለቆ በመሄድ የተሻለ ሠላም ለማግኘት በሌላ ሀገር የሚኖር ማለት ነው:: በተባበሩት መንግሥታት በስደተኞች ጉዳይ ላይ እገዛ ማድረግ ከተጀመረ ከ70 ዓመታት በላይ ሆኖታል:: የስደተኞች ስምምነት (ኮንቬንሽን) በዓለም አቀፍ ደረጃ የተደነገገው እና ስደተኝነት የሕግ ማዕቀፍ ያገኘው ከ73 ዓመታት በፊት በአውሮፓውያኑ አቆጣጠር በ1951 ነው::

ከዚህ ሁሉ በፊት ኢትዮጵያ ምን ነበረች? የሚለውን እንመልከት:: ለዚህም የስደተኞችና ተመላሾች አገልግሎት በጥር ወር 2016 ዓ.ም ለመገናኛ ብዙኃን ባለሙያዎች ያቀረበውን ጥናት ዋቢ አድርገናል:: ተቋሙ በተለያዩ የዲጂታል አማራጮች ያሰራጫቸውን መረጃዎችን እና የተቋሙ ባለሙያዎች ያቀረቧቸውን ጥናቶች ዋቢ አድርገን የኢትዮጵያን የስደተኞች የሕግ ማዕቀፍ፣ እንዲሁም የኢትዮጵያ ባሕል በራሱ ለስደተኞች የሕግ ማዕቀፍ የተመቸ መሆኑን እንመልከት::

ኢትዮጵያ ስደተኞችን ተቀብሎ በማስተናገድ ረጅም ታሪክ ያላት ሀገር ስትሆን፤ በታሪክ በማሳያነት ከሚጠቀሱት ውስጥ በ7ኛው ክፍለ ዘመን የመጀመሪያዎቹ የእስልምና ተከታዮች በሃይማኖታቸው ምክንያት ወደ ኢትዮጵያ በስደት መምጣታቸው አንዱ ነው:: ይህ እንግዲህ ከአንድ ሺህ 400 ምናምን ዓመታት በፊት ማለት ነው:: በሌላ በኩል በመጀመሪያው የዓለም ጦርነት ወቅት ከእስያና ከአውሮፓ ስደተኞች ወደ ኢትዮጵያ መምጣታቸው፣ በአፍሪካ ሀገራት በነበረው የፀረ ኮሎኒያሊዝም ትግልና የእርስ በእርስ ጦርነቶች ከተለያዩ የአፍሪካ ሀገራት ስደተኞች ወደ ኢትዮጵያ መምጣታቸው ይገኙበታል::

በዚህም ኢትዮጵያ የረጅም ጊዜ ስደተኞችን ተቀብሎ የማስተናገድና በክብር ወደ ሀገራቸው እንዲመለሱ የማድረግ ታሪክ ውስጥ ያለባትን ኃላፊነት በመወጣት በዓለም አቀፉ ማኅበረሰብ ከፍተኛ አድናቆትንና ተቀባይነትን አግኝታለች:: ይህ የሆነው ደግሞ የማኅበረሰቡ ሥነ ልቦና እና ባሕል ለስደተኞችና ለተገፉ ሰዎች የሚሰጠው ቦታ ጥሩ በመሆኑ ለስደተኞች ከለላ ምቹና በስደተኞችም ተመራጭ እንድትሆን አድርጓታል::

እዚህ ላይ የኢትዮጵያን ባሕል ልብ ብሎ ማስተዋል ያስፈልጋል:: «ቤት ለእንግዳ ነው» የሚል የቆየ ባሕል አለ:: የሀገሬው ሰው «አልጋውን ለእንግዳ ለቆ መሬት ላይ ይተኛል» የሚለው በተደጋጋሚ የተገለጸና የታወቀ ነው:: በሃይማኖት እና በባሕል የተገነባው ሥነ ልቦናው ይህን ለማድረግ ያስገድደዋል:: የሞራል ልዕልና ፈጥሮለታል:: «እንግዳ መጣልኝ» የሚለው የሀገሬው ሕዝብ ሥነ ልቦና ጠንካራ ነው:: በቤቱ ውስጥ አለ የተባለውን ነገር ሁሉ ይጠቀማል:: ይህ ባሕል ነው ኢትዮጵያን በስደተኞች ተቀባይነት እንድትታወቅ ያደረጋት::

ለምሳሌ፤ በብዙ ሀገራት የዘረኝነት ጥቃቶችን እናያለን እንሰማለን:: ኢትዮጵያ ውስጥ ግን ቢያንስ የራሱ የእርስ በእርስ መነቋቆርና መጋጨት ቢኖርም የሌላ ሀገር ዜጋን የማጥቃት ልማድ ግን የለም:: ይህም ከራስ በላይ ሌሎችን የማክበር ሞራል ስላለ ነው:: እርስ በእርስ መነቋቆሩ ነውር ቢሆንም፣ ልናወግዘውና ልናስወግደው የሚገባ ቢሆንም፤ የሌላን ሀገር ዜጋ የማጥቃት ልማድ ግን የለም:: በዚህ ምክንያት ነው ኢትዮጵያ በስደተኞች ተመራጭ እና ተመስጋኝ የሆነችው::

ለመሆኑ በኢትዮጵያ በየትኞቹ አካባቢዎች ስደተኞች ይበዛሉ? የሚለውን የስደተኞችና ተመላሾች አገልግሎት መረጃን ዋቢ አድርገን ስናይ፤ በድንበር አዋሳኝ አካባቢዎች ባሉት ይበዛሉ፤ ይህም ነባራዊ ሁኔታው ያደረገው ነው::

ከስድስት ወራት በፊት (ታኅሣሥ 2016 ዓ.ም) በነበረው መረጃ፤ ከፍተኛው የስደተኛ ቁጥር ያለው በጋምቤላ ክልል ሲሆን፤ 385 ሺህ 205 ስደተኞች ይገኛሉ:: ሁለተኛው የሶማሌ ክልል ሲሆን፤ 310 ሺህ 411 ስደተኞች ይገኙበታል:: ሦስተኛው የቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል ሲሆን፤ 79 ሺህ 863 ስደተኞችን ይዟል:: መረጃው የአዲስ አበባን፣ አፋር ክልልን፣ አማራ ክልልን፣ ኦሮሚያ ክልልን እና የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልልን የያዘ ሲሆን ዝቅተኛውን የስደተኛ ቁጥር የያዘው የትግራይ ክልል ነው፤ 2 ሺህ 37 ስደተኞችን ይዟል:: ከክልሎች በተጨማሪ ደግሞ በተበታተኑ አካባቢዎች የሚኖሩ 14 ሺህ 909 ስደተኞች አሉ:: የስደተኞችና ተመላሾች አገልግሎት ይህን መረጃ ሲሠራ ዋቢ ያደረገው የተባበሩት መንግሥታት የስደተኞች ከፍተኛ ኮሚሽንን ነው::

ለመሆኑ ስደተኞች በብዛት ከየትኞቹ ሀገራት የሚመጡ ናቸው? የሚለውን ስንመለከት ደግሞ በብዛት ከአጎራባች ሀገራት የሚመጡ ናቸው:: ከፍተኛውን ቁጥር የሚይዙት የደቡብ ሱዳን ስደተኞች ሲሆኑ፤ 43 በመቶ የሚሆነውን ቁጥር ይይዛሉ:: በሁለተኛ ደረጃ የሶማሊያ ስደተኞች ሲሆኑ፤ 32 በመቶ ድርሻ አላቸው:: ሦስተኞቹ ኤርትራውያን ሲሆኑ፤ 17 በመቶ ናቸው:: ከሱዳን፣ ከየመን እና ከሌሎች ሀገራት የሚመጡ ስደተኞችም ተመዝግበዋል::

አኃዛዊ መረጃዎችን ማስቀመጥ የፈለግንበት ምክንያት ነባራዊ ሁኔታውን ስለሚያሳይ ነው:: ለምሳሌ፤ ወደ ጋምቤላ የሄደ ሰው የስደተኞች መጠለያ ካምፕ ሲያስተውል ለምን እዚህ አካባቢ በዛ? የሚል ጥያቄ ሊፈጠርበት ይችላል:: ነባራዊ ሁኔታው ግን ለደቡብ ሱዳን አዋሳኝ ስለሆነ ነው:: በመረጃው ላይ እንደታየው የደቡብ ሱዳን ስደተኞች ይበዛሉ:: ከኢትዮጵያ አካባቢዎችም በጋምቤላ ይበዛል ማለት ነው:: የዕድሜና የፆታ መረጃዎችን እንተዋቸውና ቁጥሩ ግን የሀገሬው ሰው በዓይኑ የሚያየውን እውነታ ያሳያል ማለት ነው::

ለምሳሌ፤ ብዙ ሰው የየመንና የሶሪያ ስደተኞችን በአዲስ አበባ ውስጥ ያስተውላል:: መረጃው እንደሚያሳየውም፤ ከሶርያ፣ ሊቢያ፣ ኢራቅ፣ ሊባኖስ፣ ኮንጎ፣ ሩዋንዳ፣ ቡሩንዲ፣ አፍጋኒስታን፣ ፍልስጤም፣ ጅቡቲ፣ ዮርዳኖስ የመጡ ስደተኞች ይገኛሉ::

ለእነዚህ ስደተኞች፤ የስደተኞችና ተመላሾች አገልግሎት ተቋም በጋምቤላ ክልል 6፣ በትግራይ ክልል 2፣ በአማራ ክልል አንድ፣ በአፋር ክልል 2፣ ኦሮሚያ ክልል 2፣ በቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል 3፣ በሶማሌ ክልል 8 እና በደቡብ ኢትዮጵያ ክልል አንድ፤ በአጠቃላይ 25 የስደተኛ መጠለያ ጣቢያዎች በማቋቋም እንዲሁም የከተማ ስደተኞችን በአዲስ አበባና ሌሎች ከተሞች የሚኖሩ ስደተኞች ያስተዳድራል::

ኢትዮጵያ የ1951 የስደተኞች ኮንቬንሽንን እንደ አውሮፓውያኑ የዘመን ቀመር በ1969 በማፅደቅ የሀገሪቱ የሕግ አካል አድርጋለች:: ነገር ግን ስምምነቱን ስታፀድቅ የመጀመሪያ ደረጃ የትምህርት ዕድል እና የቅጥር ሥራ ላይ መሰማራትን በተመለከተ ገደብ አስቀምጣለች:: በተመሳሳይ የ1969 የአፍሪካ የስደተኞች ኮንቬንሽንን በመፈረምና በማፅደቅ ስምምነቱ የሚያስቀምጣቸውን የአፍሪካ የተለዩ የስደት ሁኔታዎችን የሀገሪቱ ሕግ አካል አድርጋለች::

ከላይ የተገለፁትን ዓለም አቀፍና አሕጉራዊ የሕግ ሰነዶችን በሚገባ ሥራ ላይ ለማዋል ብሔራዊ ሕግ በማውጣት ሕጋዊና አስተዳደራዊ መዋቅር በመመስረት ስደተኞችን በመቀበል፣ ደኅንነታቸውን መንከባከብና በተቻለ መጠን የዘለቄታዊ መፍትሔ የሚያገኙበትን ሁኔታ ማመቻቸት አስፈላጊ በመሆኑ የስደተኞች ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 409/1996 በማውጣት ስትሠራ መቆየቷ ይታወሳል::

ሆኖም አሁን በዓለም አቀፍ ደረጃ የስደተኞች ድጋፍ ሁኔታ ላይ ባጋጠሙ የተለያዩ ችግሮች የተነሳ የሚገኘው ድጋፍ መጠን በከፍተኛ ሁኔታ በመቀነሱ በገባቻቸው ዓለም አቀፍ ስምምነቶች ውስጥ የተቀመጡ የስደተኞችን መብቶች በተሻለ የሚያስከብርና ከለላ የሚሰጥ እንዲሁም ለችግሮቻቸው ዘላቂ መፍትሔ እንዲያገኙ የሚያስችል በዓለም አቀፍ መመዘኛዎች መሠረት የተሟላ የሕግ ማዕቀፍ በማስፈለጉ፤ በአዲስ መልክ የስደተኞች ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 1110/2011 እንዲፀድቅ ተደርጓል::

አዋጁን ለማስፈፀም የስደተኞችና ተመላሾች አገልግሎት ሦስት መመሪያዎችን በሥራ ላይ እንዲውሉ ያደረገ ሲሆን፣ እነርሱም፤ ስደተኞች በሥራ ላይ የሚሰማሩበትን ሁኔታ ለመወሰን የወጣ የአሠራር መመሪያ፣ ስደተኞች ከመጠለያ ጣቢያ ውጭ የሚንቀሳቀሱበትና የሚኖሩበትን ሁኔታ ለመወሰን የወጣ መመሪያ እና የስደተኞች ቅሬታና አቤቱታ ማስተናገጃ መመሪያ ናቸው::

በአጠቃላይ ኢትዮጵያ የእንግዳ ተቀባይነት ባሕሪዋ ስደተኞችን በማስተናገድ ተመስጋኝ እንድትሆን አድርጓታል:: የኢትዮጵያ ባህል ሕዝቡን ሁሉ ዲፕሎማት አድርጎታል ማለት ነው::

# ዓለም አቀፍ



## ሰሜን ኮሪያ ያስወነጨፈችው ሚሳይል አየር ላይ መፈንዳቱ ተገለጸ

በጋዜጣው ሪፖርተር

ሰሜን ኮሪያ ከምስራቅ ጠረፍ ያስወነጨፈችው ሀይፐርሶኒክ ሚሳይል እንደሆነ የተገመተው መሣሪያ አየር ላይ መፈንዳቱን የደቡብ ኮሪያ ጦር አስታውቋል።

የደቡብ ኮሪያ ጦር አዛዥ እንደተናገሩት፤ ሚሳይሉ የተተኮሰው ከዋና ከተማዋ ፒዮንግያንግ በቅርብ ርቀት ከሚገኝ ቦታ ነው።

የጃፓን መከላከያ ሚኒስቴር በበኩሉ ሚሳይሉ በ100 ኪሎሜትር ከፍታ ላይ ሲበር እንደነበር እና 200 ኪሎ ሜትር ርቀት እንደሚሸፍን ገልጿል።

የደቡብ ኮሪያ፣ አሜሪካ እና ጃፓን ከፍተኛ ባለሥልጣናት የሚሳይል ማስወንጨፍ ሙከራው በርካታ የተመድ የፀጥታው ምክር ቤት ሕጎችን ይጥሳል በሚል አውግዘውታል።

የደቡብ ኮሪያ እና አሜሪካ አየር ኃይሎች በኤፍ-22 እና ኤፍ-35 የጦር አውሮፕላኖች የታገዘ ዓመታዊ የጋራ ልምምድ ማድረጋቸውንም ገልጸዋል።

የደቡብ ኮሪያ ባሕር ኃይል ደቡብ ኮሪያን ከሰሜን ኮሪያ ጋር በሚያዋስነው የማሪታይም ድንበር በተናጠል ልምምድ አድርገዋል። ይህ ልምምድ የተካሄደው ሴውል የኢንተር ኮሪያ ወታደራዊ ስምምነትን ከሰረዘች በኋላ ለመጀመሪያ ጊዜ ነው።

የአሜሪካ፣ የኢንዶ ፓሲፊክ እዝ የሰሜን ኮሪያን ድርጊት አውግዞ፣ ፒዮንግያንግ ከእንዲህ አይነት ሕጋዊ ያልሆነ እና ሠላም የሚያደፈርስ ተግባሯ እንድትቆጠብ ጥሪ አቅርቧል።

“ይህ ክስተት በአሜሪካ ወታደሮች፣ ግዛት እና አጋሮቿ ላይ ጥቃት ባያደርስም፣ ሁኔታውን መከታተላችንን እንቀጥላለን” ብሏል እዙ ባወጣው መግለጫ።

ሰሜን ኮሪያ ለመጨረሻ ጊዜ ሚሳይል የሞከረችው በፈረንጆች ባለፈው ግንቦት 30 ነበር።

አሜሪካ ከደቡብ ኮሪያ ጋር ለምታደርገው ልምምድ የጦር ጄት ተሸካሚ መርከብ መላኳን ባለፈው ሳምንት የተቃወመችው ሰሜን ኮሪያ በርካታ የማስጠንቀቂያ ሙከራዎችን እንደምታደርግ አስጠንቅቃ ነበር።


የሚሳይል ማስወንጨፍ ሙከራው የተደረገው የኮሪያ የእርስ በእርስ ጦርነት የተጀመረበት 74ኛ ዓመት ከተከበረ ከአንድ ቀን በኋላ ነው።

ባለፈው ሳምንት የሰሜን ኮሪያው መሪ ኪም ጆንግ ኡን እና የሩሲያው ፕሬዚዳንት ቭላድሚር ፑቲን ወታደራዊ ጥቃት በሚሰነዘርባቸው ወቅት አንደኛቸው ለሌላኛቸው ሁሉንም አይነት ድጋፍ ለማድረግ የሚያስችላቸውን ስምምነት ተፈራርመዋል።

ሴውል፣ ዋሽንግተን እና ቶኪዮ የሁለቱን ሀገራት ወታደራዊ ግንኙት መጠናከር ያወገዙ ሲሆን የደቡብ ኮሪያው ፕሬዚዳንት ዩን ሱክ ዩኦል ደግሞ ስምምነት “ኋላቀር” ሲሉ አጣጥለውታል።

## በሱዳን ከጥይት በበለጠ ረሃብ በርካቶችን ለሞት እየዳረገ ነው - ሃምዶክ

በጋዜጣው ሪፖርተር



በሱዳን ጦርነት ምክንያት በረሃብ የሚያልቀው ሕዝብ ቁጥር አሳሳቢ መሆኑን የቀድሞው የሀገሪቱ ጠቅላይ ሚኒስትር አብደላ ሃምዶክ ተናገሩ።

ሃምዶክ ከዘናሽናል ጋዜጣ ጋር ባደረጉት ቆይታ ሱዳናውያን በጦርነቱ ምክንያት “ከሚታሰበው በላይ ስቃይ” ውስጥ እንደሚገኙ ነው የገለጹት።

ከ10 ሚሊዮን በላይ ሰዎች በሀገር ውስጥ የተፈናቀሉባት እና ከ25 ሚሊዮን በላይ ሕዝብ በረሃብና ቸነፈር ውስጥ የሚገኙባትን ሱዳን ቀውስ ለመፍታት ፈጣን እርምጃ ያሻል ብለዋል።

በሰሜን ዳርፉር ዋና ከተማ ኤል ፋሸር ለሳምንታት የዘለቀ ጦርነት እየተካሄደ መሆኑን ያነሱት የቀድሞው ጠቅላይ ሚኒስትር፥ የሱዳን ጦርና የፈጥኖ ደራሽ ኃይሉ በመላ ሀገሪቱ እያካሄዱት ያለው ጦርነት በፖለቲካዊ ንግግር እንዲቆም ጥረት እያደረጉ መሆኑን አንስተዋል።

የሱዳን የሲቪል ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ጥምረት ሊቀመንበሩ ሃምዶክ ከሰሞኑ በኖርዌይ መዲና ኦስሎ በሱዳን ወቅታዊ ሁኔታ ላይ ባተኮረው ምክክር ተሳትፈዋል።

ነፃነቷን ከማወጇ አስቀድሞ ከፈረንጆቹ 1955 ጀምሮ ጦርነት የተፈራረቀባት ሱዳን፥ ከ2 ሚሊዮን በላይ ዜጎቿን በእርስ በርስ ጦርነት አጥታለች፤ በዳርፉር የዘር ፍጅትም ከ300 ሺህ በላይ ሱዳናውያን ሕይወታቸው መቀጠፉን የመንግሥታቱ ድርጅት መረጃ ያሳያል።

ካርቱም በየጊዜው በሚቀያየር ሕገመንግሥት እና ወታደራዊ መንግሥት መመራቷ ከጦርነት አባዜ እንዳትወጣ እንዳደረጋትም ነው አብደላ ሃምዶክ ለዘናሽናል የተናገሩት።

ሱዳንን ለ30 ዓመታት የመሩት ኦማር አል በሽር ከሥልጣን እንደተወገዱ ከ2019 እስከ 2021 ጠቅላይ ሚኒስትር ሆነው ያገለገሉት ሃምዶክ፥ በተፋላሚዎቹ ጄኔራሎች ላይ ጫና ለማሳደርና የሲቪል አስተዳደር እንዲቋቋም እየሠሩ ነው።

በጥቅምት ወር 2023 ባቋቋሙት የሲቪል ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ጥምረት (ታቃዱም) ስርም የተለያዩ ሲቪል ተቋማት እና የፖለቲካ ኃይሎችን ለማቀራረብ ጥረት በማድረግ ላይ ናቸው።

የመጀመሪያ ስብሰባቸውንም በአዲስ አበባ አድርገው ባለፈው ወርም ከ600 በላይ ተሳታፊዎች በተገኙበት ምክክር ማድረጋቸው ይታወሳል።

የሱዳን ዲያስፖራዎችን እና የሲቪል ተቋማትን እያስተሳሰረ ያለው “ታቃዱም” ጄኔራል አብዱልፈታህ አልቡርሃን እና ጄኔራል ሃምዳን ዳጋሎ (ሄሚቲ) ልዩነታቸውን በፖለቲካዊ ንግግር እንዲፈቱና ሱዳን ከጦርነት አዙሪት እንድትወጣ የጀመረውን ጥረት ዓለማቀፉ ማኅበረሰብ እንዲደግፍ ሃምዶክ ጠይቀዋል።

ባለፈው ዓመት ሚያዚያ ወር የጀመረው የሱዳን ጄኔራሎች ፍልሚያ በንግግር እንዲቆም ሳዑዲ ዓረቢያ እና አሜሪካ በጂዳ ካደረጉትና በአጭሩ ከተቀጨው ሙከራ ውጭ እስካሁን ተስፋ ሰጪ ንግግር አልተካሄደም።

የምስራቅ አፍሪካ በይነ መንግሥታት (ኢጋድ) እና የሱዳን ጎረቤቶች ተፋላሚ ጄኔራሎቹን ፊት ለፊት ለማገናኘት ያደረጉት ሙከራም ሳይሳካ መቅረቱ ይታወቃል።

# “የኅብረተሰቡን ተሳትፎ ማሳደግና የጎደሉ ነገሮችን ቆጥረን መሙላት ከቻልን ብልፅግናን ለማረጋገጥ የጀመርነው ሥራ የሚሳካበት ጊዜ ሩቅ አይሆንም”

- አቶ እንዳሻው ጣሰው
የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ርዕሰ መስተዳድር

ፋንታነሽ ክንዴ

አዲስ አበባ፡- የኅብረተሰቡን ተሳትፎ በየጊዜው ማሳደግና የጎደሉ ነገሮችን ቆጥረን መሙላት ከቻልን የሕዝባችንን ኑሮ ለመቀየርና ብልፅግናን በኢትዮጵያ ለማረጋገጥ የጀመርነው ሥራ የሚሳካበት ጊዜ ሩቅ አይሆንም ሲሉ የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ርዕሰ መስተዳድር አቶ እንዳሻው ጣሰው ገለጹ፡፡

ከለውጡ ትሩፋቶች አንዱ ዋና እና አጋር የሚለውን ሁኔታ በመቀየር ሁሉም ለኢትዮጵያ ዋና መሆኑን ማረጋገጥ መቻሉ መሆኑንም ጠቁመዋል፡፡

ርዕሰ መስተዳድሩ ያለፉትን የለውጥ ዓመታት ጉዞና በክልሉ የተመዘገቡ ስኬቶችን በሚመለከት በሰጡት ማብራሪያ እንዳሉት፤ በባለፉት ዓመታት ምንም እንኳን በተለያዩ ችግሮች ውስጥ ብናልፍም ከፍተኛ የኢኮኖሚ እድገት ማስመዝገብ ተችሏል፡፡

እድገቱን እኛ ብቻ ሳንሆን የኢኮኖሚ እድገት የሚመዝኑ ሀገራት መዝነው እንዳረጋገጡት በጦርነት ውስጥም ሆነን ከስድስት ነጥብ አምስት እስከ ሰባት ነጥብ አምስት በመቶ ኢኮኖሚያዊ እድገት ተመዝግቧል፡፡ ይህ የአመራሩ መግባባትና ውሕደት እንዲሁም ሕዝቡን አስተባብሮ መሥራት መቻሉ የፈጠረው ነው፡፡

በቀጣይነትም ሀገሪቱን ወደተሻለ ደረጃ ለማድረስ እስካሁን የነበሩ ጥረቶች ተጠናክረው መቀጠል እንደሚኖርባቸው ጠቅሰው፤ አሁን የምንሰጠው አመራር ብቻ በቂ አይደለም፡፡ አዳዲስ ሀሳቦችን ማምጣትና ማፍለቅ፣ የኅብረተሰቡን ተሳትፎ በየጊዜው ማሳደግና የጎደሉ ነገሮችን ቆጥረን መሙላት ይጠበቅብናል ብለዋል።

ይህን ማድረግ የምንችል ከሆነ የሕዝባችንን ኑሮ ለመቀየርና ብልፅግናን በኢትዮጵያ ለማረጋገጥ የጀመርነው ሥራ የሚሳካበት ጊዜ ሩቅ አይሆንም ብለዋል ርዕሰ መስተዳድሩ፡፡

አሁን ያለንበት ዘመን የግሎባላይዜሽን ዘመን በመሆኑ ዓለም ወደ አንድ መንደር መምጣቷን ገልጸው፤ ይህም ለማደግ እና ድሎችን ለማስመዝገብ ውድድራችን ከብዙ ሀገራት ጋር እንዲሆን ያደርገዋል ብለዋል፡፡

ስለሆነም ይህን ውድድር በአግባቡ መረዳትና ኢትዮጵያ ባለችበት ጂኦ ፖለቲካዊ አቀማመጥ ምክንያት የስበት ማዕከል መሆኗን በመገንዘብ ለእያንዳንዱ እንቅስቃሴ ትንተና መስጠት ይኖርብናል ብለዋል፡፡

ርዕሰ መስተዳድሩ እንዳሉት የብልፅግና ፓርቲ ከምሥረታው ዋዜማ ጀምሮ በፕሮግራሞቹ ውስጥ ከያዛቸው ጉዳዮች አንዱ ግማሹ በደንብ በፓርቲ ውስጥ የሚሳተፍ ግማሹ ደግሞ ውጪ ሆኖ የሚመለከት እንዳይሆን ማድረግ ነው፡፡

በዚህ ዋና እና አጋር የሚለውን አገላለጽና አሠራር በመቀየር ሁሉም ለኢትዮጵያ ዋና መሆኑን ማረጋገጥ መቻሉ ከለውጡ ትሩፋቶች አንዱ ነው ብለዋል፡፡

ሁሉም ለኢትዮጵያ ዋና ነው የሚል አስተሳሰብና ፕሮግራም መሠረት ከተቀረጸ በኋላ በሁሉም ክልሎች ያሉ አመራሮች ክልላቸውን እየመሩ በፌዴራል መንግሥቱ ላይም በቂ አስተዋፅዖ እንዲኖራቸው ተደርጓል ያሉት ርዕሰ መስተዳድሩ፤ ሁሉም ያለልዩነት ለሀገሩ እኩል ይንቀሳቀሳል፡፡ በዚህም በብልፅግና ዘመን የሥልጣን ፍትሐዊነት ክፍፍል ላይ ብዙ ነገር ተሻሽሏል ሲሉ ተናግረዋል፡፡

ለውጡ የተመራበት አጠቃላይ ሂደት ሪፎርም በመሆኑ ብዙ ነገሮች አብሮ ይዞ እንደሚሄድ ጠቁመው፤ ሪፎርም በደንብ ጠርቶ የሆነ ደረጃ እስኪደርስ በሕዝቡ ውስጥ ብቻ ሳይሆን በአመራሩ ውስጥም ብዙ ውዥንብር ይፈጠራል ብለዋል፡፡

በዚህም መንግሥት የቀረጻቸውን ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች ተግባራዊ ለማድረግ የአመራር ቁመናን ማስተካከል በጣም ፈታኝ የነበረ፣ ግን ደግሞ የተሻገርነው ነው ብለዋል፡፡

# ኢትዮጵያዊቷ ላምበርጊን

ቃልኪዳን አሳዬ

## ዜና ሐተታ


ወጣት ሀብታሙ አበራ

ወጣት ሀብታሙ አበራ ይባላል፤ ቀን በጋራዥ ውስጥ ተቀጥሮ እየሠራ ትምህርቱን በማታ መርሐግብር ሲከታተል ቆይቷል፡፡ ትምህርቱንም በቴክኒክና ሙያ ኮሌጅ እስከ ደረጃ ሁለት አጠናቋል፡፡ ከትምህርቱ ይልቅ ሙያው ላይ በማተኮር በጋራዥ ውስጥ ለበርካታ ዓመታት የሠራ ሲሆን በሙያውም ለ15 ዓመታት ያክል ሠርቷል፡፡ ያገኘው ልምድ ሙያውንም በሚገባ እንዲያዳብር አግዞታል፡፡

አዲስ ነገር ለማወቅም ሆነ ለመፍጠር ጥልቅ ፍላጎት እንዳለው የሚናገረው ወጣት ሀብታሙ፤ አዲስ ነገር ለመማርና ለማወቅ ፍላጎቱ ካለን ሁሉም ቀላል ነው ይላል፡፡ በዘርፉ ላይ ያለው አረዳድ እያደገ ሲመጣ አዳዲስ ነገሮች ከኢንተርኔት ዳሰሳ በማድረግ እራሱን በራሱ ማስተማሩን ቀጠለ፡፡

ወጣቱን ያገኘነው በአዲስ አበባ ኤግዚቢሽን ማዕከል እየተካሄደ በሚገኘው 14ኛው ከተማ አቀፍ የቴክኒክና ሙያ ሳምንት ላይ የቦሌ ማኑፋክቸሪንግ ኮሌጅን በመወከል ተሳትፎ እያደረገ ባለበት ወቅት ነው፡፡ ለእይታ ያቀረበውም በራሱ ሀሳብ አመንጭነት የሠራውን የመኪና ሞዴል ነው፡፡

ሲያዩዋት ላምበርጊንን የምትመስለዋ አዲሷ በወጣት ሀብታሙ የተሠራችው መኪና በሚሠራበት የተቋም ስያሜ ኤች ቢኤም በመባል ተሰይማለች፡፡ በሌሎች የዓለም ሀገራት የሚታወቁ እንደላምበርጊን፣ ፌራሪና ኡጋቲን ከመሳሰሉት እንደሞዴል ተደርጋ የተሠራች ሲሆን ይችን መኪና ሠርቶ ለመጨረስ ከሁለት ዓመታት በላይ ጊዜን ፈጅቶበታል፡፡

መኪናዋን ለመሥራት የሚያስፈልጉ ግብዓቶችን ለማምረት ረጅም ጊዜ እንደወሰደበት የሚናገረው ወጣት ሀብታሙ፤ በዚህም ለበርካታ ጊዜ ሲያፈርስና ሲሠራ መቆየቱንም ይናገራል፡፡ “መኪናዋን በምሠራበት ወቅት ደስ የሚለው ነገር ግን አድካሚ ጊዜያትን አሳልፍያለሁ። ያሳለፍኩት ጊዜ አድካሚ ቢሆንም እለት ከእለት የማየው ለውጥ ደስ የሚል ነበር” ይላል ወደኋላ መለስ ብሎ ሂደቱን እያስታወሰ፡፡

እንደ ወጣት ሀብታሙ ገለጻ፤ ይህችን መኪና ሠርቶ ለመጨረስ የሁለት ዓመታት ጊዜና እስከ ሦስት ሚሊዮን ብር ፈጅቷል፡፡ የቦሌ ማኑፋክቸሪንግ ኮሌጅም ከሀሳብ ባለፈ የመገጣጠሚያ አካላትን ድጋፍ ሲያደርግ ነበር፡፡ አሁን እንደማሳያ ነው ያቀረብኩት፡፡ በቀጣይም ወደ ምርት እገባለሁ። እንደእነኝህ አይነት ተሽከርካሪዎች በውጭው ዓለም ውድና ታዋቂ ግለሰቦች የሚገለገሉባቸው ናቸው፡፡

የመሥሪያ ቦታና የተለያዩ ቁሶችን የሚያግዝ አካል ካገኘ በቅርቡ ወደምርት በመግባት መኪናዋን በኢትዮጵያ ገበያ ላይ የማቅረብ ፍላጎት እንዳለው የሚገልጸው ወጣቱ፤ ባጭር ጊዜ ውስጥ የዚች ሞዴል ያላቸውን በርካታ ተሽከርካሪዎችን በማምረት ለተጠቃሚዎች ማድረስ እንደሚቻል ይናገራል፡፡

መኪናዋን በስፋት በማምረት ለገበያ የማቅረብ እቅዶች ቢኖሩም ዋጋ አልተተመነላትም፤ ነገር ግን እንደእነኝህ አይነት ተሽከርካሪዎች ከውጭ ወደሀገር ውስጥ ሲገቡ እንደ ሞዴሎቹ እስከ ሦስት ሚሊዮን ዶላር በመሸጥ ላይ ናቸው ብሏል፡፡ ወጣት ሀብታሙ በስሩ በቋሚነት ቀጥሮ ከሚያሠራቸው 15 ሠራተኞች በተጨማሪ በርካታ የኮንትራት ሠራተኞች እያሠራ ይገኛል፡፡

ሁሉም ሰው በዚች ዓለም በሚኖርበት ጊዜ ሊያሳካ የሚፈልጋቸው እሳቤዎች አሉት፡፡ እሳቤውንም ከግብ ለማድረስ ሳይሰለችና ሳይደክም በዙሪያው ካሉ ተግዳሮቶች ጋር ታግሎ ወደተግባር መቀየር ይኖርበታል፡፡ የሰው ልጅ ከትንሽ በመነሳት በሂደት ወደግቡ እንደሚደርስና ተስፋ ሳይቆርጡ መጣር እንዳለበት ወጣቱ ይናገራል፡፡

ወጣት ሀብታሙ በቀጣይም በርካታ ቅንጡና ከኢትዮጵያ አየር ንብረት ጋር ተስማሚ የሆኑ ኢትዮጵያዊ ብራንድ ያላቸውና በሀገራዊ እሳቤ የተቃኙ መኪናዎችን በማምረት ለዓለም ገበያ ለማቅረብ ውጥን ይዟል፡፡ ታዲያ በዚህም ጥበብን ከትዕግስት አዋሕዶ ለውጤታማነት ላደረሰው አምላክ ምስጋና ያቀርባል፡፡ እንዲሁም በእውቀትና በግብዓት እየደገፈው ለሚገኘው ቦሌ ማኑፋክቸሪንግ ኮሌጅም ምስጋናውን ችሯል፡፡

# “የንብረት ማስመለስ አዋጁ...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

ምንጩ ያልታወቀ ሀብትን በተመለከተ የተሟላ የሕግ ድንጋጌን ለማሳደግ እንዲሁም ዓለም አቀፍ ግዴታዎችን ለመወጣትና ዓለም አቀፍ የሕግ ስምምነት መስፈርቶችን ለማሟላት እንደተዘጋጀ አስታውቀዋል፡፡

ኢኮኖሚያዊ ወንጀሎች እየተበራከቱ በመምጣታቸው ሰዎች ትርፍ ለማግኘት ብለው የሚፈጽሟቸው ኢኮኖሚያዊ ጥቅሞች ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተበራከቱና ይበልጥ ውስብስብ እየሆኑ መምጣታቸውን ሚኒስትሩ ገልጸዋል፡፡

መሰል ወንጀሎችን ለመከላከልና ሰዎች ከሕገ ወጥ ድርጊታቸው ተቆጥበው በዚህ መንገድ ጥቅም እንዳያገኙ ማድረግ አስፈላጊ በመሆኑ ረቂቅ አዋጁ መዘጋጀቱን ጠቁመዋል፡፡

ሰዎች እንዲህ ያለውን ወንጀል የሚሠሩት ኢኮኖሚያዊ ጥቅም ለማግኘት ብለው ነው ያሉት ሚኒስትሩ፤ እነዚህ ሰዎች ጉዳያቸው በእስራት ብቻ የሚያበቃ ሳይሆን በወንጀል ተግባራቸው ያገኙት ሀብትም የሚወረስ ከሆነ ወደ ወንጀል ተግባር የመሰማራት ዕድላቸውም ሊቀንስ እንደሚችል ጠቁመዋል፡፡

ከዚህ አኳያ የንብረት ማስመለስ ረቂቅ አዋጁ መዘጋጀቱ ኢኮኖሚያዊ ወንጀሎችን ለመከላከል ትልቅ ሚና ያለው እንደሆነም አስታውቀዋል፡፡

በወንጀል የተገኘው ንብረት በሕግ ሲነጠቅ የሚመለሰው ወደ መንግሥት ብቻ ሳይሆን የወንጀል ተጎጂ ወደሆኑ የግል ተበዳዮችም ይሆናል ነው ያሉት፡፡

እንደ ሚኒስትሩ ገለጻ፤ አሁን ያሉት የሕግ ክፍተቶች ማሻሻያ ካልተደረገባቸውና ርምጃ ካልተወሰደ የኢኮኖሚ ወንጀሎች እየተበራከቱና እየሰፉ ይመጣሉ። ወንጀሎቹ ሲበዙ ደግሞ አጠቃላይ የፖለቲካ ኢኮኖሚውን ነጣቂ የማድረግ ዕድሉ ይሰፋል፡፡

በሐቅ፣ በቅንነትና ሕግ አክብሮ ለሚሠሩ ሰዎች የማይመች፤ ለሚዘርፉና ሕግ ለማያከብሩት ደግሞ እንደልባቸው ሀብት የሚያፈሩበት ኢኮኖሚ እንዳይኖርም እንዲህ ያለ አዋጅ አስፈላጊ ነው ሲሉ አብራርተዋል፡፡

አዋጁ ትኩረት የሚያደርገው ከሕዝብ የሚሰርቀው አካል ላይ ነው ያሉት ሚኒስትሩ፤ ሕግንና የሀገርን ኢኮኖሚ የሚደግፉት ላይ አላግባብ ጫና እንዳያስከትል ጥንቃቄ መደረጉን አንስተዋል፡፡

ይህ አካሄድ በኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን በብዙ ሀገራት ተግባራዊ እየተደረገ ያለ ነው በማለት፤ ረቂቅ አዋጁ ሀገራዊና ዓለም አቀፋዊ ተሞክሮና ልምዶችን መሠረት አድርጎ የተዘጋጀ መሆኑን ገልጸዋል፡፡ በዚህም ልምድ ያላቸው ባለሙያዎች ተሳትፎ ማድረጋቸውን ተናግረዋል።

በአሁን ወቅትም ረቂቅ አዋጁ ለተጨማሪ ውይይት ለሚመለከተው ቋሚ ኮሚቴ መመራቱን አስታውቀዋል።

የኢ.ፌ.ዴ.ሪ የንብረት ማስመለስ ረቂቅ አዋጅ ስምንት ክፍሎችና 57 አንቀጾችን ያካተተ ሲሆን፤ በወንጀል የተገኘ ንብረትን ጨምሮ ምንጩ ያልታወቀ ንብረትን እና ሌሎች የኢኮኖሚ ወንጀሎችን ለመለየት፣ ለማገድ፣ ለመያዝ በንብረት አስተዳደር ስር እንዲቆይ ለማድረግ፣ ለመውረስና ዓለም- አቀፍ ትብብር ለማድረግ የሚያስችል አንድ ወጥ ሕግ የሚያስፈልግ በመሆኑ ፍትሕ ሚኒስቴር ለፓርላማ ያቀረበው ረቂቅ አዋጅ ነው፡፡

# በዘንድሮው ፈተና የተሻለ ውጤት ለማስመዝገብ...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ስትሠራ መቆየቷን የገለጸችው ተማሪ ደራርቱ፤ አሁን ላይ በንባብ ራሷን ብቁ በማድረጓ የነበራት ፍርሐት መቀነሱን ተናግራለች። በዚህም በማትሪክ ፈተና የተሻለ ውጤት ለማምጣት አስፈላጊውን ዝግጅት ማድረጓን ገልጻለች።

“የ2016 ዓ.ም የ12ኛ ክፍል ፈተና ከሐምሌ 3 ቀን 2016 ጀምሮ የሚሰጥ በመሆኑ ለፈተና ያለው ጊዜ አጭር ነው፡፡ በመሆኑም ተማሪዎች በርካታ የማትሪክ ጥያቄዎችን በአጭር ጊዜ ውስጥ ቢሠሩ ውጤታማ ሊሆኑ ይችላሉ። እኔም በርካታ ጥያቄዎችን በመሥራት ያነበብኩትን የማስታወስ ሥራ እየሠራሁ ነው” ያለችው ደግሞ ተማሪ ቅድስት ወርቁ ነች።

ተማሪ ቅድስት የኮተቤ ቀዳማይ ምኒሊክ ሳይንስ ሼርድ ካምፓስ የተፈጥሮ ሳይንስ ተማሪ ስትሆን በማትሪክ ፈተና ጥሩ ውጤት ለማምጣት ከሌሎች ተማሪዎች ጋር በርካታ የማትሪክ ጥያቄዎችን እየሠራች እንደሆነ እና ሰፊ ሃሳብ የያዙ ምዕራፎችን በጥልቀት እየዳሰሰች መሆኑን ተናግራለች።

በጥናት ሂደት የከበዳትን ምዕራፎች ደግሞ መምህሮቿን በመጠየቅ ራሷን ለፈተና እያዘጋጀች ነው። ሞዴል ፈተናም ሁሉንም ትምህርቶችና ምዕራፎች ያካተተ መሆኑ ለፈተናው የምታደርገውን ዝግጅት እንዳጠናከረላት ገልፃለች።


ተማሪ ዕድሳዊት በፍርዱ


ዶ/ር ብርሀነመስቀል ጠና

ተማሪ ዕድላዊት በፍርዱ በበኩሏ፤ በመጪው ሐምሌ ወር ለሚሰጠው የመውጫ ፈተና አስፈላጊውን የጥናት ዝግጅት እያደረገች መሆኑን ገልፃለች። በዝግጅቷም ፈተናውን በውጤት በመቋጨት ለቤተሰቧም ሆነ ለእራሷ ደስታና ስኬትን ለማምጣት የጥናት ዝግጅትና የማካካሻ ትምህርት እየወሰደች እንደምትገኝ ተናግራለች።

ፈተናውን በተሻለ ውጤት ለመቋጨት ተማሪዎች ጥናት ላይ ትኩረት አድርገው መሥራት እንዳለባቸው ተናግራ፤ ለሁሉም የዩኒቨርሲቲ መግቢያ ፈተና ተፈታኞች መልካም ዕድል ተመኝታለች።

የዳግማዊ ምኒሊክ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ምክትል ርዕሰ መምህር ጋዲሴ ደረሰ በበኩላቸው፤ በትምህርት ዘመኑ የተሻለ ውጤት እንዲመዘገብ ከተማሪ፣ ከተማሪ ቤተሰብ እና መምህራን ጋር በጥምረት የተለያዩ ሥራዎች ተሠርተዋል ብለዋል።

በዚህም ለተማሪዎች ተጨማሪ ማጠናከሪያ ትምህርት የተሰጠ ሲሆን የተለያዩ ግዜያት የማትሪክ ጥያቄዎችን በማሰባሰብ ተማሪዎችን ለፈተናው እንዲዘጋጁ ጥረት መደረጉን ገልጸዋል።

የኮተቤ ትምህርት ዩኒቨርሲቲ ፕሬዚዳንት ዶክተር ብርሃነመስቀል ጠና፤ የ12ተኛ ክፍል ተማሪዎች የማትሪክ ውጤት ከፍተኛ እንዲሆን ትምህርት ቤቱ የበኩሉን ሚና እየተወጣ ይገኛል ብለዋል። ትምህርት ቤቱ ተማሪዎች የሥነ ልቦና ዝግጁነት እንዲኖራቸው በተለያዩ ጊዜያት መድረኮችን ማዘጋጀቱንም ጠቁመዋል።

በትምህርት ቤቱ የእለት እለት ክትትል እንደሚያደርጉ የገለጹት ዶክተር ብርሃነመስቀል፤ ለማንኛውም ውጤት የአመራር ሚና ወሳኝ ነው። እንደአመራር በትምህርት ቤቱ ለተማሪዎች አስፈላጊ የሆኑ ግብዓቶችን በማሟላት ብቁ መምህራን በትምህርት ቤቱ እንዲገኙ ተደርጓል ነው ያሉት።

የ12ኛ ክፍል ማጠናቀቂያ ሀገር አቀፍ ፈተና መርሐ ግብርና የኦንላይን ፈተና ለመስጠት እየተደረገ ያለውን ቅድመ ዝግጅት አስመልክቶ በትምህርት ሚኒስቴር መግለጫ መስጠቱ ይታወሳል።

በዚህም የ12ኛ ክፍል ማጠናቀቂያ ሀገር አቀፍ ፈተና በድብልቅ (በወረቀትና በኦንላይን) ለመስጠት አስፈላጊው ዝግጅት እየተደረገ መሆኑን የትምህርት ምዘናና ፈተናዎች አገልግሎት ምክትል ዳይሬክተር አቶ ተፈራ ፈይሳ ገልጸዋል።

በዚህም ለተፈታኝ ተማሪዎች በወረቀትና በኦንላይን ፈተናውን ለመስጠት የሚያስችል አስፈላጊው የፈተና ዝግጅት፣ ኅትመት፣ ተፈታኝ ተማሪዎችን በሥነ ልቦና የማዘጋጀትና በየዩኒቨርሲቲው የመመደብ ሥራ ሲሠራ መቆየቱን ምክትል ዳይሬክተሩ ገልጸዋል።

ሀገር አቀፍ የትምህርት ምዘናና ፈተናዎች አገልግሎት የ2016 ዓ.ም የ12ኛ ክፍል ፈተና ከሐምሌ 3 ቀን 2016 ዓ.ም ጀምሮ እንደሚሰጥ መግለጹ ይታወቃል።

# ስፖርት





# ዓመታዊው ኬሮድ የጎዳና ሩጫ በወልቂጤ ከተማ

ዓስማየሁ ግዛው

የኬሮድ 15 ኪሎ ሜትር የጎዳና ሩጫ ዘንድሮ ለአራተኛ ጊዜ በወልቂጤ ከተማ ሐምሌ 14 ቀን 2016 ዓም የሚካሄድ ይሆናል:: በውድድሩ ታዋቂ አትሌቶችን ጨምሮ የከተማዋ ነዋሪዎች የሚሳተፉ ሲሆን፤ ለአሸናፊዎች ከፍተኛ የገንዘብ ሽልማት መዘጋጀቱም ታውቋል::

በጉራጌ ዞን፣ ወልቂጤ ከተማ ላይ የሚደረገው ዓመታዊው ኬሮድ የ15 ኪሎ ሜትር የጎዳና ሩጫ ተተኪ አትሌቶችን ለማፍራት ታስቦ የሚደረግ ሲሆን፤ ዘንድሮም ለአራተኛ ጊዜ ለማካሄድ ዝግጅቱ በመጠናቀቅ ላይ ነው::

ውድድሩ ሐምሌ 14 ቀን 2016 ዓ.ም መነሻውን ወልቂጤ ዩኒቨርሲቲ፣ መድረሻውን ደግሞ ወልቂጤ ከተማ በማድረግ እንደሚካሄድ የሩጫው አዘጋጆች በሰጡት ጋዜጣዊ መግለጫ አስታውቀዋል:: ከአዋቂዎች ውድድር በተጨማሪ የ1 ኪሎ ሜትር የዊልቸር ውድድር፤ እንዲሁም የሕጻናት ሩጫ ለማካሄድም ከዞኑ አስተዳደር ጋር ውይይት እየተደረገ ነው:: ውድድሩ በተሳካ ሁኔታ እንዲካሄድና የፀጥታ ችግር እንዳይገጥምም ቅድመ ዝግጅቱ ተጠናቋል::

በውድድሩ ከሁሉም ክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች የተወጣጡ አትሌቶች የሚሳተፉ ሲሆን፤ ምዝገባውም ከዛሬ ሰኔ 20 ቀን 2016 ዓም ጀምሮ እንደሚካሄድም ተነግሯል:: በርካታ አትሌቶች ይሳተፉሉ ተብሎ በሚጠበቀው ሩጫ፤ ከ600 በላይ አትሌቶችን እና ከ10ሺህ በላይ የኅብረተሰብ ክፍልን ለማሳተፍ ታቅዷል:: ለውድድሩ ወደ ከተማዋ ለሚጓዙ አትሌቶችም ከወልቂጤ ዩኒቨርሲቲ ጋር በመሆን የደርሶ መልስ መጓጓዣ፤ እንዲሁም ማረፊያ ተዘጋጅቷል:: የከተማዋ ነዋሪም በስፋት ወጥቶ በሩጫው እየተዝናና እንዲሳተፍም ከፍተኛ የቅስቀሳ ሥራዎች እየተሠሩ እንደሆነ ተገልጿል::

በውድድሩ ለሚያሸንፉ አትሌቶች ከፍተኛ የገንዘብ ሽልማት የተዘጋጀ ሲሆን፣ ክብረወሰን የሚያሻሽሉ አትሌቶች ደግሞ ተጨማሪ የገንዘብ ሽልማት የሚያገኙ ይሆናል:: በሁለቱም ፆታዎች አንደኛ ደረጃን በመያዝ የሚያጠናቅቁ አትሌቶች 100ሺህ ብር ሲሸለሙ፤ በወንዶች 43 እና በሴቶች 51 ደቂቃ የሆነውን የቦታውን ክብረወሰን የሚያሻሽሉ አትሌቶች ተጨማሪ ጉርሻ ያገኛሉ:: ከሁለተኛ እስከ ስድስተኛ ደረጃን በመያዝ ለሚያጠናቅቁትም የገንዘብ ሽልማት የተዘጋጀ ሲሆን እንደየደረጃው ከ50ሺህ ብር እስከ 5ሺ ብር ሽልማት ይበረከትላቸዋል::

በጋዜጣዊ መግለጫው ላይ የተሳተፈው አሰልጣኝ ተሰማ አብሽሮ፤ ከባለፈው ዓመት የተሻለ ተሳታፊ እንዲወዳደር ከዞኑ አስተዳደር ጋር እየሠሩ መሆኑን ጠቁሟል:: የውድድሩ ዓላማ ለታዳጊ አትሌቶች የውድድር ዕድልን መፍጠር ነው:: በከተማዋ የሚገኙ ታዳጊ አትሌቶች የውድድር ዕድልን በማግኘት የክለቦች ዓይን ውስጥ የሚገቡበትን ሁኔታ ማመቻቸት ዋንኛው ግቡ ነው:: ከውድድሩ በተጨማሪም በአራት ክልሎች የታዳጊ ፕሮጀክቶችን ለማቋቋምም ታስቧል:: የውድድሩን ደረጃ ከፍ ለማድረግና በዓለም አቀፍ ደረጃ ለማስመዝገብም ከሚመለከታቸው አካላት ጋር እየተሠራ እንደሆነም ገልጿል::




አትሌት ሰለሞን ባረጋ በበኩሉ ክረምት መሆኑ ለውድድር አመቺ ባይሆንም ከሌሎች ውድድሮች ጋር እንዳይጋጭ ታስቦ በዚህ ወቅት እንደሚካሄድ ጠቅሷል:: ለውድድር የሚያመቸውን ጊዜ ለመምረጥ ከአትሌቶች ጋር ውይይት መደረጉንና ውድድሮች ከመጀመራቸው በፊት እና ማጠናቀቂያ ላይ ለማካሄድ ታስቦ እየተሠራ መሆኑንም ገልጿል:: ከዚህ በፊት በተካሄዱ ሦስት ውድድሮች ጥሩ ምልክት የታየ ሲሆን፣ ዘንድሮም ውጤታማ አትሌቶችን ለማግኘት ዝግጅት ላይ ይገኛሉ::

ማኅበሩ አዲስ አበባን ጨምሮ በሌሎች የክልል ከተሞች ተመሳሳይ የሩጫ ውድድር የማድረግ ፍላጎት ቢኖረውም በፀጥታ ስጋት ምክንያት እንዳልተቻለ ተመላክቷል:: ውድድሩ እስከ አሁን በወልቂጤና ቡታጅራ እየተካሄደ ያለ ሲሆን በቀጣይ ወራቤ እና በሆሳዕና ከተሞች ለማካሄድ፤ ከዚያም በሁሉም ክልሎች ለማስፋፋት ታቅዶ ከፌዴሬሽኖች ጋር እየተሠራ መሆኑን አዘጋጆቹ ገልጸዋል::

ኬሮድ ሩጫ አዘጋጅ ማኅበር የተመሰረተው በታዋቂ አሰልጣኞችና አትሌቶች ሲሆን አትሌት ሰለሞን ባረጋ፣ ሙክታር እድሪስ፣ አየለ አብሽሮ፣ ጥላሁን ኃይሌ እና አሠልጣኝ ተሰማ አብሽሮ ከመሥራቾቹ ውስጥ የሚጠቀሱ ናቸው::

በመድረኩ የተሳተፉ አትሌቶች ከሽልማት በተጨማሪ የውጪ የውድድር ዕድሎችን በማግኘት ራሳቸውን ማሳየት እንደቻሉ የተገለጸ ሲሆን፤ ከ1-25 ባለው ደረጃ የሚያጠናቅቁ አትሌቶች ውጪ ሄደው እንዲወዳደሩ የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን መፍቀዱንም በጋዜጣዊ መግለጫው ተብራርቷል::


የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት
Ethiopian Electric Utility

## INVITATION FOR BIDS

### Bid No.EEU-PPMO- OGU/ADELE /NCB-017

1. The Ethiopian Electric Utility (EEU) Project Portfolio Management Directorate intends to purchase different office furniture through National competitive bidding **(NCB).**
2. The Ethiopian Electric Utility Project Portfolio Management Directorate invites sealed bids from eligible bidders for the following goods.

| S. No. | Description of goods | Bid security amount (ETB) | Bid closing date | Bid opening date |
|---|---|---|---|---|
| 1 | Office Furniture | 450,000.00 | July 26, 2024 at 2:00pm | July 26, 2024 at 2:30pm |

3. Bidding will be conducted in accordance with the open tendering procedures contained in the public procurement proclamation of the government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and open to all bidders from eligible bidders.
4. Interested eligible bidders may obtain further information from Ethiopian Electric Utility (EEU) Project portfolio management and inspect the bidding documents at the address given below.

Ethiopian Electric Utility (EEU) Project Portfolio Management Office, Procurement, Logistics, Warehouse & Facility 11th Floor New Mahberawi Wasetina Building Near to Statistics Agency Addis Ababa, Ethiopia P.O.BOX 1233 Tel, +251-11-1263159/ 09 11 66 65 78

5. A complete set of bidding Documents may be purchased by interested Bidders at the address above and upon payment of a non-refundable fee of against payment receipt of ETB 300.00 (Three Hundred birr).
6. Bids must be delivered to the address mentioned above before the closing date and time. All bids must be accompanied by a bid security as mentioned above. Late bids shall be rejected.
7. Bids will be opened in the presence of the bidders or bidders representatives' who choose to attend at the address above on the above mentioned date and time.
8. Bidders are advised to submit their offer after examining the bid document carefully.
9. The Ethiopian Electric Utility (EEU) Project Portfolio Management reserves the right to reject all or partial bid without arranging any request.

**Ethiopian Electric Utility (EEU) Project Portfolio Management Directorate**